DSpace Institution

DSpace Repository http://dspace.org

Ethiopian Languages and Literature - Amharic Thesis and Dissertations

2015-02

# þÿ u `E` ( f õ • ( Ì •ce

þÿ è, «3

http://ir.bdu.edu.et/handle/123456789/15250

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ሞት በቅበላ ረጅም ልቦለድ ነገረ ህላዌ ንባብ

በ

ሙሉየ ካሳ

የካቲት 2015 ዓ.ም

ባሕር ዳር

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል

# ሞት በቅበላ ረጅም ልቦለድ፤ ነገረ ህላዌ ንባብ

ለሁለተኛ  ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

በ

ሙሉየ ካሳ

አማካሪ

ዶ/ር ስንታየሁ ገነት

የካቲት 2015 ዓ.ም

ባሕር ዳር

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናት “ሞት በቅበላ ረጅም ልቦለድ፣ ነገረ ህላዌ ንባብ” በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ መመረቂያ ጽሁፍ ነው፡፡ ጥናቱ የእኔ ወጥ ስራ ሲሆን ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ሥነጽሁፍ ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ሆኖ አልቀረበም፡፡ ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸው መረጃዎችን በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የጥናቱ አቅራቢ፡- ሙሉየ ካሳ እጅጉ

ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ፡- ባሕር ዳር

የቀረበበት ጊዜ---------------------

ፊርማ------------------------------

## ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ

## ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

### የቴሲስ ማረጋገጫ

ይህን “ ሞት በቅበላ ረጅም ልቦለድ፣ ነገረ ህላዌ ንባብ” የተሰኘ የሁለተኛ ዲግሪ መመረቂያ ጽሁፍ በደንቡ መሠረት እያነበብኩ ማማከሬን በማረጋገጥ ለቃል ፈተና እንዲቀርብ ስምምነቴን እገልፃለሁ፡፡

ስንታየሁ ገነት (ዶ/ር) ፊርማ …………… ቀን ……………..

______________________ ________________ ______________

የትምህርት ክፍሉ ኃላፊ ስም ፊርማ ቀን

**ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ**

**ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ- አማርኛ ትምህርት ክፍል**

## የቴሲስ ፈተና ውጤት ማረጋገጫ

እኛ የፈተና ቦርድ አባላት "ሞት በቅበላ ረጅም ልቦለድ፣ ገነረ ህላዌ ንባብ" የሚለውን መመረቂያ ጽሁፍ ፈትነን፣ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ መመረቂያ ጽሁፍ እንዲያሟላ የሚፈለገውን አሟልቶ የተዘጋጀ መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡

የፈተና ቦርድ አባላት

| | | |
|---|---|---|
| ______________________ | __________________ | ______________ |
| የውጭ ፈታኝ ስም | ፊርማ | ቀን |
| ______________________ | __________________ | ______________ |
| የውስጥ ፈታኝ ስም | ፊርማ | ቀን |
| ------------------------- | ---------------------- | ------------------- |
| የፈተናው ሰብሳቢ ስም | ፊርማ | ቀን |

# ምስጋና

በመጀመሪያ ከክፉ ነገር ሁሉ ጠብቆ ለዚህ ደረጃ ላበቃኝ ለልዑል እግዚአብሔር ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያምና ከቅዱሳን ጋር ክብር ምስጋና ይግባው፡፡

አማካሪዬ ዶክተር ስንታየሁ ገነት ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ አሁን ካለበት ደረጃ እንዲደርስ የጎደለዉን በመሙላት የተጣመመዉን በማቃናት ሳትሰለችና ሳትሰስት ለሰጠኸኝ ገንቢና አስተማሪ አስተያየቶችህ ብሎም ለመልካም ስብዕናህ እጅግ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ እግዚአብሔር ዉለታህን ይክፈልህ፡፡

እንዲሁም ዉድ መምህሮቼ ዶ/ር አንተነህ አወቀ እና ዶ/ር አየነዉ ጓዱ በትምህርት ቆይታየ ስላደረጋችሁልኝ መልካም ነገር እና ጥናቱን ስሰራ አስፈለጊውን መጽሐፍት በመላክና  የአባት ምክር በመስጠት ለጥናቱ ከዚህ ደረጃ መድረስ ላደረጋችሁልኝ እገዛ ቢያንስም ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡ በእናንተ በመማሬ በጣም እድለኛ ነኝ፡፡ በተለይም ደግሞ መምህሬ ዶ/ር አንተነህ አወቀ ሁለተኛ ዲግሪዬን እንድማር ስላነሳሱኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ትምህርቴ ዳር ይደርስ ዘንድ በሁሉም ነገር ከጎኔ ሆነሽ የደገፍከኝና ያበረታታሽኝ ዉድ ባለቤቴ ወ/ሮ በለጡ ጌትነት እንዲሁም ልጄ የአብስራ ሙሉየ በጣም አመሰግናችኋለሁ፡፡ አከብራችኋለሁ፡፡

በተጨማሪም ጥናቱን ሳካሂድ ከጎኔ ሆናችሁ በሞራል እና በተለያየ መንገድ የረዳችሁኝ ጓደኞቼ በሙሉ ለውለታችሁ መጣኝ ባይሆንም፤ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

በመጨረሻም የስኬቴን መጨረሻ ለማየት ሁሌም በጸሎታችሁ ያልተለያችሁኝ ዉድ አባቴ አቶ ካሳ እጅጉ እና  እናቴ ወ/ሮ ዳሳሽ ይታየው እንዲሁም ወንድሜ ምስክር እጅጉ በጣም አመሰግናችኋለሁ፡፡

# ማውጫ

**ይዘት** **ገፅ**


ምስጋና ............ i

ማውጫ ............ ii

አጠቃሎ ............ iii

ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ ............ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ............ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ............ 5

1.3. የጥናቱ ዓላማ ............ 6

1.4. የምርምር ጥያቄዎች ............ 6

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ............ 6

1.6. የጥናቱ ወሰን ............ 7

1.7. የጥናቱ ዘዴ ............ 7

1.7.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ............ 8

1.7.2. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ............ 8

1.8. የጥናቱ አደረጃጀት ............ 8

ምዕራፍ ሁለት፡- የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት ............ 10

2.1. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ............ 10

2.2. ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ ............ 13

2.1.1 ነገረ ህላዌ (Existentialism) ............ 13

2.2.2. የነገረ ህላዌ ፍልስፍና ታሪካዊ እድገት ............ 19

2.2.3. ሞት (Death) ............ 25

2.2.3.1. ስነ ህይወታዊ ሞት ............ 29

2.2.3.2. ራስ ግድያ ............ 30

2.2.3.3. ጊዜውን የጠበቀና ጊዜውን ያልጠበቀ ሞት ............ 31

ምዕራፍ ሶስት፡- የሞት ጭብጥ ትንተና በቅበላ ረጅም ልቦለድ ............ 32

3.1. የልቦለዱ አጽመ ታሪክ ............ 32

3.2. ስነ ህይወታዊ ሞት ............ 34

3.3. የራስ ግድያ ............ 43

3.4. ጊዜውን ያልጠበቀ ሞት ............ 50

ምዕራፍ አራት፡- ማጠቃለያ ............ 59

ዋቢ ጽሑፎች ............ 61

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት “ሞት በቅበላ ረጅም ልቦለድ፣ ነገረ ህላዌ ንባብ” በሚል ርዕስ የተጠና ነዉ፡፡ የዚህ ጥናት አብይ ዓላማም ለምርምር በተመረጠዉ ልቦለድ ዉስጥ የነገረ ህላዌ፣ ሞት ጭብጥ ተንትኖ ማቅረብ ነዉ። ይህን ጉዳይ ለማጥናት ምክንያት የሆነዉ ደግሞ ለምርምር የተመረጠዉ ልቦለድ ራሱን ችሎ ሞትን ከነገረ ህላዌ ፍልስፍና አኳያ ጥናት አለመደረጉ፤ የነገረ ህላዌ ጭብጥ፣ ሞት በስፋት ስለሚንፀባረቁበትና በነገረ ህላዌ ሂስ ለማጥናት አመቺ መሆኑ ነዉ። ይህ የህልዉናዊ ጭብጥ ከራሱ ከነገረ ህላዌ ፍልስፍና የሚመነጭ በመሆኑ ይህ ፍልስፍና በመተንተኛ ስልትነት ጥቅም ላይ ዉሏል። በዚህ መሰረት ለምርምር በተመረጠዉ ልቦለድ ዉስጥ ባሉ ገፀ ባህርያት ህልዉና ዉስጥ ተመላልሰዉ የተከሰቱ ዋና ዋና የሞት ጭብጦች ማለትም ስነህይወታዊ ሞት፣ ራስ ግድያ፣ ጊዜውን  የጠበቀ ሞት፣ ጊዜውን ያልጠበቀ ሞት፣ በነገረ ህላዌ ፍልስፍና መተርጎሚያነት ተተንትነዉ ቀርበዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በልቦለዱ የተገለፁት የነገረ ህላዌ ጭብጥ፣ ሞት የትኞቹ እንደሆኑ፣ እነዚህ ጭብጦች መነሻ ምክንያታቸዉ ምን እንደሆና የቀረቡበትን ስልት እንዲሁም በገፀባህሪያቱ ህልዉና ላይ ያስከተሉትን ተፅዕኖ በመተንተን ለማሳየት ተሞክሯል። በዚህ መሰረት በዚህ ልቦለድ የቀረቡ ሁሉም ገፀባህርያት ትርጉም ለማግኘት ይጠይቃሉ፤ ልዩ ልዩ ተግባራትን ይተገብራሉ፡፡ ትርጉም ሲያጡ ምርጫቸዉን ሞት ያደርጋሉ፡፡ በሚደርስባቸዉ የተለያዩ ተፅዕኖዎች ምክንያት የሚኖሩበትን እዉነተኛ ዓለም ይጠላሉ፡፡ በህልም ዓለም መኖርን ይመርጣሉ፡፡ ሁሉም ባለትዳር ገጸ ባህሪያት በሚባል መልኩ የቅርብ የሚሉትን ሰዉ በመግደል ራሳቸውንም በሞት ሲቀጡ ወይም ሲገድሉ ይታያል፡፡ በዚህ ጥናቱ በተሰራበት ልቦለድ ያሉ ገጸ ባህሪያት ጊዜውን ያልጠበቀ ሟች ገጸ ባህሪያት ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በልቦለዱ ውስጥ የተቀረፁ ገጸ ባህርያት ኑሮ ጊዜውን ካልጠበቀ ሞት በተጨማሪ ገድሎ ሟች ናቸው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡ እነዚህ ሁሉ በልቦለዱ የተገለፁት በዚህ ጥናት የተለዩ ናቸዉ፡፡

## ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

ሥነጽሑፍ የሰውን ልጅ የተለያዩ የህይወት ገፅታዎች ሊያሳይ የሚችል የፈጠራ ስራ ነው፡፡ በመሆኑም በተለያዩ የሥነጽሑፍ ዘውጎች (አጭር ልቦለድ፣ ረጅም ልቦለድ፣ ግጥምና ተውኔት) ውስጥ የሚንጸባረቀው በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ በተለያየ መልኩ የሚታዩ ማህበራዊ ገፅታዎች፣ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች፣ ሥነልቦናዊ አመለካከቶች፣ ፖለቲካዊ ጉዳዮች፣ ባህልና ወግ፣ ልማድና ሌሎች ጉዳዮችን ሥነጽሑፋዊ በሆነ ለዛ አስውቦ መልሶ ለሰው ልጅ የሚያበረክት የኪነጥበብ ዘርፍ ነው (ዘሪሁን፣1992፣5-7)፡፡

ሥነጽሑፍ ዘመናዊነትን ከመላበሱ በፊት የሰውን ልጅ የማዝናናትና ሥነምግባርን የማስተማር ተግባራትን ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ይህን አስተምሮውን መነሻ በማድረግ አሁን በየዘመኑ አዳዲስ የፍልስፍና እሳቤዎችንና ንድፈ ሀሳቦችን በማንሳት የእይታ አድማሱን በማስፋት በይነዲሲፕሊናዊነቱን አረጋግጧል፡፡ ለዚህም ማሳያ በዚህ ዘመን የሚካሄዱ የሥነጽሑፍ ጥናቶች የተለያዩ ሀሳቦች የሚንፀባረቁበት በመሆኑ በየጊዜው እድገቱ እንድፋጠን እያደረጉት ይገኛሉ፡፡ ይህም የሥነጽሑፍ ጥናቶች በይነዲሲፕሊናዊ ደረጃ የደረሱት ከተለያዩ ሙያዎች ጋር በማቀራኘት እየተሰሩ በመሆናቸው ነው (ቴዎድሮስ፣ 2001፣xiv)፡፡ በዚህ በሥነጽሑፍ ዙሪያ የሚካሄዱ የጥናት ስራዎች በሙያዎች መካከል ያሉ የሙያ ዲሲፕሊኖችን የተራራቁትን በማቀራረብ፤ የተጎራበቱትን በማዛመድ ድንበሮችን በማፍረስና በማዋሃድ በርካታ የጥናት ስራዎች እየተሰሩ በመሆናቸው የሥነጽሑፍ እድገት በነበረበት ተወስኖ የተቀመጠ ባለመሆኑ ምክያት በይነዲሲፕሊናዊ ደረጃ ላይ መድረሱን አመላክተዋል (ቴዎድሮስ፣ 2001፣xix)፡፡

ሥነጽሐፍ ማለት እውነትን፣ ህይወትን እና ውበትን አጠቃሎ የሚይዝ በሰዎች ለሰዎች ስለሰዎች የሚፃፍ ነው (ዘሪሁን፣1992)፡፡ ይህ ማለት በሰዎች ህይዎት ውስጥ የሚፈጠሩ የሰው ልጅ ባህሪያት ወይም ጠባያት መገለጫ የሆኑ ዘርፉ ብዙ ጉዳዮች በደራሲው የምናብ ነጻነት ኪናዊ ውበት ተላብሰው በሥነጽሐፍ ውስጥ ይገኛሉ ማለት ነው፡፡

ሥነ ጽሑፍ በየዘመኑ በሚነሱ ፍልስፍናዊና ርዕዮተ ዓለማዊ እንቅስቃሴዎች፣ በየጊዜው እንደ አዲስ በሚበቅሉ፣ በሚያድጉና በሚገኑ የእውቀት መስኮች ይሳባል፡፡ እንደአዲስ በቅለውና ገነው የሥነ ጽሑፍን ንድፈ ሐሳብና ሒስ አቅጣጫና ትኩረት ከቀየሱ የእውቀት መስኮች መካከል አንዱ ነገረ ህላዌ ነው፡፡ ቴውድሮስ ገብሬ ማኳሪ(1972)ን ጠቅሰው እንደገለጹት ነገረ ህላዌ

ወይም የህልውና ፍልስፍና መሰረት ተጣለ ተብሎ የሚታመነው በጥንታዊው የግሪክ ስልጣኔ ነው፡፡ በዚህ ዘመን የሰው ልጅ ንቃተ ህሊና እጅጉን ተስሏል፤ እንደ ቀዳሚው የሚቶሎጂ ዘመን በደመ ነፍስ ሳይሆን በሙሉ ንቃት መሰረታዊ ሊባሉ በሚችሉ የህልውና ጥያቄዎችን ማንሳት፣ መመርመርና መፈላሰፍ ጀምሯል፡፡ የፍልስፍናውን ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ጋር ብቻ መቆራኘት የሚተቸው ፍሊን፣ የጀማሪነቱን ማእረግ የሚሰጠው ቅድመ ክርስቶስ ከ469-399 ለኖረው ግሪካዊ ፈላስፋ፣ ለሶቅራጥስ (Socrates) ነው፡፡ ይህ ፈላስፋ እንደ ዘመናዊዎቹ የነገረ ህላዌ ፈላስፎች፣ የፍልስፍናን ትኩረት ከተፈጥሮ (ከ object) ይልቅ ወደ ባለቤቱ (ወደ subject ኡ) ወደ ሰው ልጅ እንዲያዘነብል አስችሏል፡፡ ራስን መጠየቅን እና እራስን ማወቅን የፍልስፍናው ዘዴ የፍልስፍናው ግብ አድርጓል፡፡ (ቴዎድሮስ፣ 2001፣ 141)

ቴዎድሮስ ገብሬ የተለያዩ ምሁራንን ጠቅሰው አያይዘው እንደገለጹት ከዚህ ዘመን በኋላ እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የነገረ ህላዌ ፍንጮች እና አዝማሚያዎች፣ የተለያዩ ፍልስፍናዎችና ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎችን እየታከኩ ነው በተበታተነ መልኩ ብልጭ -ድርግም ሲሉ የኖሩት፡፡ 19ኛው ክፍለ ዘመን፣ የዘመናዊው ነገረ ህላዌ መስራች ተደርገው የሚወሰዱት ዴንማርካዊው ሰ'ረን ኪየርክጋድ (Soren kierkegaard) እና ጀርመናዊው ፍሬድሪክ ኒቼ (Friedrich Nietzsche) የተነሱበት ዘመን ነው፡፡ ኪየርክጋድ በተለይ፣ ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን የሚያተኩርባቸው እና የክርስትና ሃይማኖት ተቋሞችን የሚተችባቸው ጽሁፎቹ የዚህ ፍልስፍናው መከሰቻዎች መሆናቸውን የተለያዩ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡ ዳሩ ግን፣ በዚህ ዘመን ይህ ፈላስፋ ተከታዮችን አልያም የቅርብ ተኪዎችን አላገኘም፡፡ ጽሁፎቹም ቢሆኑ የሚገባቸውን ክብር ማግኘትና መደነቅ የጀመሩት "ትክክለኛው የነገረ ህላዌ ዘመን" ተብሎ በሚጠራው በ20ኛው ክፍለ ዘመን ነው፡፡

20ኛው ክፍለ ዘመን ምንም እንኳ ማርቲን ሃይደጋርን (Martin Heidegger) እና ዣን-ፓል ሳርትርን (Jean-paul sartre) ጨምሮ ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ፈላስፎች የተነሱበት፤ የህልውናዊነትን ንቅነቄ ያቀጣጠሉበት ዘመን ነው ቢባልም፣ እነዚህን ፈላስፎችና ፍልስፍናወቻቸውን በአንድ ወጥ አስተምሮ እንዳልነበር ብዙዎቹ ጸሐፍት ይናገራሉ፡፡ ይሁን እንጂ ፈላስፎቹ የሚጋሯቸው በርካታ ጉዳዮችም አሉ፡፡ በብዙዎቹ ህልውናዊ ፈላስፎች ስራዎች ውስጥ ተመላልሰው የሚመጡ የተወሰኑ ጭብጦች አሉ፡፡ እነዚህን ጭብጦች ማኳሪ (ገጽ 16) በሶስት ወገን ይከፍሏቸዋል፡፡ የመጀመሪያው ወገን ለአንድ ሰው ግለሰባዊ ማንነት መሰረት የሆኑ ሶስት/አራት ጉዳዮችን፣ ማለትም - ጨመቅና ህልውናን (essence and existence)፣ ምርጫና ውሳኔን (choice and decision)፣ እንዲሁም ነጻነትና ሃላፊነት (freedom and

responsibility) የያዘ ነው። እንደ ወንጀለኝነት፣ ሞት፣ ባይተዋርነት፣ ቀቢጸ ተስፋ፣ የመሳሰሉ የሰው ህልውና ትራጀዲያዊ ገጽታዎች ደግሞ በሁለተኛ ወገንነት ይፈረጃሉ። ሶስተኛው ወገን በቀደምት ፈላስፋዎች ትኩረት ተነፍጎት የኖረውን የሰው ልጅ የስሜት ጣጣ ጭንቀት፣ ፍርሃት፣ ስጋት የመሳሰሉ ስሜቶችን ይይዛል። (ቴዎድሮስ፣ 2001፣142-143) በማለት ጠቅሰው አስረድተዋል።

ከነዚህ ጭብጦች ውስጥ የጥናቱ ትኩረት በሁለተኛነት ከተወገኑት ትራጀዲያዊ ገጽታዎች ውስጥ ሞት ላይ የተመሰረተ ነው።

ቴዎድሮስ (2001) ስለሞት የሚከተለውን ብሏል።

> ሞት የነገረ ህላዌ መገለጫ ጭብጦች ከሆኑት፣ የርዕይ መነጠቅ፣ ቀቢጸተስ፣ ራስ ውንጀላ፣ ባይተዋርነት፣ ግዞት እና ባዘናነት አንዱ ነው። እነዚህ ጭብጦች አንዱ ከሌላው ይዛመዳሉ። ይዋለዳሉ። ተዋረዳዊ የሚመስል ግንኙነትም በመካከላቸው እንዳለና በዚህ ተዋረድ ውስጥ ደግሞ የሰው ልጅ ሁለንተናዊ እጣ የሆነው ሞት ትልቁን ስፍራ ይይዛል።

ሞት ከሚጠናባቸው ዲሲፕሊኖች ወይም የሙያ መስኮች መካከል ይህ ጥናት የስነጽሁፍ ዘርፍ በሆነው ልቦለድ ላይ ያተኩራል። ስነጽሁፍ የማይዳስሱት የሙያ መስክ ባለመኖሩ ይዘታቸውን ለመተንተን የሚያስፈልጉ ንድፈ ሃሳቦችን ይጠቀማሉ። በመሆኑም ጥናቱ ሞት የነገሰበትን የአለማየሁ ገላጋይ *ቅበላ* ልቦለድ ለመተንተን የነገረ ህላዌን ንድፈ ሃሳብ የሚጠቀም ሲሆን ትኩረቱም በልቦለዱ ውስጥ የሞት አይነቶችን በመመርመር ላይ ነው። በመሆኑም በዚህ የአለማየሁ ገላጋይ *ቅበላ ረጅም ልቦለድ* መሰረት በማድረግ ሞትን ተንትኖ ለማሳየት ሞክሯል።

ደራሲ እና ሐያሲ አለማየሁ ገላጋይ የተወለደው በ1960 ዓ.ም በአድስ አበባ ከተማ 4 ኪሎ አካባቢ ነው። ትምህርቱንም በዳግማዊ ሚኒልክ ትምህረት ቤት የተማረ ሲሆን ትምህርቱንም እንዳጠናቀቀ በጋዜጠኝነት ሙያ ላይ ተሰማርቶ ለረጅም አመታት በሙያው አገልግሏል። በተለያዩ ጋዜጦችም ወደሰባት በሚደርሱ የብዕር ስሞች ልዩ ልዩ ጽሑፎችን እየጻፈ ለአንባቢያን እንዲደርስ አድርጓል።

በአንድ ወቅት እንደ ደበበ ሰይፉ የአርስቶትልን ፍልስፍና በመከተል “አንድ ደራሲ መጻፍ ያለበት ስድሜው 40 ዓመት ሲሞላ ወይም ከደረሰ በኋላ ቢሆን ይመረጣል” በማለት ለወጣት ደራሲያን ስልጠና ሲሰጡ የታደመው ወጣቱ አለማየሁ ወደሚወደው ሙያ ለመቀላቀል 40

ዓመት እስኪሞላው በትግስት ለመጠበቅ ተገዷል፡፡ በ40 ዓመቱ ገደማ መጻፍ የጀመረው ይህ ስመጥር ደራሲ የመጀመሪያ ስራው "አጥቢያ" ናት፡፡

ደራሲና ሃያሲ አለማየሁ ገላጋይ የድህረ ዘመናዊነት የአጻጻፍ ስልትን ተከትለው ከሚጽፉ የሃገራችን ደራሲዎች መካከል አንዱ መሆኑን የሚመሰክሩ የልቦለድ ድርሰቶችን ለኪነ ጥበብ አፍቃሪያን አበርክቷል፡፡ የብርሃን ፈለጎች፣ ወሪሳ፣ ቅበላ፣ በፍቅር ስም እና ታለ በተሰኙት አምስት ልቦለዳዊ ስራዎቹ ውስጥ ደራሲው የተለያዩ የድህረ ዘመናዊነት አጻጻፍ መገለጫ ስልቶችን በብዛት ተጠቅሞ እናስተውላለን፡፡

ደራሲና ሃያሲ ዓለማየሁ ገላጋይ የተፈጥሯዊነት የአፃፃፍ ስልትን የሚከተልና እንደ ወሲብ ያሉ ተፈጥሯዊ ጉዳዮችን በግጽ የሚያሥቀምጥ የዘመኑ ጸሐፍት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም የሚመጣውን ጥበብ ለጥበብነቱ/ ሥ-ጽሑፍ ለሥነ-ጽሑፋዊነቱ የተሰኘውን መርህ የሚያቀነቅን ደራሲ ነው፡፡

በልቦለዶች የሕይወት አስገኝ የሆነውን ፈጣሪ ሲመረምረው እንቃኛለን፡፡ ዓለማየሁ  ይህን እሳቤ ከደራሲ ስብሀት ግብረ እግዚያብሄር የወሰደው- ይመስላል ስብሀት በአንድ ወቅት "እኔ የምወደው የሐዲስ ኪዳኑን ፈጣሪን(እግዚአብሔር ወልድን/ኢሱስ ክርስቶስን) ነው፡፡ ምክንያቱም እሱ ይቅር ባይ ነው፡፡" በማለት ገልጾ ነበር፡፡ አንዳንድ ሰዎች"አለማየሁ የስብሐት ደቀ መዝሙር ነው፡፡" የሚሉትን ልብ ያላል፡፡ ለምሳሌ ከደራሲ ልብ ወለዶችውስጥ የመጀመሪያ የሆነችው" አጥቢያ"፣ እንዲሁም ተከታትለው የወጡት የብርሀን ፈለጎች እና ወሪሳ በብሉ ኪዳን ዘመናት ይመሰላሉ፡፡ በዚህ ዘመን ፈጣሪ ፍጥረታቱን ከፈጠረ በኂላ ፍጥረታቱ ግራ የተጋቡት እና ልዩ ልዩ ፍጥረቶችን እንደ ፈጠሪ ያዩበት፣ ፈጣሪ የለም ብለውም በርካታ ፈላስፎች የተነሱበት ጊዜ ነው፡፡ "በአዲስ ኪዳን ትመሰላለች"

የደራሲና የሃያሲ አለማየሁ ገላጋይ ልቦለዳዊ ስራዎች በይዘት እረገድ ትኩረታቸውን በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ አያደርጉም፡፡ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ታሪካዊ ይዳስሳል፡፡

አለማየሁ አጥቢያ ካሳተመበት ከ1999 ዓ.ም እስካሁን ባላት ዓመታት ከ10 በላይ ልቦለዳዊ እና ኢ-ልቦለዳዊ መጽሓፍትን ያሳተመ ሲሆን እነሱም አጥቢያ፣ስብሐት ገ/እግዚአብሔር ሕይወት እና ክህሎት፣ ቅበላ፣ የፍልስፍና አጽናፍ፣ ኢሓድግን እከሳለሁ፣ ኩርቢት፣ የብርሃን ፈለጎች፣ መልክአ ስብሐት፣ ወሪሳ፣ መለያየት ሞት ነው፣ የተጠላው እንዳልተጠላ፣ በፍቅር ስም፣ ታለ በእውነት ስም፣ ውልብታና እና ሀሰተኛው በእምነት ስም ናቸው፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው በ2009 ዓ.ም በታተመው ቅበላ ረጅም ልቦለድ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በዚህ ልቦለድ የሞት ጉዳዮችን ከነገረ ህላዌ ፍልስፍና አኳያ በልቦለዱ ውስጥ የተከሰተበትን ሁኔታ ትንተና ይሂል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በተዘዋዋሪም ይሁን በቀጥታ መልኩ ተዛማጅነት ያላቸው በተለያዩ ጊዜያትና በተለያዩ አካላት አማካኝነት ጥናቶች የተደረጉ መሆኑን አጥኚዉ ባደረገዉ የቀደምት ጥናቶች ክለሳ አረጋግጧል፡፡ በዚህ መሰረት ከዚህ ቀደም በአማርኛ ረጅም ልቦለዶች ላይ ከተካሄዱ ጥናቶች መካከል፡- የመጀመሪያዉ የመሰለች ተሻገር(2010) "የነገረ ህላዌ ጭብጦች በአለማየሁ ገላጋይ *ቅበላ*፤ የነገረ ህላዌ ንባብ" የተሰራ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ ባይተዋርነት፣ ከንቱነት፣ ክስተት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ነፃነት፣ ትክክለኛና ትክክለኛ አለመሆን የተሰኙ የነገረ ህላዌ ጭብጦች ነገረ ህላዌ ንድፈ ሀሳብን መሰረት በማድረግ ትንተና አካሂዳለች፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የንጉስ መለሰ(2013) "የህልውናዊነት ጭብጦች ትንተና በትዝታሽ ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ" ረጅም ልቦለድ በሚል ርዕስ የተሰራ ጥናት ነዉ፡፡ ጥናቱ ምርጫ፣ ትርጉምን መፈለግ፣ ብቸኝነት፣ ተፅዕኖ፣ ኢ-ምክንያታዊነትና ባዶነት የተሰኙ የነገረ ህላዌ ጭብጦች ነገረ ህላዌ ንድፈ ሀሳብን መሰረት በማድረግ በትንተና ተካተዋል፡፡ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ጥናት ያካሄዱት መሰለችና ንጉስ የህልውናዊነት ጭብጥ የሆነውን ሞት አካተው አላጠኑም፡፡ በሌላ አገላለጽ ያልተጠኑና ሊጠኑ የሚገባቸዉ በአማርኛ ስነጽሑፍ ስራዎች ዉስጥ የሚገለፁ ሌሎች ጭብጦችን እናገኛለን፡፡ እናም ይህ ሁኔታ የዚህ ጥናት የንድፈሀሳብና የጥናቱን ክፍተት ስለሚሞላ መነሻ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ሶስተኛ የቴዎድሮስ ገብሬ (2011) "የአማርኛ የርእይ መነጠቅ ልቦለዶች" በሚል ርዕስ የተጠናዉ መጣጥፍ ነዉ፡፡ ቴዎድሮ ስለህልውናዊ ንባብ አድርጎ ቢያጠናም ሞትን ራሱን ከነገረ ህላዌ ንባብ አኳያ አላጠናም፡፡ እናም ይህ ሁኔታ የዚህ ጥናት መነሻ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ አራተኛው የአንለይ ወንዲራዴ "ሥነልቡናዊ ሞት በበውቀቱ ስዩም በእንቅልፍ እና እድሜ፤ ፍካሬ ልቡናዊ ንባብ በሚል ርዕስ የተሰራ ጥናት ነዉ፡፡ ይህ ጥናት ሞትን ከፍካሬ ልቡና አንፃር እንጅ ከነገረ ህላዌ አንፃር ሞትን አላጠናም፡፡ የአጥኚው ትኩረት ሞትን ከነገረ ህላዌ አንጻር ስለሚያጠና የጥናቱ መነሻ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ አራቱም ጥናቶች ይዘውት በተነሱት ዓላማ፣ በመጽሐፍ ምርጫ እና በተጠቀሙት ማናበቢያ ጽንሰ-ሐሳብ ከዚህ ጥናት ይለያሉ፡፡ ስለሆነም የንድፈ-ሃሳብ እና የጥናት ዘዴ ክፍተት ለመሙላት ለጥናት እንድነሳሳ አስችሎኛል፡፡

ሁለተኛው አነሳሽ ምክንያት ደግሞ በዚህ ለጥናት የተመረጠው ረጅም ልቦለድ የነገረ ህላዌ ጭብጥ፣ ሞት በስፋት ተንፀባርቆበታል። ይህ የነገረ ህላዌ ጭብጥ በስፋት በመንፀባረቁ ይህን ጥናት በነገረ ህላዌ ፍልስፍና ለማጥናት ምቹ ሆኖ አጥኝው በማግኘቱ የትናት ትኩረቱን በዚህ ላይ እንዲደርግ አነሳስቶታል።

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአለማየሁ ገላጋይ በቅበላ ረጅም ልቦለድ የሞት  ጭብጥ መተንተን ነው።

ይህ ጥናት  የሚከተሉት ንዑሳን ዓላማዎች አሉት ።

ሀ. በልቦለዱ ውስጥ የታዩትን የሞት ጭብጦችን መመርመር

ለ. በልቦለዱ ውስጥ ለሞት መከሰት መንስኤ የሆነው መፈተሽ

ሐ. የገጸ ባህርያት ሞት በሌሎች ባልሞቱት ገጸ ባህርያት ላይ የሚፈጥረውን ተጽዕኖ መተርጎም፣

## 1.4. የምርምር ጥያቄዎች

በዚህ ጥናት ውስጥ ለማሳካት ከሚሞከሩት ዋናና ንዑሳን ዓላማዎች በተጨማሪ በጥናቱ ሂደት ውስጥ ለመመለስ የሚሞከሩ የምርምር ጥያቄዎችም አሉ።

ሀ. በልቦለዱ ውስጥ የታዩት የሞት ጭብጮች ምን ምን ናቸው?

ለ. በተመረጡት ልቦለዱ ውስጥ ለሞት መከሰት ምክንያት ሊሆኑ የቻለ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

ሐ. የገጸ ባህርያት ሞት በሌሎች ባልሞቱት ገጸ ባህርያት ላይ የሚፈጥረውን ተፅዕኖ ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎች ናቸው።

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

አንድ ጥናት ሲጠና ይብዛም ይነስም የራሱ ሆኑ ፋይዳዎች ይኖሩታል። ይህ ጥናትም የሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች መካከል የመጀመሪያዉ አጥኚዉ ይህን ጥናት ለማከናወን የተለያዩ ጽሑፎችን አንብቧል። በዚህም ጥናቱ ትኩረት ባደረገበት የነገረ ህላዌ ፍልስፍና ንድፈ ሀሳቦችና ጭብጥ ዙሪያ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረዉ አድርጎታል። ጥናቱን ለሚያነቡም በተለይም ለዩኒቨርስቲ ተማሪዎችና ተመራማሪዎች ተጨማሪ እዉቀትና ክህሎትን የሚያገኙበትን፣

ለማጣቀሻነት የሚጠቀሙበትን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ያገለግላል። እንዲሁም ሌሎች የስነጽሁፍ አንባቢያን በነገረ ህላዌ ፍልስፍና እና በስነጽሑፍ መካከል ያለዉን ግንኙነት እንዲገነዘቡ ያደርጋል። ይህ ማለት አንድን የስነ ጸሑፍ ስራ ከነገረ ህላዌ አንፃር በመፈተሽ በቀላሉ መረዳት እንዲቻል ያግዛል። በተጨማሪም አንባቢያን ስለልቦለዱ እንዲሁም ስለደራሲዉ የአፃፃፍ ፍልስፍና የበለጠ እንዲገነዘቡት ያደርጋል።

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በአለማየሁ ገላጋይ *በቅበላ* ረጅም ልቦለድ ላይ ሲሆን ይህ ልቦለድ በ2009 ዓ.ም ታትሞ የቀረበ ነው። በዚህ ልቦለድ ውስጥም ሞት እንዴት እንደሚገለጽ ገጸ ባህርያትም በአላማቸው እንዴት ጸንተው እንዳልቀጠሉ እና የገጸ ባህርያት ሞት ምን ምን እንደሆኑ በመተንተን ላይ ብቻ የተመሰረተ ነው። የደራሲውን ሌሎች ስራዎች የማይመለከት ሲሆን፣ ሌላ የስነ ጽሁፋዊ እይታም አይኖርም።

## 1.7. የጥናቱ ዘዴ

የትንተና ዘዴ፡- ጥናቱ ስነ ጽሑፋዊ ጥናት እንደመሆኑ መጠን አይነታዊ የምርምር ዘዴን መሰረት በማድረግ በጥልቅ ንባብ ተተንትኖ ቀርቧል። በሂደቱም ልዩ ልዩ መረጃዎች፣ መጽሐፍት፣ ጥናቶች በጥልቀት ተፈትሸዋል።

ይህ ጥናት በዋናነት ይዞት የተነሳዉ አብይ ጉዳይ ለጥናት በተመረጠዉ ረጅም ልቦለድ ዉስጥ ዋና ዋና የነገረ ህላዌ ጭብጥ፣ ሞትን ዘርዝሮ መተንተን ነዉ።

በመሆኑም እነዚህ ጭብጦች በስፋት ተንፀባርቀዉበታል ተብሎ የታመነበትና ጭብጦችን ለይቶ ለማዉጣት አመቺ ይሆናል ተብሎ የተመረጠዉ ሞት በቅበላ ረጅም ልቦለድ፤ “ነገረ ህላዌ ንባብ” ነው። ይህም የጥናቱን ዓላማ መሰረት ተደርጎ ተመርጧል።

ስለዚህ ለዚህ ጥናት ማስኬጃነት የተመረጠው ልቦለዶች በዉስጡ የያዛቸዉን የነገረ ህላዌ ጭብጥ፣ ሞት ለይቶና ተንትኖ ለማሳየት ያስችላል በሚል እምነት ልቦለዶቹ በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ (Purposive Sampling Method) የተመረጠ ነዉ። በሌላ አባባል አጥኚዉ ይህን ረጅም ልቦለድ ባነበበበት ወቅት በተዋቀረባቸዉ ታሪኮችና በገፀባህርያቱ ኑባሬ ዉስጥ ከዚህ በፊት ካነበባቸዉ ሌሎች ልቦለዶች በተሻለ ህልዉናዊ ጉዳይ፣ ሞት ያነሳ መሆኑን አስተዉሏል።

በተጨማሪም ይህ ለጥናት የተመረጠው ልቦለድ እስካሁን በተደረገ ፍተሻ ጥናት ቢካሄድበትም ሞትን ከነገረ ህላዌ አንጻር ያጠና የሌለ መሆኑን አጥኚዉ አረጋግጧል። በነዚህ ምክንያቶች

አጥኚዉ በልቦለዱ የተገለፁ የህልዉናዊ ጭብጦች፣ ሞት ተንትኖ ለማሳየት ካለዉ ጽኑ ፍላጎት አንፃር ይህን ልቦለድ በናሙናነት መርጧል፡፡

### 1.7.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ለጥናቱ መረጃ ይገኝባቸዋል በሚል ሁለት የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ አንደኛው ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ በመሆን የሚያገለገሉት ራሳቸው ታላሚ የሆነው ቅበላ ረጅም ልቦለድ በውስጡ አጭቆ የያዛቸው የሞት ጣጣዎች በነገረ ህላዌ ንባብ አይቶ ለመፎከር ስለሚያስችል የመጀመሪያ የመረጃ ምንጮች በመሆን አገልግለዋል፡፡ በሁለተኛ ወይም በዳህራይ የመረጃ ምንጭነት የሚያገለገሉት በነገረ ህላዌ ሁነቶች ዙሪያ የተጻፉ የስነ ጽሑፍ ቲዎሪዎች፣ ድርሰቶች እና የምርምር ስራዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ የተመረጠውን ቴክስትና ከጥናቱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መረጃ ይገኝባቸዋል የተባሉ የሥነ ጽሁፍ ስራዎችን በመጠቀም መረጃው መሰብሰብ ተችሏል፡፡

### 1.7.2. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

የመረጃ መተንተኛ ዘዴው በተመረጠው ልበለድ ስራ ውስጥ መረጃውን ለመተንተን የሚያስችል የሰው ልጅ ሞት ነገረ ህላዌ ንባብ በማድረግ ትንታኔ ተካሂዶበታል፡፡ ለትንተናው እንዲያመች ለጭብጦች መንስኤ የሚሆኑ የነገረ ህላዌ  ጣጣዎች ምን ምን እንደሆኑ በምዕራፍ ሁለት በተለዩት መሰረት ከሞት አይነቶቹ ጋር በማስተሳሰር ከቴክስቱ ማሳያ የሚሆኑ ሀሳቦች እየተመረጡ የሀቲት ትንተና ተደርጓል፡፡ ትንተናው መሰረት የሚያደርገው በእያንዳንዱ ታሪክ ውስጥ የሚገኙት ገጸ ባህሪያት በእለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው የሚያጋጥማቸውን የተመሰቃቀለ የህይዎት ውጣ ውረድ ከሞት አይነቶች ጋር እያዛመዱ ማየት ነው፡፡ እንግዲህ የጥናቱ የአተናተን ዘዴና ሂደት ስልቱ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ ለጥናቱ በተመረጡት ልቦለዶች ውስጥ እነዚህ የሞት አይነቶች መገለጫ ባሕሪያት በምን መንገድ እንደተገለጹ ነገረ ህላዌ ንባብ በማድረግ የሃቲት ትንተና ማድረግ ነው፡፡

## 1.8. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በአራት ምዕራፎች የተደራጀ ነው፡፡ በመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱን ማዕቀፍ (framework) የሚያስተዋውቁ አስር ንዑሳን ርዕሶች አካቷል፡፡ እነሱም የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የአጠናን ዘዴ፣ የናሙና አመራርጥ፣ የመረጃ አሰባሰብና አተናተን ዘዴ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

በምዕራፍ ሁለት ደግሞ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትና ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት በሚሉ ሁለት ክፍሎች የተደራጀ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ከሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥ የሆኑ ንድፈ ሃሳቦች በስፋት የተዳሰሱበት ከመሆኑም በተጨማሪ አጥኚው ከሚያጠናው ርዕሰ ጉዳይ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተሰሩ ጥናቶች የዳሰሰበት ምዕራፍ ነው፡፡ በምዕራፍ ሦስት ከልቦለዱ የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነው የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡ ምዕራፍ አራት ደግሞ የጥናቱ ማጠቃለያ የተሰጠበት ነው፡፡

## ምዕራፍ ሁለት፡- የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት

በዚህ ክፍል ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጽሁፎች ለጥናቱ ማስኬጃና መቀንበቢያ የሚያገለግሉ ንድፈ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡ ይህ ምእራፍ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ከጥናቱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ዝምድና ያላቸው ቀደምት ጥናቶች የተዳሰሱበት ክፍል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ስለ ነገረ ህላዌና ሞት ጭብጥ የሚያትተው ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ የቀረበበት ክፍል ነው፡፡

### 2.1. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ክፍል ስር የነገረ ህላዌ የትችት አንፃርን በዋነኛ መነፀርነት በመጠቀም የተለያዩ የነገረ ህላዌ ጭብጦችን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የዳሰሱና ከዚህ ጥናት ጋር በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ዝምድና ያላቸዉ የምርምር ስራዎች ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸዉን ተዛምዶ በሚያሳይ መልኩ ቅኝት ተደርጎበታል፡፡

የነገረ ህላዌ የትችት አንፃርን ዋነኛ ማዕቀፍ በማድረግ የተለያዩ የህልዉናዊነት ጉዳዮችን ለመተንተን የሞከሩ በርካታ የሀገር ዉስጥም ሆነ የዉጭ ጥናቶች አሉ፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት ቅኝት የሚደረግባቸዉ የሀገር ዉስጥ ጥናቶች ይሆናሉ፡፡ ምክንያቱም ይህ ጥናት የሚያተኩረዉ "ሞት በቅበላ ረጅም ልቦለድ፤ ነገረ ህላዌ ንባብ" በሚል ርዕስ ሲሆን ዋና ዓላማዉም በልቦለዱ ዉስጥ የተከሰቱ የሞት ጭብጥ መተንተን ነው፡፡

ስለሆነም በሀገር ዉስጥ በተለይም በአማርኛ ስነ ጽሑፍ ስራዎች በተካሄዱ ጥናቶች ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡ አጥኚዉ የዳሰሳቸዉ ቀደምት ጥናቶች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

በአንደኛ ደረጃ ከእኔ ጥናት ጋር ቀረቤታ ያለዉ የመሰለች ተሻገር "የነገረ ህላዌ ጭብጦች በአለማየሁ ገላጋይ ቅበላ፤ የነገረ ህላዌ ንባብ" በሚል ርዕስ በነሐሴ 2010 ዓ.ም በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበዉ ጥናት ነዉ፡፡

የጥናቱ አቢይ ዓላማም በአለማየሁ ገላጋይ ቅበላ የድርሰት ስራ የተገለፀዉ ታሪክ የነገረ ህላዌ ታሪክ መሆኑን ፈክሮ ማሳየት ነዉ፡፡

ይህን ዓላማ ለማሳካትም ባይተዋርነት፣ ከንቱነት፣ ክስተት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ነፃነት፣ ትክክለኛና ትክክለኛ አለመሆን የተሰኙ የነገረ ህላዌ ጭብጦች ነገረ ህላዌ ንድፈ ሀሳብን መሰረት በማድረግ በትንተና ተካተዋል፡፡ ይህ ጥናት ትኩረቱን ያሳረፈው በአለማየሁ

ገላጋይ ቅበላ ረጅም ልቦለድ ላይ ሲሆን ቴክስቶችን በተናጠል በመፈተሽ በቴክስቱ የበቀለ የነገረ ህላዌ ጭብጦችን በማገናዘብ ድርሰቱ ውስጥ የተነሱት ታሪኮች የነገረ ህላዌ ታሪኮች መሆናቸውን ማሳየት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚዋ እነዚህን ጭብጦች በመተንተን ለጥናት የተመረጠዉ ረጅም ልቦለድ ታሪክ የነገረ ህላዌ ታሪክ መሆኑን መናገር ይቻላል በማለት ከድምዳሜ ደርሳለች፡፡ የመሰለች ጥናት ነገረ ህላዌንና ጭብጦችን የተነተነች ቢሆንም ይዛው በተነሳችው ዓላማ፣ በማናበቢያ ፅንሰ-ሃሳብ፣ በሚተነተኑ ጭብጦች ከዚህ ጥናት ልዩነት አለው፡፡ ይሁን እንጂ እንደ አጥኝው ሂሳዊ ዳሰሳ የመሰለች ጥናት ጥሩ ሒደቶችን የተከተለ ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጅ ከዚህ ጥናት ጋር ቀረቤታ ያለዉና ዳሰሳ የሚደረግበት የቴዎድሮስ ገብሬ በይነ ድሲፕሊናዊ የስነ ጽሑፍ ንባብ በ2011 ዓ.ም በታተመዉ መጽሐፍ ዉስጥ ካሉት አራት መጣጥፎች መካከል "የአማርኛ የርእይ መነጠቅ ልቦለዶች" በሚል ርዕስ የተጠናዉ መጣጥፍ ከዚህ ጥናት ጋር ይዛመዳል፡፡

የቴዎድሮስ ጥናት አቢይ ዓላማ በጥናቱ በተመረጡ አራት ልቦለዶች ማለትም ፍቅር እስከ መቃብር፣ የቴዎድሮስ እምባ፣ አደፍርስና ከአድማስ ባሻገር ዉስጥ የሚኖሩ የጋራ ጉዳዮችንና ተመሳሳይ ገጽታዎችን ፈልጎ ማግኘትና ነድፎ ማሳየት ነዉ ((ቴዎድሮስ፣2001፣134)፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካትም በጥናቱ በተመረጡ ልብወለዶች ዉስጥ በተንፃባረቁ የጋራ የህልዉና ትራጀዲያዊ ገጽታዎች ማለትም ሞት፣የርእይ መነጠቅ እና ቀቢፀ ተስፋ፣ እና ግዞት የተሰኙ ጭብጦች ነገረ ህላዌ ንድፈ ሀሳብን መሰረት በማድረግ ትንተና ተካሂዷባቸዋል፡፡

ከጥናቱም በልቦለዶቹ ዉስጥ ሞት፣ የርእይ መነጠቅ እና ቀቢፀተስፋ፣ እና ግዞት ከነአጃቢዎቻቸዉ የልቦለዶቹን ፈር የሚያበጁ ተከታታይና ቋሚ ገጽታዎች መሆናቸዉን እንረዳለን፡፡ እነዚህ ገጽታዎች በየልብወለዶቹ ዉስጥ ተከታታይነትና ወጥነት ያላቸዉን ፍቺዎች ከማስገኘት በተጨማሪ የየልቦለዶቹን መታገቢያ ሰብረዉ የሚወጡ፣ ድርሰቶቹ ከበቀሉበት ዘመንና ስፍራ ጋር የሚናበቡ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ርእዮተ ዓለማዊ አንደምታዎችን መፍጠራቸዉን አጥኝዉ ያስረዳል፡፡ ልቦለዶቹ በጥቅሉ ነገ ከፍርሃት፣ ከስጋትና ከጭንቀት ጋር ተዛምዶ፣ ተቀይጦ የቀረበባቸዉ ስራዎች መሆናቸዉንም እንድሁ (ቴዎድሮስ፣2001፣ 249)፡፡ የቴዎድሮስ ጥናት በንድፈ ሀሳብ ምርጫ ቢመሳሰልም ይዞት በተነሳው ዓላማ፣ በማናበቢያ ፅንሰ-

ሃሳብ፣ በሚተነተኑ ጭብጦች ከዚህ ጥናት ልዩነት አለው፡፡ ይሁን እንጂ እንደ አጥኝው ሂሳዊ ዳሰሳ የቴዎድሮስ ጥናት በጣም ጥሩ ሒደቶችን የተከተለ ነው፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ከእኔ ጥናት ጋር ቀረቤታ ያለዉ የንጉስ መለሰ "የህልውናዊነት ጭብጦች ትንተና በትዝታሽ ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ" ረጅም ልቦለድ በሚል ርዕስ ሰኔ 2013 ዓ.ም በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበዉ ጥናት ነዉ፡፡

የጥናቱ ዋና ዓላማ አላማም በትዝታሽን ለኔ ትዝታዬን ላንቺ ረጅም ልቦለድ የተገለፁ ዋና ዋና የነገረ ህላዌ ጭብጦችን በመዘርዘር መተንተን ነዉ፡፡ የድርሰት ስራ የተገለፀዉ ታሪክ የነገረ ህላዌ ታሪክ መሆኑን ፈክሮ ማሳየት ነዉ፡፡

ይህን ዓላማ ለማሳካትም ምርጫ፣ ትርጉምን መፈለግ፣ ብቸኝነት፣ ተፅዕኖ፣ ኢ-ምክንያታዊነትና ባዶነት የተሰኙ የነገረ ህላዌ ጭብጦች ነገረ ህላዌ ንድፈ ሀሳብን መሰረት በማድረግ በትንተና ተካተዋል፡፡ ይህ ጥናት ትኩረቱን ያሳረፈውም በእሱባለው አበራ በትዝታሽን ለኔ ትዝታዬን ላንቺ ረጅም ልቦለድ በመፈተሽ በቴክስቱ የበቀለ የነገረ ህላዌ ጭብጦችን በማገናዘብ ድርሰቱ ውስጥ የተነሱት ታሪኮች የነገረ ህላዌ ታሪኮች መሆናቸውን ማሳየት ላይይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ የጥናቱን ዘዴ በተመለከተ ደግሞ ጥናቱ ስነጽሑፋዊ በመሆኑ አይነታዊ ምርምር ዘዴ መሰረት በማድረግ በጥልቅ ንባብ ትንተና ላይ ያተኮረ ነዉ፡፡ የመለሰ ጥናት በንድፈ ሀሳብ ምርጫ ቢመሳሰልም ይዞት በተነሳው ዓላማ፣ በማናበቢያ ፅንሰ-ሃሳብ፣ በሚተነተኑ ጭብጦች ከዚህ ጥናት ልዩነት አለው፡፡

በአራተኛና የመጨረሻ ጥናት ደግሞ በአንለይ ወንዲራድ (2012) "ሥነ ልቡናዊ ሞት በበውቀቱ ስዩም በእንቅልፍ እና እድሜ" በሚል ርዕስ በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበዉ ጥናት ነዉ፡፡

የጥናቱ አቢይ ዓላማም በበእውቀቱ ስዩም እንቅልፍ እና እድሜ ውስጥ ሥነ ልቡናዊ ሞት ከሰው ልጅ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ርዕዮተ ዓለማዊ ጉዳዮች ጋር ያለውን ግንኙነት ማሳየት ነው፡፡

በበእውቀቱ ስዩም እንቅልፍና እድሜ የተሰኙ ስራዎችን በመውስድ በቴክስቶቹ ስነ ልቦናዊ የሞት ጭብጦችን ማለትም ፍርሃት፣ ጭንቀት፣ ቀቢጸ ተስፋና ለራስ የሚሰጥ ዝቅተኛ ግምት አንፃር ለመተንተን ሞክሯል፡፡ ጥናቱ ማያነት የተመረጠው ደግሞ የሲግመንድ ፍሮይድ ፍካሬ

ልቦና (Psychoanalysis) ሲሆን ለትንተና የተመረጠው ዘዴ ፍካሬ ልቡናዊ ንባብን ተጠቅሞ የሃቲት ትንተና ማድረግ ነው፡፡

የአንለይ ጥናት ሞት የሚለውን ቃል መጠቀሙ ቢያመሳስለውም ይዞት በተነሳው ዓላማ፣ በንድፈ ሀሳብ ምርጫ፣ በማናበቢያ ፅንሰ-ሃሳብ፣ በሚተነተኑ ጭብጦች ከእኔ ጥናት ጋር ልዩነት አለው፡፡

በአጠቃላይ የቀደምት ጥናቶችን በምዳስስበት ጊዜ ለዚህ ጥናት የጭብጥ መረጣ፣ አተናተን እና ሌሎችም አጋዥ የሆኑ እውቀቶችን አግኝቼባቸዋለሁ፡፡ ስለሆነም በቀደምት ጥናት ዳሰሳዬ “ሞት” ከነገረ ህላዌ አንጻር በወጉ ያልተብራራ ሆኖ ስላገኘሁት፣ የጥናት ክፍተትን መሙላት በሚል ሃሳብ “ሞት በቅበላ ረጅም ልቦለድ ውስጥ፣ ከነገረ ህላዌ” በሚል ርዕስ የተቀነበበ ጥናት ነው፡፡

## 2.2. ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ

በንድፈ ሃሳባዊ ዳራዉ የሚዳሰሱት የነገረ ህላዌ ምንነት፣ የነገረ ህላዌ ፍልስፍና ታሪካዊ እድገትና የነገረ ህላዌ ጭብጦች መካከል አንዱ የሆነው ሞት ምንነት ይብራራበታል፡፡

### 2.1.1 ነገረ ህላዌ (Existentialism)

ነገረ ህላዌ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በኋላ በተለይ በጀርመን እና በፈረንሳይ ከፍተኛ ተጽእኖ መፍጠር የቻለ ፍልስፍና እና ፍልስፍናዊ አመለካከት ነው:: በማንኛውም ሁኔታ የተለያዩ እሳቤዎች ወይም ፈላስፋዎች እርስ በእርሱ የሚጣረስ እና የተሰባጠረ እይታ ያላቸው በመሆኑ ለነገረ ህላዌ ራሱን  የቻለ ቁርጥ ያለ ትርጓሜ መስጠት አስቸጋሪነው፡፡ አሜሪካን የእንግሊዘኛ ቋንቋ መዝገበ ቃላት(2004) ነገረ ህላዌን እንዲህ በማለት ይተረጉማል፡-

> A philosophy that emphasizes the uniqueness and isolation of the individual experience in ahostile or indifferent universe, regards human existence as unexplainable, and stresses freedom of choice and responsibility for the consequences of one 's act.

እያንዳንዱ ሰው በዚህች አለም ላይ ሲኖር ከሌላ ሰው የሚለየው ልዩ የሆኑ ባህሪያትን እንዲሁም አስቸጋሪ ወይም የማይመች ዩንቨርስ ውስጥ እያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ የሚያሳልፈው ለሱ ብቻ የተሰጠ ልምድ ላይ የሚያተኩር እና የሰዎች ህልውና በአንድ ቃል እንዲህ ነው ተብሎ ሊብራራ የማይችል መሆኑን የሚገልጽ እንዲሁም የሰዎች ምርጫ፣ ነጻነት እና አንድ ሰው በሚሰራዉ

ድርጊት የሚያጣው ውጤትን የመቀበል ሀላፊነት ላይ አጽንኦት የሚሰጥ የፍልስፍና መስክ ነው፡፡

ራቪ (2011፣185) እንደገለጹት፣ ነገረ ህላዌ ህልውናው በተራቀቀው የሳይንስ እና የቴክኖሎጂ ህብረተሰብ ውስጥ የጠፋውን የሰው ልጅ ሁኔታ እንደገና የማረጋገጫ እና መልሶ የማግኘት ፍልስፍና ነው፡፡ ስለሆነም ይህ እያንዳንዱ ሰው ስለሕልውናው እንዲያስብ የሚጠይቅ የግለሰብ ትርጉም ንድፈሀሳብ ነው፡፡

“Existentialism is a philosophy of reaffirming and regaining the lost status of man in the advanced scientific and technological society. Therefore, this is a theory of individual meaning which asks each mantoponder over there a son for his existence.”

የፍልስፍናው አራማጆች እና አቀንቃኞች እንዲሁም የሥነጽሁፍ ንቅናቄ እንዲሆን ስፊ መሰረት የጣለ ሊሂቃን እንደሚገልጹት የፍልስፍናው (የንድፈሃሳቡ) ዋና ትኩረት የሰው ልጅ ህልውና ነው፡፡ “ነገረ ህላዌ በሰው ልጆች ሁለንተናዊ ህይወት ላይ መሰረት ያደረገ የህልውና ፍልስፍና ነው” የሚለውን ብያኔ አብዛኞቹ ልሂቃን የሚጋሩት እና የሚያራምዱት ሃሳብ ነው፡፡

> ፍልስፍናው በሕልውና ላይ አፅንዖት የሚሰጥ ነው (ማንኛውንም ዓይነት ረቂቅ እና ግለሰባዊ ያልሆነ ትርጉም እና የሰው ሕይወት ፅንሰ-ሀሳቦችን በመቃወም) […] ሕልውና የሚያመለክተው ከጋራ ሕልውና ይልቅ የግል (የግለሰባዊ) መኖርን ነው፡፡” (Robert Solomon፣ 2003፣175-176)
>
> The philosophy puts the emphasis on existence (in opposition to any number of abstract and impersonal conceptions of meaning and human life) […] existence refers to personal, individual existence rather than collective existence”. (Robert Solomon 2003, 175-176)፣

ቴዎድሮ(2001፣ 143) የነገረ ህላዌ ፍልስፍናን አስመልክቶ የሚሰነዘሩ ሃሳቦች የተለያዩ ነገር ግን የማይራራቁ መሆናቸውን ገልፆ፣ በዚህ ፍልስፍናዊ እሳቤ ላይ የተሰማሩ ፈላስፋዎችን እና የሚሰነዝሯቸውን የብያኔ ሃሳቦች ተመሳስሎ ያመለክታል ያላቸውን ሦስት ዓበይት ጉዳዮችን ያስቀምጣል፡፡ በዚህ መሠረት የመጀመሪያው፣ የሁሉም የነገረ ህላዌ ፈላስፋዎች ማዕከላዊ ጉዳይ የሰው ልጅ መሆኑ ሲሆን፣ በሁለተኛነት የሚያስቀምጠው ደግሞ በሁለተኛው

የዓለም ጦርነት ሳቢያ ሰዎች ላጧቸው የጋራ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ እሴቶች ምላሽ በሚሆኑ ጉዳዮች እና የወደፊት ዕጣፈንታን በመተንበይ ላይ ማተኮራቸው እንደሆነ ያብራራል፡፡ ይኸውም አብዛኛዎቹ የዘርፉ ታላላቅ እና ተጽዕኖ ፈጣሪ ፈላስፋዎች እና ጸሀፊያን ብቅ ያሉት የሁለተኛውን የዓለም ጦርነት ተከትለው መሆኑ እና በወቅቱ በሥራዎቻቸው ያስተጋቧቸው የነበሩ መልዕክቶችም የጦርነቱን ክስተቶች እንደነበሩ፣ ሌላው እና ሦስተኛው ደግሞ፣ የአብዛኛዎቹ ፈላስፋዎች የጭብጥ ምርጫ መመሳሰሉ መሆኑን አጽንኦት ሰጥቶ ይገልፃል፡፡

Mallah (2016፣2) ደግሞ "ነገረ ህላዌ በግለሰቦች ትክክለኛ ህልውና ላይ ትኩረት በማድረግ የግለሰብዓዊነትን ኃያልነት የሚያቀነቅን ብቸኛ ፍልስፍና ነው፡፡ ምናልባትም ነገረህላዌ በግለሰቦች አጠቃላይ ህልውና ላይ በማነጣጠር እና ግለሰብዓዊነትን ዋና ጉዳዩ በማድረግ የሚካሄድ የፍልስፍና ዘርፍ በመሆኑም የትክክለኛ ሰውነት ፍልስፍና ተብሎም ሊጠራ ይችላል" ሲሉ ምልከታውን ያስቀምጣል፡፡

> Existentialism is the only philosophy which considers individuality as supreme…ingeneral terms existentialism may be described as an attempt to reach the inmost core of human existence in a concrete and individual fashion. Therefore it is called a philosophy ofa concrete man. (Mallah, 2016, 2)

ጠቅለል ባለ ሁኔታ የነገረህላዌ ፍልስፍና ስንመለከተው አብዛኞቹ ሊሂቃንም እንደሚስማሙበት ነገረህላዌ በሰው ልጆች ላይ ብቻ በተለይም በግለሰብ ህልውና ላይ በመወሰን የህይዎትን ሁለንተናዊ ጉዳዮች የሚገልጽ ፍልስፍና ነው ማለት ይቻላል፡፡

ነገረ ህላዌ በሰው ልጅ የህልውና ምርምር ላይ ልዩ ትኩረት ያደረገ እና ሰዎች በቁሳዊው ዓለም ወይም ተፈጥሯዊ ዓለም ላይ ሲኖሩ ራሳቸውን ለማግኘት እና ከፍ ሲልም ህይወታቸውን የተደላደለ ለማድረግ የሚያልፉባቸውን የህልውና መንገዶች የሚመረምር እና የሚያጠና የ20ኛው ክፍለ ዘመን የፍልስፍና ማዕቀፍ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ስለዚህ ነገረህላዌ በዚህ ውስብስብ እና ውጣውረድ በበዛበት ቁሳዊ ዓለም ውስጥ ራስን የመፈለግ እና የማግኘት ወይም የህይወትን ትርጉም የመረዳት ፍልስፍና ነው ተብሎም ሊገለጽ ይችላል፡፡

በዚህ የፍልስፍና መስክ አተያይ እና እምነት ሁሉም የሰው ልጆች በዓለም ላይ ሲኖሩ ከየትኛውም አይነት ማህበራዊ ሥርዓት፣ ህግ እና ደንብ ተጽዕኖ (አስገዳጅነት) ነጻ መሆን እንዳለባቸው ያምናል፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱ የሰው ልጅ በሚፈለገው ሥርዓት ሙሉ ማንነቱን የመፍጠርና የመገንባት ስልጣኑ የራሱ ለግለሰቡ ብቻ የተተወ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ የሰው ልጅ ራሱን በራሱ በመፍጠር ሂደት መካከል የትኛውም አይነት ቅድመ ሁኔታ ሊገድበውም ሆነ ጣልቃ ሊገባበት ፈጽሞ አይገባም የሚል ፍልስፍናዊ እሳቤ ነው ብንለውም የሚያስሄደን ነው፡፡

እንደ ነገረህላዊያን እምነት የሰው ልጆች ንቃተ-ህሊና (Consciousness) ፣ ስሜታዊነት (Sentient) ያላቸው እና ራሳቸውንም የሚፈጥሩ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ እያንዳንዱ የሰው ልጅ በተፈጥሮው ከሌሎች የተፈጥሮ አካላት በተለየ መልኩ አዕምሮውን የመጠቀም አቅሙ እና ችሎታው አንዱ ግለሰብ ከአንዱ ይለይ እንጅ የማሰቢያ እና የማገናዘቢያ ክህሎት ያለው፣ ፈጣሪ፣ አሰላሳይ እና መርማሪ ነው፡፡ ይህ የሰው ልጅ ብቻ የተቸረው መክሊቱ ነው፡፡ ሌሎች የተፈጥሮ አካላት የማይለወጥ ማንነት ያላቸው ከመሆናቸውም በላይ ማድረግ የሚፈልጉትንም ይሁን የሚከውኑትን ማንኛውንም አይነት ድርጊት የመምረጥ ነጻነት እና የራሳቸውን ዓለም ራሳቸው የመፍጠር ችሎታም ሆነ አቅም የላቸውም፡፡

ስለዚህ ለነገረህላዊያን (Existentialists) ለእነዚህ ሁሉ ጸጋዎች ብቸኛው ባለቤት የሰው ልጅ ነው የሚል ፅኑ እምነት እናዳለቸው መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ የተነሳ ይህ የነገረ ህላዌ ፍልስፍና የግለሰቦችን ነጻነት እና ምርጫ አስፈላጊነት አጉልቶ በማሳየት ለእያንዳንዱ ህልውና፣ ነጻነት እና ምርጫ መከበር ዘብ የሚቆም ነው ብንለው ያስሄደናል፡፡ በመጨረሻም እንደነገረ ህላዌ የፍልስፍና እሳቤ እያንዳንዱ ግለሰብ በህይወቱ ውስጥ የራሱን እድል ራሱ የመወሰን እና የማራመድ እንደዚሁም የህይወት ጎዳናውን በራሱ አቅጣጫ የመቀየስና የመምራት አቅምም ሆነ ስልጣን አለው፡፡

በርካቶች እንደሚስማሙት የዘመናዊዉ የነገረህላዊ ፍልስፍና የተመጀረው የጀርመን ፈላስፋ የሆነው ሄግል (Hegel) ፍጹማዊ አይዳሊዝም ፍልስፍና ላይ በተጀመረው ትችት መሰረት ነው፡፡ ነገርግን ሊቃውንት በዚህ ክርክር ረገድ ልዩነት ያሳያሉ፡፡ አንዳንዶች የነገረ ህላዌ ቀደምት መስራች (ቅዱስ ቶማስ አኳይናንስ፣ 1525-1574) እንደሆነ እና ይህም ፈላስፋ ፍልስፍናዊ አስተሳሰቡ የህልውና እና የአይዲያሊዝም ፍልስፍና እንደሆነ ያያሉ ሬናርት (Reinhardt,1952, p.228)፡፡ ሌሎች ነገረ ህላዌ የተጀመረው በብሌይዝ ፓስካል (Blaise Pascal,1623-1662)

እንደሆነ የሚናገሩ ሲሆን ይህ ፈላስፋ "የሰው ልጅ ማለት በአእምሮ እና በቁሳዊ ሰውነቱ መካከል እርስ በእርስ የሚጋጭ ፍጥረት ነው።" የሚል አስተሳሰብን ያራምዳል። ድሬፈስ እናራስሆል (Dreffus and Wrathall, 2006,3)፤

ነገር ግን የነገረ ህላዌ ፍልስፍና ቃሉ ራሱ ዋጋ ኖሮት በሰፊው ጥቅም ላይ መዋል የቻለው ከፈረንሳዩ አሰላሳይ፣ ልቦለድ ደራሲ እና ጸሀፊ ተውኔት ዣንፖል ሳርተር በኋላ ነው። በተጨማሪም ሊቃውንት ይህን ፍልስፍና ያገነነው እና ታዋቂ ያደረገው ሳርተር "ነገረ ህላዌ ማለት ሰው መሆን ማለት ነው።" የሚለውን ትምህርቱን በክለብ ሜንትና በፓሪስ በኦክቶብር 29/1995 ባቀረበበት ወቅት ነው። በዚህ ትምህርታዊ ገለጻ ወቅት ላይ በነገረ ህላዌ የተሰነዘሩ ተቃርኖዎችን የተቀላቀለበት ገለጻ ቀርቧል ( kaufman፣ 1989) ።

ያም ሆኖ የዳኒሽ አሰላሳዩ ሶረን ኬርክጋርድ (1813-1855) የነገረ ህላዌ አባት ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ይህ አሰላሳይ የሄግል ያአይዲያሊዝምን ሙሉ ለሙሉ ውድቅ አድርጓል። እንደዚህ አሰላሳይ ከሆነ "እውነት እንደ ሁኔታዎች ተለዋዋጭ የሆነች እና እያንዳንዱ ሰውም ከዩኒቨርስ በላይነው። እንዲሁም ዘላለማዊነት ሊኖር የሚችለው ጊዜ የሚባለው ነገር ሲኖር ብቻ ነው።" ከኪየርክጋርድ በኋላ ብዙ አሰላሳዮች እና ደራሲዎች በየራሳቸው የፍልስፍና እይታ ዋናዋና የነገረ ህላዌ አራማጆች ተብለው ተፈረጅዋል። ከእነዚህ መካከል ፈረንሳዩ አሰላሳይ ዣን-ፖል ሳርተር (Jean-paul Sartre) ፣አልበርት ካሙ (Albert Camus)፣ ሲሞን ደ ቦቯ (Simone de Beauvoir)፣ ገብሬል ማርሴል (Gabriel Marcel) እንዲሁም የጀርመን ፈላስፋዎች ፍሬድሪች ኒቼ(Friedrich Nietzsche )፣ ካር ጃስፐር እና ማርቲን ሄዲገር( Karl Jaspers and Martin Heidegger )እንዲሁም የነገረ ህላዌ ጸሀፊ የሆኑት ፊዮዶር ዶስቶቭስኪ(Fyodor Dostoevsky)፣ ፍራንዝ ካፍካ(Franz Kafka )እና ሳሙኤል ቤኬት(Samuel Beckett) ይገኙበታል።

ጀርመናዊ ፈላስፋ ኤድመንድ ሀሰር (Edmund Husserl) የዚህ ንቅናቄ መስራች እንደሆነ ይነገራል። እንደ ክላውድ ሰምነር (Semner፣ 1974፣ 244) ከሆነ "ፌኔሜኖሎጂ ማለት አንድ ገላጭ ለሆነ ትንተና እና ትርጓሜ ማለትም አንድ ንቃተ ሂሊናን የተላበሰ ህይወትን፣ በህይወት የመኖር ሂደትን ፣አመለካከትን ፣ይዘት እና ቁስ የሚተነተንበት እና የሚተረጎምበት የፍልስፍና ንቅናቄ ነው።"

ከዚህ በተጨማሪም የነገረ ህላዌ ተጽእኖ ከፍልስፍና በዘለለ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እውን በሆኑ የባህል ንቅናቄዎች ውስጥ ማለትም ስነጽሁፍ፣ ቲያትር፣ ሙዚቃ፣ ፊልም፣ ስነመለኮት እና

የስነልቦና ትንተና ላይ በሰፊው ተንጸባርቋል፡፡ የዚህ ፍልስፍና ዋናዋና አረማጆች በእነዚህ ባህል ነክ እንቅስቃሴዎች ተሳታፊ የነበሩ ናቸው፡፡ እንዲያውም Honderich (1995) እንደገለጸዉ ከሆነ እንደ ሳርተር ያለ የነገረ ህላዌ አራማጅ፣ ዋና ጸሀፊተውኔት፣ ልቦለድ ደራሲ፣ የፖለቲካ ጽንሰ ሃሳባዊ አራማጅ እንዲሁም የስነጽሁፍ ሂሰኛ የለም፡፡

እዚህ ጋር መነሳት ያለበት ሌላው ነጥብ በነገረ ህላዌ አራማጆች መካከል እጅግ የተለያዩ እርስ በእርሳቸው የሚጠራሱ እይታዎች መኖራቸውን ማየት ነው፡፡ ለምሳሌ ሄድገር እና ሳርተርን ብንወስድ ሆንድሪች (1995፣ 261) የሚከተለውን ብሏል፤

> Heidegger's existentialism is essentially metaphysical. He even denies that the authentic - inauthentic distiniction has any ethical content, although his actual language betrays him here. Sartre, by contrast, explicitly presents existentialism as an ethical doctrine. He largely takes his existentialist starting point from Heidegger, except that where Heidegger clearly separets human existence from the exercise of choice, Sartre reformulates the position as one in which the role of choice in human life is absolutely fundamental.

> የሄድገር ኤግዚዝቴንሻልዝም አቋም በዋነኛነት ሜታፊሲካል ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ ትክክለኛ የሆነ ትክክለኛ ያልሆነ ተብሎ የተቀመጠው የሰውልጅ አገላለጽ ባህሪ ስነ-ምግባራዊ ይዘት የሌለው እንደሆነ አስረግጦ ይናገራል፡፡ በተቃራኒው ሳርተር እንደሚለው ከሆነ ነገረ ህላዌ የሚያቀርበው በግልጽ የስነምግባር ቀኖና በማድረግ ነው፡፡በከፍተኛ ደረጃ ይህንን የነገረ ህላዌ መነሻ ነጥብ ከሄድገር የሚወስድ ሲሆን ነገርግን ከሄድገር የሚለየው ሄድገር የሰውልጅ ህልውናን ከሰውልጅ ምርጫ ለይቶ ማየቱ ሲሆን ሳርተር በበኩሉ የሰውልጅ ህይወት በነገረ ህላዌ አራማጆች መካከል ልዩነት ቢኖርም አንድ የሚያደርጋቸው ተመሳሳይነቶች አሏቸው፡፡ከእነዚህ መካከል ሁሉም የነገረ ህላዌ አሰላሳዮች የፍልስፍናቸው ማዕከል ያደረጉት ሰውን ሲሆን በስራቸው ውስጥ አለም ትርጉም አልባ በመሆንዋ እያንዳንዱ ሰው ህይወት ስሜት እንድትሰጠው የራሱን ጥረት ማድረግ አለበት ይላሉ፡፡

### 2.2.2. የነገረ ህላዌ ፍልስፍና ታሪካዊ እድገት

ስለ ነገረ ህላዌ ፍልስፍና ወጥ የሆነ ታሪካዊ ዳራ ማስቀመጥ በእጅጉ አስቸጋሪ ቢሆንም ልክ እንደትረጓሜው ሁሉ ስለታሪካዊ እድገቱም የሚሰነዘሩት ሃሳቦች ልዩነቶች ቢኖሩም ቅሉ ተወራራሽ እንደሆኑ በዘርፉ ላይ ምርምር ያደረጉ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

Flynn (2006፣ ix) የነገረ ህላዌ ፍልስፍናን እድሜ በሚመለከት የሚከተለውን ሀሳብ ሰንዝሯል፡፡

> የነገረ ህላዌ ፍልስፍና፣ አንደኛውን እና ሁለተኛውን የዓለም ጦርነት ክስተቶች ተከትሎ ብቅ ያለ ቢመስልም የፍልስፍና ጉዳዮችን በማራመድ እና የሰው ልጆችን ህይወት በማንጸባረቅ ረገድ የራሱን የፍልስፍናውን ያህል እድሜ ያስቆጠረ ጉዳይ ነው፡፡
>
> If it bears the mark sofits post-war apearance, existentialism as a manner of doing philosophy and away of addressing the issues that matterin people's lives isat least as old as a philosophy itself" (Flynn, 2006, ix)

ስለዚህ የነገረ ህላዌ ፍልስፍና ከ20ኛው ክፍለ ዘመን የሥነጽሁፍ ንድፈ ሃሳብነትም የራቀ እና ቀደምትነት ያለው የፍልስፍና ዘርፍ እንደነበረ ይኸው የFlynn ሃሳብ አይነተኛ ማስረጃ ነው፡፡

ይህ ፍልስፍና ምንም እንኳን በ20ኛው ክፍለ ዘመን "ነገረ ህላዌ"(existentialism) የሚል ስያሜ አግኝቶ በአዲስ መንገድ በስፋት ቢቀነቀንም፤ ይህ የህልውና ፍልስፍና ፅንሰ ሃሳብ ከ469 እስከ 399 ቅድመ ልደት ክርስቶስ ጀምሮ በዘመኑ ታላላቅ ፈላስፎች፣ ትንቢተኞች (Seers) እና ቅዱሳን(Saints) በእነSocrates እና Plato አማካኝነት እንደፈለቀ ብሎም በተለያዩ ሥራዎች ሲንጸባረቅ የቆየ ስለመሆኑ Azhar(2013፤30) በጥናት ምርምሩ ውስጥ ምስክርነቱን አስቀምጧል፡፡ በዘመኑም በመጀመሪያ ጊዜ የሰው ልጅ እንደ ትክክለኛ የእውቀት እና የምርምር ባለቤት ተደርጎ የታየበት ወቅት ሲሆን፣ በተለይም Socrates፣ የሰው ልጅ ለውጤታማ እና ትክክለኛ አለማዊ ኑባሬ የራስ ምርምር እና እውቀት(self-enquiryand self-knowledge) ሊኖረው ግድ ነው የሚል እምነት የነበረው ታላቅ ፈላስፋ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ

የSocrates ተከታይ የሆነው Plato በርካታ የነገረ ህላዌ ፍሬ ሃሳቦችን ያሰላሰለ እና ህልውናዊ የሆኑ ቃላትን በንግግሩ ውስጥ ይጠቀም የነበረ ሌላው ታዋቂ ፈላስፋ ነው፡፡ ከነSocrates እና Plato በተጨማሪ ደግሞ St. Augustine በተናጠላዊ ህልውና ላይ በማተኮር የሰዎችን ውድቀት፣ ከሃይማኖት መውጣት(spiritualwithdrawal) እና የተለያዩ ህልውናዊ እንቅስቃሴዎችን ያራምድ የነበረ  ቀደምት ፈላስፋ  መሆኑን በመግለጽ በ20ኛው ክ/ዘመን እንደ አዲስ ብቅ ባሉት በMarcel እና በSartre  የነገረ ህላዌ እሳቤ ውስጥ የAugustine ፅንሰ ሃሳብ በግልጽ እንደሚስተዋል (Azhar፣ 2013፣ 29-30) ያስረዳል፡፡

Stefan Bolea (2018፣ 70-71) ደግሞ የነገረ ህላዌን ታሪክ በሦስት ዋና ዋና ምዕራፎች ከፋፍሎታል፡፡ በዚህ መሰረት የመጀመሪያው የነገረ ህላዌ እንቅስቃሴ በ1840ዎቹ አካባቢ ታላላቅ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሥራዎችን በዴንማርክ ባበረከተው ምሁር ሶረን ኬርክጋርድ (Soren Kierkegaard) ተወክሏል፡፡

የሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ በዋናነት በ1880 እና በ1940 መካከል በነበሩት የተለያዩ ሥራዎቻቸው አማካኝነት የጀርመን ሀሳባውያንን የሚመለከት ሲሆን ከእነዚህ መካከል ፍሬደሪክ ኒቼ (Friedrich Nietzsche)፣ ማርቲንሄዴገር (Martin Heidegger)፣ ካርሌጃስፐርስ (Karl Jaspers) እና ኤድመንድ ሃሰርሌ (Edmund Husserl) ይገኙበታል፡፡

ሦስተኛው እና የመጨረሻው ምዕራፍ ደግሞ ነገረ ህላዌ የተሻለ እውቅናን ያተረፈባቸውን ዘመናት የሚመለከት ሲሆን፣ ይኸውም በ1930 እና በ1970 መካከል ባሉት ጊዜያት ውስጥ በፈረንሳያውያን ፈላስፋዎች አማካኝነት የላቀ የፍልስፍና ዝንባሌ እና ታላቅ እምርታ እያሳየ የመጣበትን ወቅት ያጠቃላል፡፡ ከወቅቱ ዋና ዋና ፈላስፋዎች መካከል ደግሞ አልበርት ካሙ (Albert Camus)፣ ሲሞን ዳ ቤቮር (Simone deBeauvoir)፣ ማውሪስ ሜርሎዩፖንቲ (Maurice Merleau-Ponty)፣ ጋብሬል ማርሴል (Gabriel Marcel)፣ እና በተለይ ደግሞ ላቅ ያለ ቦታ የሚሰጠው ዣን ፖሌሳርተር (Jean-paulSartre) ግንባር ቀደም ተጠቃሾች ናቸው፡፡

"ነገረህላዌ ታላቁ የሰውን ልጅ ያህል የእድሜ ዘመን ያለው እሳቤ እና በፍልስፍናው፣ በጥበባቱ፣ እንዲሁም በሥነጽሁፍ ዘርፍ የተንጸባረቀ የአስተሳሰብ ዘይቤ ነው" (Mobini እና Salim pour፣ 2016፣ 7)

"Existentialism is a method of thought in philosophy, art, and literature that is as

old as the oldest human’s thoughts” (Mobini and Salim pour, 2016, 7).

እንደ Mobini እና Salim pour (2016፣ 87) ገለፃ፣ የ20ኛው ክ/ዘመን የህልውናዊነት ጽንሰ ሃሳብ እንደ አዲስ የፍልስፍና የትምህርት መስክ ይተዋወቅ እንጅ ታሪካዊ ስሩ ግን ከረጅም ጊዜ በፊት ሲመረመር እና ሲጠና የቆየ ፍልስፍናዊ እሳቤ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የነገረ ህላዌ ፍልስፍናን ጽንሰሃሳብ የሚያሳዩ የተለያዩ ጉዳዮች መንጸባረቅ ከጀመረ ረጅም ዘመንን ያስቆጠሩ ብቻም ሳይሆን የራሱን የሰውን ልጅ ህልውና ያህል ረጅም እድሜም ያስቆጠረ ነው፡፡

“The existential philosophy in the 20th century was introduced as school of philosophy but its historic roots could be searched in a long time ago because the discussed issues in the existentialism philosophy areas oldas human existence.”

Michelman (2008) ደግሞ፣ ዋናው እና ትክክለኛው የህልውናዊነት ፍልስፍና ምዕራፍ ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በኋላ በ1920ዎቹ እና በ1930ዎቹ ከጀርመን እንደመጣ እንዲሁም በወቅቱ ይህ የፍልስፍና ዘርፍ እንዲያቆጠቁጥ እና እንዲያንሰራራ ያደረጉት ደግሞ Karl Jaspers እና Martin Heidegger እንደሆኑ ይሞግታል፡፡ Michelman በሁለተኛው ምዕራፍ ይህ ፍልስፍና በ1930ዎቹ እና በ1940ዎቹ በጀርመናዊው ፈላስፋ በFriedrich Nietzsche እና በዴንማርካዊው Soren Kierkegaard ትኩረት እያገኘ መምጣቱን ይገለጣል፡፡ በዚህ በሁለተኛው ምዕራፍ ዋና ግንባር ቀደም ተጠቃሽ የሆነው ደግሞ ፈረንሳያዊው ፀሀፊ እና ፈላስፋ Jean-Paul Sartre ነበር ይላል፡፡ ከዚህ አኳያም ከእነFlynn እና Wolcott በተቃራኒ ይቆማል፡፡ በተጨማሪም ከ1945 ጀምሮ አዲስ መስመር እና ዘመናዊ መልክ እንዲይዙ በማድረግ ረገድ ከሌሎቹ ማለትም ከSimonede Beauvoir እና Maurice Merleau-Ponty ጋር በመሆን የነገረ ህላዌ ምሁራንን እንቅስቃሴ በዋና ተዋናይነት መራ እንጅ ነገረ ህላዌ ሙሉ በሙሉ የSartre ፍልስፍና ነው ሊባል አይችልም ሲል የSartreን የነገረ ህላዌ ፍልስፍና አፍላቂነት የሚያቀነቅኑ ወገኖችን ሞግቷል፡፡

የነገረ ህላዌ ፍልስፍና ወደ ሥነጽሁፍ ንድፈ ሃሳብነት (Literary theory) እና ማህበራዊ የትችት አንጻርነት (social criticism) መስክ በመምጣት ተጽዕኖ መፍጠር የጀመረው ደግሞ በ1930ዎቹ እና በ1940ዎቹ ገደማ በHeidegger አማካኝነት ነው በማለት Hubert L.drefus

እና Mark A.Wrathall (2006) የMichelmanን ሀሳብ ይጋራል።

ወደ 19ኛው እና 20ኛው ክፍለ ዘመን ስንመጣ Wolcott H.F (1992) ፣ ለነገረ ህላዌ ፍልስፍና በአዲስ መልክ ብቅ ማለት የSartreን ሥራዎች እንደምክንያት በማስቀመጥ ይህንን ወቅት ዘርፉ መሻሻል ያሳየበት እና ከፍተኛ ተቀባይነትንም ያገኘበት ጊዜ እንደሆነ ያብራራል። በተመሳሳይ፣ይህ ዘመናዊ የነገር ህላዌ ፍልስፍና ምንጭ ከወደፈረንሳይ ፓሪስ ከ2ኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ አካባቢ በዣንፖል ሳርተር (Jean-paul Sartre) እና ሲሞን ዳ ቤቮር (Simone de Beauvoir) አማካኝነት እንደፈለቀ (Flynn፣ 2006) ያስረዳል።

Azhar (2013) ደግሞ፣ ለ20ኛው ክ/ዘመን የነገረ ህላዌ ፍልስፍና የፈርቀዳጅነት ሚናን ለGabriel Marcel እና ለJean-Paul Sartre ያወርሳቸዋል። ከዚህ ባለፈ ግን ከላይ ካስቀመጧቸው ግንባር ቀደም የፍልስፍና አባቶች በኋላ በተለይ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ እና በ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ አካባቢ ራሳቸውን እንደነገረ ህላዌ ፈላስፋ ይቆጥሩ የነበሩ በርካታ ዘመናዊ ፈላስፋዎች እና ፀሀፊያን በዚሁ የህልውና ፍልስፍና ላይ የየራሳቸውን ትላላቅ አሻራ ጥለው እንዳለፉ ያትታል። ከእነዚህ መካከል ደግሞ የFyodor Dostoevsky 'Notes from under ground" በዚህ የነገረ ህላዌ ፅንሰ ሃሳብ ላይ የተመሰረተ ፋና ወጊ የሥነጽሁፍ ሥራ ነው። Dostoevsky በሥራዎቹ ውስጥ የሰዎችን ግለሰባዊ አመለካከት (subjectivity) እና ነጻነት በጥልቀት መርምሮ ያሳየ ዘመናዊ ፀሀፊ እንደሆነም (Peterfreund እና Deniseን 1967፣ 192-193) ዋቢ አድርጎ ይገልጻል። (Azhar፣ 2013፣ 31)

ይሁን እንጅ በዋናነት አዲስ መልክ ይዞ ብቅ ያለው ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በኋላ ሲሆን፣ ታልቅ እምርታ ያሳየው እና ተፅዕኖ መፍጠር የጀመረው ደግሞ የሁለተኛውን የዓለም ጦርነት ተከትሎ ነው። በወቅቱ በእነዚህ ታላላቅ ጦርነቶች ምክንያት እጅግ አስከፊ የሆኑ ክስተቶች በሰው ልጅ ህልውና ላይ እርግጠኛ አለመሆን፣ ጭንቀት፣ ድብርት፣ የኢኮኖሚ ድቀት እና ግራ መጋባት ከባድ የሆነ ምስቅልቅል እና ስቃይን በሰው ልጆች ላይ ማስከተሉ ይታወቃል። በመሆኑም ሁለቱ ጦርነቶች በሰው እና በእግዚአብሔር ላይ ያሉትን ሁሉንም ተስፋዎች እና በራስ መተማመን (ትምክህቶችን) እንዳይፈርሱ ይታመናል።

የ20ኛው ክፍለ ዘመን የነገረ ህላዌ ፍልስፍና (Existentialism) የተቃውሞ ድምጽ እና ነጸብራቅ ሆኖ የተጀመረ ንቅናቄ ሲሆን፣ ቀደም ባሉት ጊዜያት የነበረውን ማንኛውንም የእውናዊነት (Rationalistic) እና መላምታዊ (Speculative) ፍልስፍና ለመቃወም ሲባል

የተጀመረ እንቅስቃሴ ነው (Azhar፣2013)፡፡ እንደ Azhar ትንታኔ በተለይ ደግሞ የHegelian (የሄግሎያን) ፍልስፍና ያነጣጥር የነበረው ዓለምን እንደፈጣሪ ስጦታ እና የሰው ልጆችን ደግሞ ረዳት የሌላቸው የትልቅ ሚስጥራዊ ድራማ ተዋናይ ወይም ገፀ ባህርያት አድርጎ ይቆጥር በነበረው የሃሳባዊያን እሳቤ ላይ ነበር፡፡ ይሁን እንጅ ከዚህ አተያይ በተለየ መልኩ ነገረ ህላዌ የሰዎችን ሁኔታዊ አስተሳሰብ ወይም ግለሰባዊ ህላዌ እና የህላዊ ፍላጎትን የሚያጎላ ፍልስፍናዊ እሳቤ ነው፡፡ (Azhar፣ 2013፣166)

ዘመናዊው የነገረ ህላዌ ፍልስፍና እንደፍቅር ወይም ጥልቅ የሆነ የፍቅር ስሜት፣ ደስታ፣ የውሳኔ ባለቤትነት ወይም ውሳኔ ሰጭነት፣ ጭንቀት፣ ህመም(sickness)፣ ተስፋመቁረጥ እና ሞት የመሳሰሉት የሰው ልጆችን ዋና ዋና የህልውና መልኮችን ቁብ ሳይሰጥ ከቆየው የጥንታዊው (Classical) ፍልስፍና በተለየ መልኩ እነዚህን ህልውናዊ ጉዳዮች የሚያጎላ የፍልስፍና እሳቤ ነው፡፡ በሌላ አባባል ይህ ዘመናዊ የህልውና ፍልስፍና በእያንዳንዱ ግለሰብ ሁኔታ (individual situation)፣ የህልውና፣ የትክክለኛነት እንዲሁም የሁለንተናዊ ነጻነት (universal freedom) ላይ የሚያተኩር ሰብዓዊ አተያይ ነው፡፡ ዋነኛ ዓላማውም ቢሆን፣ በዘመናዊው ዓለም ውስጥ እያንዳንዱ የሰው ልጅ የተሟላ ህይወትን እንዴት መምራት እንደሚችል ማስገንዘብ እንደሆነ Azhar (2013፣134)፣ Guignon (2005፣ 252)ን ጠቅሶ ሀሳቡን ያስቀምጣል፡፡

Mobini እና Salimpour (2016) ደግሞ፣ የህልውናዊነት የፍልስፍና ጽንሰ ሃሳብ ስርዓታዊ የእውቀት መስክ እንዲሆን ያደረገው በዋናነት William Friederich Hegel ነው ይላሉ፡፡ ይህ የHegel የፍልስፍና ለውጥ ዘይቤ ደግሞ ሌሎችን የህልውናዊነት ሃሳባውያንን ወደፍልስፍና መስክ ፊታቸውን እንዲያዞሩ ወይም እንዲያዘነብሉ አድርጓቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት ከክርስቲያናዊ ህልውናዊያን (Christian existentialist) መካከል አንዱ የሆነው Kierkegaard በክርስትና እምነት እና በፍልስፍና መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሳየት ሞክሯል፡፡ Kierkegaard፣ ፍልስፍና የእምነት መነሻ ሳይሆን ሰዎች ሞራላዊ እና ሃይማኖታዊ ህላዌ እንዲኖራቸው የሚያግዝ እሳቤ ነው ብሎ ያምናል፡፡ Nietzsche በበኩሉ፣ ለጀርመናውያን ሳይንሳዊ የፍልስፍና ማዕከል ፈላስፋዎች የፍልስፍና ልምዳቸው ትክክለኛው ውጤት አስፈሪ እና አድካሚም እንደሆነ ለማሳየት በመፈለግ፣ ይኸው ፍልስፍና የባሪያዎችን (የጥቁሮችን) ሃይለኛ የስኬት ባህሪ የማግለል ባህል እንዳላው እና ይኸውም ለታላቅ ዓላማቸው መሳካትም ዋነኛ እንቅፋት እንደሚሆን በራሱ ፍልስፍና ለማሳየት ሞክሯል፡፡

> Nietzsche is someone who shows that the enthusiasm for the truth resulted from the idea list tradition of German Scientific- academic philosophy is fear fuland weaking. Nietzsche's philosophy addresses those who have the Courage to reject slaves' behavior, those who have courage to overcome the obstacle on their way to achieving their great goal. (Mobiniand and Salimpour, 2016, 87)

በተመሳሳይ መልኩ Heidegger የታላላቅ ፈላስፋዎች የህልውናዊነት ፍልስፍና ስሌት በሚያሳካ መልኩ የተደራጀ አይደለም በማለት እንደ Nietzsche እና Kierkegaard ሁሉ የጀርመናውያን ሃሳባውያንን የፍልስፍና ልምድ በተለያየ መልኩ በመቃወም እና ይኸው የፍልስፍና ባህል ከንቱ እንደሆነ እና ስሌታማ እንዳልሆነ በግልጽ የሚያሳዩ ርዕሰ ጉዳዮችን በማቅረብ አሳይቷል፡፡

እንደ Mobini እና Salimpour (2016) ሃሳብ በ19ኛው እና በ20ኛው ክፍለ ዘመናት በተለያዩ ዘርፎች የተሰማሩ በርካታ የሥነሰብዕ ተመራማሪዎች ወይም ሥነሰብዓዊያን(Humanists)፣ አማንያን(Theists)፣ በአምላክ ህላዌ የማያምኑ ወይም ኢ-አማንያን(atheists)፣ አይሁዳውያን(Jewish) እና ክርስቲያን(Christian) ጸሐፍት እና ፈላስፎች ቀደምትነት ሌላው የህልውናዊነት እሳቤ መስፋፋት እና ማደግ ታላላቅ ሚናን ተጫውተዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል በ19ኛው ክ/ዘመን እነ Kierkegaard, Nietzsche, Dostoevsky, Leo Tolstoy የሚጠቀሱ ሲሆን፤ ወደ 20ኛው ክ/ዘመን ስንመጣ ደግሞ፣ እነ Jean-Paul Sartre, Simone de Beauvoir, Albert Camus, Martin Heidegger, Gabriel Marcel, Karl Jasper, Martin Buber, Rudulf Bultmann, Berdyaev እና Maguel de Unumuno ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ ያብራራሉ፡፡

በመጨረሻም የሰው ልጆች የህልውና ፍልስፍና ጥንታዊ መሠረት ያለው እና በ19ኛው እና በ20ኛው ክፍለ ዘመናት ሠፊ ሽፋን የተሰጠው እሳቤ መሆኑን ልብ ማለት ይቻላል፡፡ ቴዎድሮስ(2001፣ 141-142) Flynnን እና John Macquarrieን ዋቢ አድርጎ የገለጸው "የነገረ ህላዌ ፍልስፍና በረጅሙ የሰው ልጅ የስልጣኔ ታሪክ ውስጥ ከሰው ልጅ ህልውና ጋር ተቆራኝቶ ዛሬን ጭምር የዘለቀ ርዕሰ ጉዳይ እና የአስተሳሰብ ዘይቤ" መሆኑን ከጠቀሰ በኋላ፣ ትክክለኛው የነገረ ህላዌ ዘመን ብሎ የሚደመድመው ግን የ20ኛውን ክፍለ ዘመን ነው፡፡

ህልውና የሁሉም መሰረት መሆን በሁሉም የነገረ ህላዌ አሰላሳዮች ማለትም ጥንታዊ፣ የመካከለኛ ዘመንም ሆነ የዘመናዊ አለም አሰላሳዮች አቋም ነው፡፡ ሁሉም ቢሆኑ በሰው ልጅ ተጨባጭ ህለውና ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ ሌላኛዉ ደግሞ እነዚህን ፈላስፎች አንድ የሚያደርጋቸዉ የጋራ ጉዳይ የጭብጥ ምርጫ ነዉ፡፡ በብዙዎቹ ህልዉናዊ ፈላስፎች ስራዎች ዉስጥ ተመላልሰዉ የሚመጡ የተወሰኑ ጭብጦች መኖራቸዉንና እነዚህን ጭብጦች ሚኪሪ በሶስት ወገን እንደሚከፍላቸዉ ቴዎድሮስ (2001፣143) ገልጸዋል፡፡

የመጀመሪያዉ ወገን ለአንድ ሰዉ ግለሰባዊ ማንነት መሰረት የሆኑ ጨመቅና ህልዉናን፣ ምርጫና ዉሳኔን እንዲሁም ነጻነትና ሀላፊነትን የያዘ ነዉ፡፡ እንደ ወንጀለኝነት፣ ባይተዋርነት፣ ቀቢጸ ተስፋ፣ ሞት የመሳሰሉት የሰዉ ህልዉና ትራጀዲያዊ ገጽታዎች በሁለተኛ ወገንነት ይፈረጃሉ፡፡ ሶስተኛዉ ወገን ደግሞ በቀደምት ፍልስፍናዎች ትኩረት ተነፍጎት የኖረዉን የሰዉን ልጅ የስሜት ጣጣ ጭንቀት፣ ፍርሃት፣ ስጋት የመሳሰሉ ስሜቶችን ይይዛል ነዉ፡፡ የሰዉ ህልዉና ትራጀዲያዊ ገጽታዎች በሁለተኛ ወገንነት ከሚፈረጁት መካከል የሆነውን ሞትን ምንነት እንደሚከተለው አሳያለሁ፡፡

### 2.2.3. ሞት (Death)

ሞት ሰፊና ዝንቅ የሆነት ርጉም ያለውት ትዕምርት ነው፡፡ ከመዝበቃላዊ ትርጉም ስንነሳ "ሞተ፡-ነፍሱከ ስጋው ተለየች፣ ተዳከመ፣ ቀነሰ፣ አቅም አጣ፣ ሰነፈ፣ ተስፋ ቆረጠ፣ አንድን ነገር ከተገቢው በላይ አደረገ" የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993) በሚል ገልፆታል፡፡ በዚህ መዝገበ ቃላዊፍች ሞት ሁለት የተለያዩ ጽንሰሃሳቦችን አንደያዘ ያሳያል፡፡ አንደኛው የህይወት ፍጻሜን ሲያመለክት ሁለተኛው ደግሞ በሰው ልጅ የህይወት እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ የአቅም ማጣት፣ መዳከም፣ መቀነስ፣ መሸነፍ (ተስፋመቁረጥ)፣ የማይገባ ስራ መስራት የሚል ሃሳቦችን እንደያዘ ያሳያል፡፡

ሌስተርና ሌስተር (1971፣ 23) ስለሞት የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> Death is a gragual process, and no one moment can be identified as the time when it occurs. From the view point of sociology, the question of when physical death occurs is less important than the individual subjective experience of death.

ሞት ሂደት ነው፤ ስለዚህ ውጤቱን መጠበቅ ያለብን ከዚህ ሂደቱ እንጂ ከሚቋጭበት ነጥብ፤ ከግብራካል ስርዓት መቋረጥ አይደለም፡፡

በነገረ ህላዌ ፈላስፋዎች እንደ አንድ የህልውናችን ቁልፍ አካል በሞት ትርጓሜ እና ፍቺ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡ ይህ ሞት የምንለው ክስተት ለሰው ልጅ ገዳቢው ከሆኑ ጉዳዮች መካከል ነው፡፡ በኤግዚስቴንሻሊዝም መዝገበቃላት ሞት የሚከተለውን ፍች ተሰጥቶታል፡፡ “አንድ ህልውና ያለው ጊዜ የምንለው ሂደት መጨረሻ እንዳለው የሚገለጽበት የማይገረሰስ ወይም የማይቆም ክስተት ነው፡፡” ሀይደጋር በበኩሉ ሞትን የውይይታችን ማእከል በማድረግ የሚከተለውን ይላል፡፡ “ሞት በእውነትም እርግጥ እስከሆነ ድረስ ማናችንም ብንሆን ከመሸፋፈን ይልቅ አይቀሬ መሆኑን ብንቀበል የተሻለ ነው፡፡ ነገር ግን ሞት አይቀሬ እንደመሆኑ መጠን እና ማናችንም መቼ እንደሚከሰት እስከማናውቅ ድረስ አንድ ነገር ከማድረግ ወይም እለታዊ ትግላችንን ከመቀጠል ወደ ኋላ አንልም” (ድሬፋስ እና ዋትሆል፣ 2006)፡፡

የሞት በእርግጠኝነት መከሰት ከነገረ ህላዌ ፈላስፋዎች ጋር ያለው ጉድኝት ምንድን ነው? የህልዉናዊነት ፍልስፍና አራማጆች እንደሚናገሩት የሰውልጅ ይህንን እውነት እስከተዋጠለት ድረስ እና መምጫው የማይታወቀው ሞትን እስከተቀበለው ድረስ ይህ ቂላቂል እና ትርጉም የለሽ ህይወትን ትርጉም እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ከዚህ ባለፈ ሬንሀርት(1952) እንደተናገረው “ከመኖር ወደ አለመኖር የመሸጋገር ሁኔታ የሚለቅብን ፍርሃት ምን አልባት የእፎይታ ስሜትም ሊኖረው ይችላል፡፡ በሞት እርግጠኝነት ውስጥ አንድ ሰው ፍጹማዊ የሆነ ከጊዜ እና ከሞት ውጪ ያለውን ሰላም ሊያገኝ ይችላል፡፡” ይህ በተዘዋዋሪ ማለት ትክክለኛ ህልውና ያለው ሰው የሚባለው ህልውናው አሁን በዚች ቅጽበት የሚገለጽ እና በተቻለ መጠን የመኖሩን ትርጉም በድርጊት የሚገልጽ ሰው ማለት ነው፡፡

ሞትን በተመለከተ ቴዎድሮስ (2001፣152) ሆልን በመጥቀስ እንዲህ ሲል ገልጾታል፡፡ “ሞት ተፈጥሯዊ ክስተት ብቻ አይደለም፡፡ የነገሮች መቋረጫ፣ መፈጸሚያም አይደለም፡፡ ይልቁኑ እንደየዘመኑ፣ እንደየግለሰቡ ርዕዮተ አለም አንድም እየተባለ ሊፈከርና ሊተረጎም የሚችል ዝንቅ ትምህርት ነው እንጂ፡፡ በስነ ጽሁፍ ውስጥ ሞት አይነት አለው፤ የሟች ማንነት፣ የአሟሟቱ እንዴትነት እሴት ያግታል፤ ፍች ይለውጣል፡፡” ቴዎድሮስ (2001፣153) ኒቼን በመጥቀስ እንዲህ ሲል ገልጾታል፡፡

> የሰው ልጅ ሞትን በድል መወጣት አልያም ሞትን “በሞት” መቀበል
> ይቻላል፡፡ አንድ ሰው በህይወት አልነውም በዩኒቨርስ ውስጥ ለመገኘቱ

> ምክንያት የሆነውን ታላቅ ተግባር በማከናወን ወይም የጀግንነትን፣ የተጋዳሊነትን ግዳጅ በመፈጸም በጥበብ ኑሮ በጥበብ ማለፍ ከቻለ፣ ሞቱ ጊዜውን የጠበቀ ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒ በርዕይ አልባነት መኖር፣ ያበጁት ርዕይ ላይ መድረስ አለመቻል ጊዜውን ባልጠበቀ ሚችነት ያስፈርጃል፡፡

ቴወድሮስ (2001፣153) ማይልስን (1991፡202) በመጥቀስ "Die at the right time! He that consummates his life dies his death victoriously." በማለት አብራርተዋል፡፡

ገብሬ ባይሌ (2010፣20) ሚችል ማንን (2008) በመጥቀስ

> ሞት ማለት የአካል መጥፋት አይደለም፤ ይልቁንስ የሁሉም የእያንዳንዱ ሰው እጣ ፈንታ በመሆኑ የሰው ልጅ ስለሞት ትርጓሜ ግንዛቤ አለው፡፡ አንድ ሰው ስለሞት የግንዛቤ እውቅና ሲኖረው እውነተኛ ህልውና ሊተገብር ይችላል ወይም ልትተገብር ትችላለች፡፡ ሞት የአንድ ሰው ህልውና የማብቂያ ወሰን አድርገን ልንመለከተው እንችል ይሆናል፡፡

በማለት ያብራራል፡፡

እንደ Whole አገለሳለጽ ሞት፤ "Death itself is not only a state, but a complex symbol, the significance of which will vary from one person to another and one culture to another."

ሞት ተፈጥሯዊ ክስተት ብቻ አይደለም፡፡ የነገሮች መቁረጫ፤ መፈጸሚያ አይደለም፡፡ ይልቁኑ እንደየባህሉ፣ እንደየዘመኑ፣እንደየግለሰቡ ርዕዮተ ዓለም አንድም እየተባለ ሊፈከርና ሊተረጎም የሚችል ዝንቅ ትዕምርት እንጂ፡፡ በስነጽሑፍ ውስጥ ሞት አይነት አለው፤ የሟች ምንነት፣ የአሟሟቱ እንዴትነት እሴት ያግታል፤ ፍቺ ይለውጣል፡፡

ሞት በማንኛውም ጊዜና ቦታ በሰው ልጅ የእለት ተለት የህይዎት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚያጋጥም ወይም የሚከሰት የኑሮ ስጋት ነው፡፡ (Mohammed,2016፣8) በሌላ በኩል ይህ ተመራማሪ ሞት በሁለት የተለያዩ መንገዶች መታየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ አንደኛው መንገድ ከግል ስሜት ጋር/subjective/ በተያያዘ ሞት በእያንዳንዱ የእለት ተዕለት የህይወት እንቅስቃሴያችን የምንገነዘበው፤ በማንኛውም እንቅስቃሴያችን የሚከሰት ተጨባጭ ምክንያት የማያስፈልገው ሁሉ ጊዜም አብሮን የሚኖር አስጊ ሁኔታ ነው፡፡ የሰው ልጅ ማንኛውንም

እንቅስቃሴ ከሞት ጋር ትይዩ ነው። ሞት ያልተለመደ ድርጊት ሳይሆን ወደፊት በማንኘውም እንቅስቃሴ ውስጥ ሊከሰት የሚችሉ ጉዳይ ነው በማለት እንደሚከተለው ገልጾታል።

"Death means; the every single day of our life you realize that the death occur at any moment and there is no necessary reason why we should live another day. --- Death is always impending."(Mohammed, 2016፣8-10) በማለት ገልጾታል።

ሁለተኛው የሞት መታያ መንገድ ሞትን ገሃዳዊው/objective/ በሆነው አለም መመልከት ነው። ሞት ታስቦ፣ አዘውትሮ ወይም ተደጋግሞ የሚመጣ አይደለም። በሰው ልጅ የኑሮ ሂደት ውስጥ ችግር በመሆን አንድ ቀን ድንገት የሚከሰት ድርጊት ነው። የሰው ልጅ ገሃዳዊ የሆነውን ሞት ተከላክሎ ወይም ወስኖ ማስቀረት አይችልም። ዜኒከማሁ /ገጽ፣11/ ሞት ሰፊና ዝንቅ ትዕምርትን እንደሚወክል የተለያዩ ምሁራን ከዚህ በላይ ከሰጡት ብያኔ እና ትርጉም መረዳት ይቻላል። ለሞት አንድ ወጥ የሆነ ሁለንም የሚያስማማ ትርጉም መስጠት እንደማይቻል ያሳያል። አንዳንዶቹ ስነ ህይወታዊ ሞትን፤ አንዳንዶቹ ማንነትን፤ አንዳንዶቹ ከነገረህላዊ ፍልስፍና አንጻር፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ከሰው ልጅ የእለት ተዕለት እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ከግል ስሜት ጋር የሚገናኘውን እና ሞትን ገሃዳዊ በሆነው ዓለም ውስጥ መመልከትን መነሻ ሲያደርጉ ታይሰን(2006) ደግሞ ከሞት ፍርሃት ጋር በማያያዝ አይታለች።

በሌላ በኩል ቴዎድሮስ(2001፣153) ሜርሎድ ዌይስትፋልን /Merlod Westphal/ በመጥቀስ ሞት በጥቅሉ ሁለት አይነትነው። አንደኛው አይነት ስነህይወታዊ ሞት ተብሎ ሲጠራ ሁለተኛው ድግሞ ነገረ ህልውናዊ ሞት ተብሎ ይጠራል ሲሉ ይገልፃሉ። ሥነህይወታዊ ሞት ከሰው ልጅ ቁጥጥር ውጭ የሆነ ህይወት ያለውን ሁሉ የሚገዛ በአደጋ፣ በረሀብ፣ በእርዛት፣...ይመጣል ሲሉ የሰው ልጅ የተለያዩ ማንነቶች ያሉት ፍጡር በመሆኑ ሥነ ማህበራዊ ማንነት፣ሥነ ልቦናዊ ማንነት እና ሥነምግባራዊ ማንነት አለው። ስለዚህ የሰው ልጅም ከሥነህይዎታዊ ሞት በተጨማሪ ራስ ግድያ እና ጊዜውን ያልጠበቀ የሞት ጭብጦችን መሰረት ያደረገ ነው።

### 2.2.3.1. ስነ ህይወታዊ ሞት

Westphal (1984, 102) ስነ ህይወታዊ ሞት ከሰው ልጅ ቁጥጥር ውጭ የሆነ፣ ፍጡርን ሁሉ የሚገዛ እጣ ነው። ይህ እጣ በአደጋ ይከሰታል፤ በርሃብ፣ በእርዛትና በጥማት ይመጣል።

ቴዎድሮስ(2001፣180) ሞትን ማን ነው በርሃብና በጥም ብቻ የሚከሰት ስነ ህይወታዊ ጉዳይ ያደረገው? የሰው ልጅ ህልውና ከስነ ህይወታዊ ተግባር ብቻ ማቆራኘት፣ ማንነቱንና ምንነቱን በእጅጉ ማሳነስ ነው። ሰው ማህበራዊ፣ ልቡናዊ፣ ህልውናዎችም አሉት። ስሊዚህ ፍርሃት፣ ጭንቀት፣ ፀፀት፣ ተስፋ ማጣት፣ ወንጀለኝነት፣ ወዘተ. የሚፈጥሩትም ሞት አለ። እንደውም እስከጽንፍ ለመከራከር ስነ ህይወታዊ ሞት ከእነዚህ ሁሉ ሞቶች የሚያመልጥበት፣ የሚገላገልበት መንገድ ነው።

ሞት ገጠመኝ ወይስ ልምድ ሊደረግ የሚችል ሃሳብ ነውን? ሞት ከህይወት ውጭ ነው፤ ከቶውንም ገጠመኝ ሊደረግ አይችልም የሚል አቋም ያለው ፉኮ (Foucault) የሚከተለው ብሏል፤ “Death is not an experience. It is an absence, avoid. There is no reflection that can indirectly or directly discover signs of its plentitude of its full presence.” (በሌሜርትና ጂላን የተጠቀሰ)።

ሞት ለቋሚው ጭምር እጅግ ቅርብ ነው። የሚከተለው የኢማኑኤል ሌቪናስ (Emmanuel Levinas, 2000፣ 12-13) ፍልስፍናዊ አቋም በተንዳጁም ቢሆን ከዚህ አቋም ጋር ይሰምራል፤ ወይም ቢያንስ ቢያንስ የፉኮን ሀሳብ ያለዝባል፤

> The death of the others who dies affects me in my identity as a responsible `me`; … which is not simple coherence of variouse acts of identification, but is made up of an ineffable responsibility. My being affected by the death of others is precisely that, my relation with his death… Dying as the dying of other [I,autre], affects my identity as `I` [Moi], its rupture with the same, its rupture of my ``I` [Moi], its rupture of the same in `I` [Moi](ቴወዎድሮስ 2001፣ 184-185)

### 2.2.3.2. ራስ ግድያ

የሰው ልጅ በገዛ ፈቃዱ የሚፈጽመው ጉስቁልና፣ ድቀት ወይም በጥቅሉ ስነ ህይወታዊ ጥንካሬውን ሚሸረሽር የትኛውም ተግባር(a voluntary elimination of biological fitness) ከራስ ጉዳት፣ ከራስ ግድያ ጋር እጅግ ጥብቅ ዝምድና አለው፡፡

ሌስተርና ሌስተር (1971፣ 58-59) ስለገድሎ ሟችና ገድሎ ሟችነት የሚከተለውን ይላሉ፤

> The suicidal murderers did not seem to have killed themselves in order to escape punishement for the previouse killing. In many cases, the suicide seemed to have motivated by despair rather than hostility…. The suicide might then wish to rejoin the person he has killed and attempt to do so by means of his own death.

በቀጣዩ ጥቅስ ዌስትፉል እንደሚለው፤ የፈጸሙትን ወንጀል ህሌና ካመነ፣ ልብ ከተቀበለ በገዳይ አንደበት የሟች ድምጽ ይመላለሳል፤ (Guilt is a kind of echo effect; for when that voice resounds off the walls of the self's inner life it has been transformed into the self's own voice) (81-82):: ለራስ ግድያ ጥናቶች ዛሬም ድረስ መሰረት በሆነው፣ በፈረንሳዊው የስነ ማህበረሰብ ምሁር፣ በኢማይል ደርኪሄም (Durkheim, 1963, 44) ስለራስ ግድያ የሚከተለውን ብሏል፡፡

"The term suicide is applied to all cases death resulting directly, or indirectly, from a positive or negative act of the victim himself, which he knows will produce this result."

የሰው ልጅ በገዛ ፈቃዱ የሚፈጽመው ጉስቁልና፣ ድቀት ወይም በጥቅሉ ስነ ህይወታዊ ጥንካሬውን ሚሸረሽር የትኛውም ተግባር(a voluntary elimination of biological fitness) ከራስ ጉዳት፣ ከራስ ግድያ ጋር እጅግ ጥብቅ ዝምድና አለው፡፡ በደርኪሄም እምነት፣ ራስን ከምግብና ከውሃ ማቀብ፣ በሽጉጥ የገዛ አናትን እንደመንደል፣ በስለት ደም ስርን እንደመበጠስ፣ መርዝ እንደመጨለጥ፣ ከፎቅ እንደመወርወር ወዘተ. ሁሉ ራስን የመግደያ ዘዴ ነው፡፡ ("Refusal to take food is as suidal sa self-destruction bay a danger or fire arm"

### 2.2.3.3. ጊዜውን የጠበቀና ጊዜውን ያልጠበቀ ሞት

Miles (1991፣ 202) እንዳለው፤ አንድ ሰው በህይወት አልነውም በዩኒቨርስ ውስጥ ለመገኘቱ ምክንያት የሆነውን ታላቅ ተግባር በማከናወን ወይም የጀግንነትን፣ የተጋዳሊነትን ግዳጅ በመፈጸም በጥበብ ኖሮ በጥበብ ማለፍ ከቻለ፣ ሞቱ ጊዜውን የጠበቀ ነው፡፡ “Die at the right time he that consumates his life dies his death victoriously. ከዚህ በተቃራኒ በርዕይ አልባነት መኖር፣ ያበጁት ረዕይ ላይ መድረስ አለመቻል ጊዜውን ባልጠበቀ ሟችነት ያስፈርጃል፡፡

በኒቼ እምነት መሰረት ደግሞ፣ የሰው ልጅ ሞትን በድል መወጣት አልያም ሞትን “በሞት” መቀበል ይችላል፡፡

ቴዎድሮስ(2001፣158) እንደሚለው፤ ድንገተኛ ሞት ሙሉ በሙሉ ያልጠበቁትን፣ ፈጽሞ ያልጠረጠሩትንና ያልተዘጋጁበትን እንደፈጣን ጥቃት ያለን ወይም እንደንጥቂያ ያለን የአሟሟት ሁኔታ ያመለክታል፡፡ እዚህ ጋር ድንገተኛ ሞት(sudden death) ጊዜውን ካጠበቀ ሞት(untimely death) ለይቶ መመልከት ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ድንገተኛ ሞት፣ በሰው ላይ የሚመጣ በሰው ላይ የሚደርስ ክስተት ነውና እጅጉን ከስነ ህይወታዊ ሞት ጋር ይዛመዳል፡፡ በአንጻሩ ጊዜውን ያልጠበቀ ሞት በዋናነት ሰውን ከሌላ ክስተት ጋር ሳይሆን ከራሱ ጋር ምን አደረኩ? የት ደረስኩ? ወዘተ. በሚሉ ጥያቄዎች ስለሚያሟግት ከስነ ህይወታዊ ሞት ይልቃል፡፡ እጅጉንም የፍልስፍና የንድምታ ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ ወገኑ የነገረ ህልውና ሞት ነው፡፡ ወቅት መጠበቅ፣ ዘመን መቁጠር፣ እድሜን መገመት በዋነኛነት ስነ ህይወታዊ ጣጣ ነው፡፡

ሀይደርጋር እንደሚለው፤ የሰው ልጅ በሕይወት ውስጥ ሁሌም ለመቅጠፍ እንደደረሰ ፍሬ ነው፡፡ “As soon as man comes to life, hi is at once old enough to die”፡፡ እነዚህ የጊዜ ገጽታዎች በነገረ ህልውናዊ ማንነት ላይ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ አይኖራቸውም ባይባልም እንኳ፣ የስነ ህይወቱን ያህል ግን ወሳኞች አይደሉም፡፡ በሌቬናስ (40) አንደሚለው፣ “በነገረ ሀልውና ማንነታችን ላይ ሞት፣ ወቅት አይጠብቅም፣ ጊዜ አይመትርም፣ ዘመን አይቆጥርም፡፡”

# ምዕራፍ ሶስት፡- የሞት ጭብጥ ትንተና በቅበላ ረጅም ልቦለድ

## 3.1. የልቦለዱ አጽመ ታሪክ

የአለማየሁ ገላጋይ የድርሰት ስራ የሆነዉ *ቅበላ* በ2009 ዓ.ም በድጋሜ የታተመና በ206 ገጾች ተወስኖ የቀረበ ሰፍ ያለ ታሪክን የያዘ ስራ ነዉ፡፡ የልብ ወለድ ታሪኩ በምእራፍ ተከፋፍሎና በሶስት ክፍሎች ተደራጅቶ የቀረበ ነዉ፡፡ የመጀመሪያዉ ክፍል ክስ የሚል ርእስ ይዞ ቀርቧል፡፡ ሁለተኛዉ ክፍል ፍትህንና ሶስተኛዉ ክፍል ደግሞ ፍርድን ይዘዉ የቀረቡ ታሪኮችን ይነግሩናል፡፡ የታሪኩ መቼት በ1966 ድህረ የአብዮቱ ዘመን ላይ ያጠነጥናል፡፡ በሶስቱም ምዕራፎች ሶስት የተለያዩ ዋና ገጸ ባህሪያት ምቾት በራቀዉ እና ህይወት ፊቷን ያዞረችባቸዉ ዉጥንቅጡ በጠፋበት አለም ዉስጥ ህልዉናን ለማቆየት መከራቸዉን የሚያዩ ገጸ ባህሪያት ተቀርጸዉበታል፡፡

ታሪኩ የሚጀምረው የማቴዎስን እለታዊ መደበኛ እንቅስቃሴውን በመንገር ነው፡፡ ማቲዎስ ከእናት እና ከአባቱ ተነጥሎ እንዲኖር የተፈረደበት ነው፡፡ ከአባቱ ጭን ተቀምጦ እንዳየጫት ከመከልከሏ በላይ አባቱን ወደውስጥ ይዛ ስትገባ ማቲዎስን ከቤት እንዲወጣ ታደረግ ነበር፡፡ እናቱ ይህን ለምን እንደምታደርገው ባይገባውም የትርፍነት፣ ተፈላጊ ያለመሆንና የመገፋት ስሜት በውስጡ አዳብሮና የእናቱ ጥላቻ አጎልብቶ ያደገ ነው፡፡ ይህ በህይወቱ ጠባሳ ጥሎበት እንዳለፈ እና እስከለዕተ ሞቱ ድረስ በህይወቱ ታሪክ አብሮ ዘልቋል፡፡

ማቲዎስ ከጉረምስና ዘመኑ እስከ አዋቂነት ዘመኑ አዲስ አበባ ያሳለፋቸውን ውጣውረዶች ይተርክልናል፡፡ ማቲዎስ ጎደሎ ቁጥር አይወድም ነበር፡፡ ምክንያቱም በልጅነቱ ከእናት እና ከአባቱ ፍቅር ያላገኘው ሶስተኛ ሰው ትርፍ ነኝ ብሎ ስለሚያስብ ነው፡፡ ከአክስቱ ጋር ሲኖር በቁጥር አምስት ሲሆኑ ለኩንየ ገንዘብ ሰጥቶ እንድትጠፋ አድርጓል፡፡ የክቴ ስትሞት ዙሮ ጎደሎነት ስለተሰማው "ከዚች ምድር ያተረፍኩት ለሰው ልጅ ያለኝ ጽኑ ፍቅር ነው፡፡ አረሳሱንም እንደ ፍቅረ ሃዋሪያ ይቀጥራል፡፡

በልጅነቱ ከእናት አባቱ የጣውን ፍቅር ከማህበረሰቡ ያገኝ ስለሚመስለው ብዙ ሰው ተሰብስቦ ወዳለበት መገኘት ያዘወትራል፡፡ ነኝ ብሎ የሚያስበውን መኖር የማይችል አስመሳይ ፍቅረ ሃዋሪያ ነው፡፡ የሚቀርባቸው በሙሉ ይጠሉታል፡፡

የማቴዎስ አባት እናቱን ገድሎ ራሱን አጥፍቷል፡፡ ሞት የሰው እጣ ፋንታ ነው ቢባልም ቢባልም ማቲዎስ ሞትን ይፈራል፡፡ በመጠጥ ራሱን ደብቆ ይኖራል፡፡ በራሱ ምርጫ አይኖርም፡፡ ስለሰው ልጅ ፍቅር ቢዘምርም መጨረሻ እንደ አባቱ  ሶሬኔን ገሎ ራሱን ያጠፋል፡፡

መንክርን ስምንተኛ ክፍል እስኪሆነው ያሳደገችው አክስቱ ናት፡፡ መንክር ከ12 ዓመት የስደት ኑሮ ተመልሶ ነው ታሪኩ የሚጀምረው፡፡ ራሱን የሚያይበት መነጸር ሌሎችን ከምያይበት እጅጉን የተለየ ነው፡፡ ስለድረሰት ስራ ባዝሃን የሚያምንበትን እና የሚቀበለውን ጉዳይ በአፍራሽነት ይተረጉመዋል፡፡ ድርሰት የገሃዱ አልመ ነጸብራቅ ሳይሆን የተቀነባበረ ውሸት ነው ይላል፡፡  ፍቅር ለሰው ልጅ ካንሰር ነው፤ ያውም የሚስተላለፍ በሽታ ይለናል፡፡ ትዳር የመተሳሰር ስምምነት ነው ይላል፡፡ ሰው የሚባለው በተናጠል ሲቀርብ እንጅ ሲሰባሰብ የማመዛዘኑ ስሜት ይሰረቃል ብሎ ያምናል፡፡ ባገኘው አጋጣሚ ማህበረሰቡ ሲያጥላላ እና ሲነቅፍ ይታያል፡፡ ተቀጥሮ ከሚሰራበት መስሪያ ቤት ጓደኛ የለውም፡፡

ሰው ከሰው ተርታ የሚመደበው ብቻውን ሲሆን ነው፡፡ ምክንያቱም ማህበራዊነት የጥፋት መነመሻ ባይሆን ኑሮ ያ ሁሉ ሰው ተሰብስቦ እናቴን ቀጥቅጦ አይገድላትም ነበር የሚል እሳቤ ያራምዳል፡፡ የእናቴ ምትክ ትሆነኛለች ያላትን አስቴር የሆነ ቡድን አሳጥቶታል፡፡

በእናቱ ሞት ምክንያት መንክር ህይወትን የሚኖራት ያለምንም ጉጉትና ፍቅር ነው፡፡ አስቴር በወቅቱ በነበረው ፖለቲካ በመንቀፍ በኢሃፓ መስመር ህዝቤን ነጻ አወጣለው ብላ ተነስታ ስለነብር እንሂድ ስተለው አከትሎ ይሄዳል፡፡ መንክር አነአሰቴር ምግብ እንዲያመጣ ያዙት ነበር፡፡ ባለቤቷ ተጫኔ የመነክር ዘመድ ይሁን እንጅ  መንክርን የሚያዘው በጥላቻ አይን ነበር፡፡ አንድ ቀን እነአስቴር የሚያድሩበት የሳር ሰቀላ የአያቱ እህት መንክርን ሲደበድቡት አደሩ፡፡ መንክር ግን በመደብደቡ ሳይሆን የበለጠ ያሰበው አሰቴር ከውስጥ ተቃጥላ እንደሆነ ብሎ ነው፡፡ አስቴርን መፈለግ የሞተችዉ እናቱን መፈለግ ያህል ተሰምቶታል፡፡ ኢሃፓን የተቀላቀለው ፈልጎ ሳይሆን አስቴርን በመፈለግ ነው፡፡ አስቴር መንክርን የእናት ያህል ነው የምትበልጠው፡፡ አንድ ልጅ እንዳላትና እሷን ሳታሳድግ ወደ ትግሉ እንደገባች ነግረዋልች፡፡ መንክርን ወደ ማሰቃያ ቦታ ተወስዶ አሰቴር የት እንዳለች እንዲነግራቸው ቢጠይቁትም ምልሽ አልሰጣቸውም፤ አጎቱ ተጫኔ እንደሚገድለው ቢነግረውም  ምንም ነገር አይመልስለትም፡፡ የእሱ ትልቁ ነገር አስቴር እንጅ ትግሉ አልነበረም፡፡ አሰቴርን ልጇን የእሱን እና የእናቱን ምስሌ አድረጎ ስሏቸዋል፡፡ ለመንክር በህይወት መኖርና መሞት አንድ ነው፡፡ አስቴርም መንክርን መያዣ ስላደረጉት እራሷን አሳልፋ ትሰጣለች፡፡ በዚህ መንክር በጣም ይናደዳል፡፡ ከእሷ ጋር አብሮ እንዳይሞት መኖር ለአስቴር ትልቅ ዋጋ እንዳለው ያምናል፡፡ እሱም የአስቴር ልጅ ትግስት ነች፡፡ ለዚህ ነው

12 አመት በባእድ ገር  ሃገር ሲንከራተተት ቆይቶ በወቅትቱ የነበረውን አገዛዝ ሲወድቅ ወደሀገር ቤት የተመለሰው፡፡ መንክር ከተመለሰም በኋላም የጣለችበትን አደራ ለመወጣት መኖሩን ታግሶ ትግስት ትክክለኛ ማናነቷን  እንድታውቅ ትክክለኛ ጊዜው እስኪደርስ በትግስት እና በተስፋ ሲጠብቅ እናየዋለን፡፡

ማቲዎስ መንክርን “አንተን የተረጋጋህ ሰው ነህ ሁሉም ነገር አለስ ሲለው ምንም ነገር ስለማልፈልግ ነው ሁሉም ነገር ያለኝ የመሰለህ፡፡” መንክር ትዳር የለውም፡፡ ለወደፊትም የሚፈልገው ነገር ምን እንደሆነ ሲናገርም ሆነ ሲያደርግ አይታይም ነበር፡፡ በህይወት መቆየት የሚፈልገው ለትግስት ብቻ ነው፡፡

የመንክርን እናት የአልጋ ቁራኛ ሁና ከመሰቃየቷ በላይ አልጋ ላይ እያለች ታረግዛለች፡፡ በዚህ ስበብ እንድትገደል በቤተክርስቲያን ሳይቀር ማህበረሰቡ ይፎክራል፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር መንክር የተወለደው፡፡ አያቱ በልጃቸው ላይ የታወጀው የሞት አዋጅ ለመመልከት ወኔ ስላልነበራቸው ወኔ ስላልነበራቸው መንክርን ይዘው ወደ አዴስ አበባ ተሰደዱ፡፡  መንክር ሲያድግ አባቴ አባቴ ማነው ሲል የጠይቃል፡፡ መንክረት በየሆነ ቡድን አስቴርን አሳጥቶታል፡፡ ከሁሉም የስራ ባልደረቦች ጋር ሳይግባባ ለመኖር ተጽእኖ የፈጠረበት ከእናቱ እስከ ስቴር መሞት ማህበረሰቡ ተጽእኖ ፈጥሮ አልፏል፡፡ ለዚህም ማስረጃ ከሚሰራበት የግል ቢሮው ተነስቶ ብዙ ስራተኛ ወዳለበት ክፍል ደመወዝ ተጨምሮለት  ቢመደብም ስራውን ሲለቅ እናየዋለን፡፡

የክቴም በሽተኛ በመሆኗ በእናቷ ሳይቀር እንክብካቤ ሳይሰጣት ከ35 ዓመት የአልጋ ቁራኛ ሆና ስትሰቃይ ኖራ ህክምና ሳታገኝ ህይወቷ ያለፈ ገጸ ባህሪ ናት፡፡ ትግስትም እናቷን የሆነ ቡድን ስላሳጣት የኔ የምትለው ርዕይ የሌለላት ገጸ ባህሪ ናት፡፡

## 3.2. ስነ ህይወታዊ ሞት

Westphal (1984, 102) ስነ ህይወታዊ ሞት ከሰው ልጅ ቁጥጥር ውጭ የሆነ፣ ፍጡርን ሁሉ የሚገዛ እጣ ነው፡፡ ይህ እጣ በአደጋ ይከሰታል፤ በርሃብ፣ በእርዛትና በጥማት ይመጣል፡፡

## የማቴዎስ እናት እና አባት ስነ ህይወታዊ ሞት

የማቲዎስ አባት እና እናት በጣም ይዋደዱ ነበር፡፡ የኦጋዴን ጦርነት ተጠናቆ ተመለሱ፡፡ እንደገና በመጨረሻ ፋታ ወደማይሰጠው የሱማሌ ጦርነት ተነስቶ አባቱ ወደሀረርጌ ክፍለ ሀጋር ዘመተ፡፡ እናቱም ወደ አዲስ አበባ የተመለሰቸው ጦርነቱ  ከተጠናቀቀ በኋላ ነበር፡፡ አባቱ ምን እንደሆነ አታውቅም ነበር፡፡ ከድል በኋላ የኢትዮጵያ ወታደሮች ያሉበት የፊት ግንባር ሁሉ

አሰሰች፣ ውዷ የለም፡፡ በእኔ እና በእሱ መካከል የሚገባ ምን አምላክ ነው? በሚል ዘወትር እግዚአብሔርን ትነቅፍ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ኖሮዋ የምናኔ አይነት ሆነ፡፡ ቤታችን አከራይታ ሌላ ቤት ተከራየች፡፡ አክስቴ ደውላ ስለኔ ስታነሳላት እሱን እንደፈለግሽው አድርጊው ትላት ነበር፡፡ አባቴ ድንገት መጣ፡፡ የአክስቴ ቤት ሲመጣ ግርማ ሞገሱ ተገፎ ቅልጥም ብቻ ሆኖ ስለነበር ማንም ያወቀው አልነበረም፡፡ አይኖቹ እንደጥንቱ የተረጋጉ አልነበሩም፡፡ ስሜቱ የደፈረሰና እርካብ ያልተቆናጠጠ ሆኗል፡፡ እናቴ አክስቴን በዘዴ ይዛት መጣች፡፡ ከዚህ በኋላ የነበረው የወላጆቼ ህይወት ምን ሊባለር እንደሚችል ግራ የሚያጋባ አይነት ነው፡፡ እናቴ አባቴን የብቸዋ ነጥላ ለማድረግ እጅግ ትጥራለች፡፡ አባቴ ደግሞ ሰው የበዛበት አካባቢ ስቅሉን ስቶ መጨፈርና ድስኩር ማድረግ እነደወግ ያዘው፡፡ ወገኖቸ ከእናንተ መካከል ከሰው እንዲነጠል የተገደደ አለ? እኔ ግን ለአስር ዓመት ከአንድ ቤት ተዘጋብኝ፡፡ ወደቤት ከመጣ በኋላ ደጃፍ እንዳይዘጋ አጥብቆ ይከላከላል፡፡ “የለም ዳግም በእኔ ላይ በር ከመዘጋቱ አስቀድሞ ራሴን አጠፋለሁ፡፡” እናቴ በወዳጆቹ አስመከረችው፡፡ እሽ አሁን እንጫወት፣ ስንጨፍር እንደር፣ መለያየት ምን አባቱ፡፡ ማታ መልሶ አይኑን የእሳት ላንቃ አስመስሎ ከእናቴ ላይ ያፈጣል፡፡ “በር አትቆልፊ፤ ስንት አመት እንደምትተኝ ታውቂያለሽ? የእድሜሽን አንድ ሶስተኛ! ስልሳ አመት ኖርሽ እንበል፣ ሃያ ዓመቱ እንቅልፍና ምሽት፡፡ ቤትሽን በራስሽ ላይ ከዘጋሽ ሀያ አመት እስር በራስሽ ላይ ፈረድሽ ማለት ነው፡፡

“ታዲያ ሌሊት በር ከፍተን ይዝረፉን፣ ይግደሉን?” እናቴ የጥንቱን አባቴን መስላለች፡፡ ለምንም አይነት ንፋስ እንደማይናወጽ ውቅያኖስ፡፡ “እራስ ላይ ከርችሞ ሃያ አመት እራስን ከማሰር በሰው መዘርፍ፣ በሰው መገደል ፀጋ ነው፡፡ አትዝጊ አትዝጊ ልውጣበት፡፡ አልጋየን ስጭኝ ከውጭ አነጥፋለሁ! በቃ!”

“ተው አካል- ተው!”

“እንደውም ሱማል እንዲህ ይላል- ‘ናጋሃ ዋቃ ዬ ሊዳታ ካሳር ሲቃቶ ኢዮ ሲርቲድ ቦጋቶ› ምን ማለት መሰለሽ? የሴት መጥፎ ማን ነች ቢሉ ያለጊዜ የምትተኛ…’ እውነት ነው! እንደውም …” በመጨረሻ ግድሏት፣ ሞተ፡፡ (ቅበላ፣2009፣ 42)

ከዚህ ትረካ የምንረዳው ይህ የማቴዎስ እናት እና አባት ምንም እንኳን ቢዋደዱና ፍቅራቸው እስከጦር ሜዳ ዘልቆ የነበረ ቢሆንም በመጨረሻ ሚስቱን ገድሎ ራሱን ማጥፋቱ የሁለቱን ከሰው ልጅ ቁጥጥር ውጭ የሆነ ስነ ህይወታዊ ሞት ያሳያል፡፡

በተጨማሪም የማቴወስ አባት ገድሎ ሟች (suicidal murderer) ገጸ ባህሪ ነው ማለት እንችላለን፡፡ ሌስተርና ሌስተር (1971, 58-59) ስለገድሎ ሟችና ገድሎ ሟችነት የሚከተለውን ይላሉ፤

> The suicidal murderers did not seem to have killed themselves in order to escape punishement for the previouse killing. In many cases, the suicide seemed to have motivated by despair rather than hostility…. The suicide might then wish to rejoin the person he has killed and attempt to do so by means of his own death.

በቀጣዩ ጥቅስ ዌስትፋል እንደሚለው፤ የፈጸሙትን ወንጀል ህሊና ካመነ፣ ልብ ከተቀበለ በገዳይ አንደበት የሟች ድምጽ ይመላለሳል፤ (Guilt is a kind of echo effect; for when that voice resounds off the walls of the self's inner life it has been transformed into the self's own voice) (81-82):: ለዚህም ማሳያ የሚሆነው የማቴዎስ አባት ሚስቱን በመግደሉ የፈጸመው ወንጅል ህሊናው ስላመነ የሟች ሚስቱ በአንደበቱ እየሰማ ሰላሙን በመንሳቱ ራሱን ሲያጠፋ እናያለን፡፡

"አባትህ እናትህን ገድሏት የሞተው ለምንድን ነው?" …

"ስለሚያፈቅራት…ስለምታፈቅረው"

"አይደለም! ደፋር ስለሆነና ፍላጎቱን በምርጫ ስላላሳከረው ነው፡፡ ምርጫው እናትህ ነበረች፡፡ እሷ ደግሞ ጥላው ለመሄድ ተነሳች፡፡ (ቅበላ፣2009፣144)

ከዚህ ትረካ የምንረዳው የማቴዎስ አባት ፍላጎቱን ስላልተቀበለቻውና ጥላው ለመሄድ ስትነሳ እናቱን ገድሏት ራሱን መጥፋቱን ያሳየናል፡፡

ለማቴዎስ እናትና አባት ሞት ምክንያት የሆነው የማቴዎስ እናት አባቱን ጥለው ልትሄድ በመሆኑ ካለእሷ መኖር ስለማይችል እናቱን ግድሎ ራሱን አጠፋ፡፡ ራሱን ያጠፋው በድርጊቱ በመጸጸቱና ያለእሷ መኖር ስለማይችል ነው ማለት ይቻላል፡፡

የማቴዎስ አባት ሞት በማቴዎስ ህይወት ላይ ከፍተኛ የሆነ ተፅዕኖ ማለትም፣ ስድት፣ ባይተዋርነት፣ ርዕይ አልባ እንዲሆን ተፅዕኖ ከማሳደሩ በላይ አባቱ በእናቱ ላይ የፈጸመውን ድርጊት፣ ግድያ አሱም ሶረኔ ላይ ሲደግመው ያሳያል፡፡ ይህን ሁኔታ ነው ቴዎድሮስ

(2001፣151)፣ "የእያንዳንዱ ገጸባህሪያት ሞት ቢያንስ የአንዱን የኑሮ ፈለግ ያስታል፤ የህይወትን ፍቺ እየነጠቀ፣ ለፍፁማዊ ባይተዋርነት ይዳርጋል።" የሚለው።

## የየክቴ ስነ ህይወታዊ ሞት

> የፊት ለፊቱ መብራት ወደጓዳ እንዲገባ አድርጌ መጋረጃውን ገለጥ ሳደርገው የክቴን አየኋት። እንቅልፍ ሸሮው አድርጎ የወሰዳት ትመስላለች። እንቅልፍ ግን አልነበረም። ወደግራ ጎኗ ገደድ እንዳለች እግሮቿ ተዘርግተው የውስጥ እግሯ የባቄላ ፍንካች መስሎ ይታያል። ነጠላ ጋቢ ከወገቧ በታች ለብሳ አንጓቸው ተጣመው የደረቁ እጆቿ … እንባየ መጣ። (ቅባላ፣ 2009፣ 56)

ከላይ ካለው ትረካ የምንረዳው የክቴ ስነ ህይወታዊ  ሞት ያሳያል። እንቅልፍ የወሰዳት ትመስላልች  ግን አይደለም ማለት መሞቷን ያስረዳል።

> አይጥ ነክስ አድረጓት መሰለኝ አለች አክስቴ ፊቷን ላለማየት ፊቷን አዙራ። ምኗን ይሆን… የምሆነው አጣሁ የተቆለመመው እግሮቿ እስከ ቋንጆዋ ድረስ ስጋቸው ተመልምሎ ተበልቷል። ጨኸት ብቻ ሆነ። ከ35 ዓመት እስር ቤቱ ወጥታ ሆስፒታል ሳትደርስ ህይወቷ አለፈ። (ቅበላ፣ 2009፣ 56-57)

የክቴ የአክስቴ ሶስተኛ ልጅ ናት። ከተወለደች ከዚች ጓዳ ወጥታ አታውቅም። ዘወትር ግድግዳ በመደገፍ ነው ተቀምጣ የምትውል። እንደሞፈር እንጨት ጎብጠው የደረቁ እጆቿ ስለማይታዘዙላት እኔን ስታይ በአይኖቿ ትዳብሰኛለች። ድምጽ ስትሰማ ሰው ይናፍቃት ይሆናል። ሰው-ሰው-ሰው። ሰው ማጣት፣ ሰው መራብ። ከሁሉም የሚከፋ… ሰው መነፈግ፣ ከሰው መታጠር፣ ከሰው መሸፈን… መተንፈስ አቃተኝ ወጣሁ።

ይህ ከላይ ካለው ሀሳብ ለ35 ዓመት በአልጋ ቁራኛነት ስትሰቃይ የነበረችዉ ግዞተኛዋ የክቴ በመጨረሻ ስነ ህይወታዊ ሞትን የሞተች ገጸ ባህሪ መሆኗን ያሳያል።

ለየክቴ ሞት ሰበቡ የእናቷ የእንክብካቤ ችግር ይመስለኛል። የክቴ ለረጅም ዓመታት በሽተኛ በመሆኗ ሰው እንዳያይ እንኳን ለብቸዋ የምትኖርበት ክፍል ከመስጠቷ በላይ ስትታመም ወደህክም አትወስዳትም ነበር። ከዚህ በተጨማሪም ታማ ከተኛችበት ክፍል ሬሳውንም አይጥ ሲበላት ምንም አይደንቃት ነበር። ከዚህ በላይም መንከባከብ ባትችል በሌሎች ድጋፍ እንዲደረግላትና መኖሯንና መታመሟን ሎሎች እንዳያውቁት በማድረግ ጊዜውን ያልጠበቀ ሟች እንድትሆን አድርጋታለች።

## የማቴዎስ ስነ ህይወታዊ ሞት

ማቴዎስ ገና የአምስት አመት ልጅ እያለ የእናትና የአባቱን ፍቅር ሳይጨርስ በእናቱ ሞት ምክንያት ከአክስቱ ጋር መኖር የጀመረ ገጸ ባህሪ ነው፡፡ ሶረኔን ያፈቅራታል፡፡ ሶረኔ ደግሞ መንክርን ትወደዋለች፡፡ "ማቴዎስ በሚቀጥለው ቀን ሶረኔን ገድሏት ራሱን አጠፋ፡፡" (ቅበላ፣2009፣144) ከዚህ ላይ ማቴዎስ ገራገር አለመሆኑን ነው የምንረዳው፡፡ የጥላቻ አሟሟት የፍቅር ቀለም መቀባት መፈለጉን ያሳያል፡፡ ጅምር ልቦለዱ የሚያሰግረውን የፍቅር ታሪክ መደምደሚያ ለማድረግም እልህ ተጋብቷል፡፡ ለዚህም እልህ ሶረኔ ጭዳ ሆነች፡፡

ማቲዎስ አብሮ የመኖርና የመቀላቀል፣ እኔ የሚለዉ አስተሳሰብ ተቀይሮ እኛ የሚለዉ አስተሳሰብ እንዲነግስ ከመፈለግና በከንቱ ምኞትና ሃሳብ ከመዋተት በዘለለ ይህን ሃሳቡን ሲኖረዉ አይታይም፡፡ እንዲያዉም ይህ የሚያሳየዉ የሆነ ሃይል መጥቶ አንድ ሁኑ ተቀላቀሉ፣ በጋራ ኑሩ የሚል መለከት አስኪነፋ የሚጠብቅ አይነት ገጸ ባህሪ ነዉ፡፡ ስለፍቅርም ቢሆን ሰዉን እወዳለሁ፣ በሰዉ ፍቅር ወድቄያለሁ ብሎ የሚያስብ እንጅ በሚለዉ ፍቅር ዉስጥ የሚኖር ገጸ ባህሪይ አይደለም፡፡ ይህንንም በተግባር ለማሳየት እናቱ የአባቱን ፍቅር እንዳያገኝ የከለከለችዉ ስለሚመስለዉ በጣም እንደሚጠላት ይናገራል፡፡ የአክስቱን ልጅ ኩንየን ብር ሰጥቶ ከቤት እንድትኮበልል አደረገ፡፡ በታሪኩ የመጨረሻ ክፍልም በጣም አፈቅራታለሁ ብሎ የሚናገርላትን ሶረኔን ገድሎ እራሱን ሲያጠፋ እንመለከታለን፡፡ ታዲያ የዚህ አይነቱ ተግባር እዴት ብሎ ነዉ ለሰዉ ልጅ ያለዉን ፍቅር የሚያሳይ እራሱንስ እንደሃዋርያ የሚያስቆጥር፡፡ ይህ በትክክል የሚያሳየዉ አስተሳሰቡም ሆነ ስብእናዉ ከሌሎች የለየዉ መሆኑን፣ በዉስጡ ያለዉን ለራስ ታማኝ አለመሆንና እራስን የመጥላት ስሜት ለማጥፋት የሚያደርገዉ ያልተገናዘበና ደመነፍሳዊ እቅስቃሴ ነዉ፡፡

በአጠቃላይ ማቴዎስ ርዕዩ የተነጠቀ፣ ተስፋው የተቀበጸ፣ ግዞተኛ ከመሆኑ በላይ ከተለመው አንዱንም ሳያሳከ የሚወዳትን ሶረኔን ገድሎ ራሱንም በማጥፋት ስነህይወታዊ ሞትን የተቋደሰ ገጸባህሪ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ማቴዎስ እንደ አባቱ ሶረኔን መግደሉ እነ ሌስተርና ሌስተር (1971, 58-59) አባባል ገድሎ ሟች (suicidal murderers) ነው፡፡

በኢማይል ደርኪሄም (Durkheim, 1963, 44) ስለራስ ግድያ የሚሉት ይህኑኑ ነው፤

“The term suicide is applied to all cases death resulting directly, or indirectly, from a positive or negative act of the victim himself, which he knows will produce this result.”

የሰው ልጅ በገዛ ፈቃዱ የሚፈጽመው ጉስቁልና፣ ድቀት ወይም በጥቅሉ ስነ ህይወታዊ ጥንካሬውን ሚሸረሽር የትኛውም ተግባር(a voluntary elimination of biological fitness) ከራስ ጉዳት፣ ከራስ ግድያ ጋር እጅግ ጥብቅ ዝምድና አለው፡፡ በደርኪሄም እምነት፣ ራስን ከምግብና ከውሃ ማቀብ፣ በሽጉጥ የገዛ አናትን እንደመንደል፣ በስለት ደም ስርን እንደመበጠስ፣ መርዝ እንደመጨለጥ፣ ከፎቅ እንደመወርወር ወዘተ. ሁሉ ራስን የመግደያ ዘዴ ነው፡፡ (“Refusal to take food is as suidal sa self-destruction bay a danger or fire arm” [ibid])፡፡

ማቴዎስም ራሱን መግደሉ አድማው በማን ላይ ነው? አለምን አልጠላም፤ አለምን አልናቀም፡፡ ዳሩ ግን፣ አለም ገፍቶታል፤ አለም ፍቅርና ተስፋ ነስቶታል፡፡

የማቴዎስ ሞቱ ምክንያት የኔ የሚለውን ሁሉን ነገር ማጣቱ ነው፡፡ ሁሉም ነገር ማጣቱን ከዚህ በታች ባለው የልቦለዱ ታሪክ መረዳት ይቻላል፡፡

“ሁልን ነገር አጣሁ፡፡ ትናንት ገንዘብ ወስጄ ለአክስቴ ብሰጣት አልቀበልም አለችኝ፡፡ ዳግም እኔን ማየት እንደማትፈልግ ገባኝ፡፡ ትናንት የመጨረሻውን ገፅ ፅፌ ሁሉም ነገር ሳይጠናቀቅ ቆመ፡፡ ትናንት ሶረኔ ሁለተኛ አጠገቤ አትድረስ አለችኝ፡፡ ትናንት ሦስቴ ተቼነከርኩ፡፡” (ቅበላ፣ 2009፣ 143)

## የአስቴር ስነህይወታዊ ሞት

አስቴር ትምህርት ከትግል በኂላ ብላ የኮሌጅ ትምህርቷን አቋርጣ ኢሃፓ አባል ነበረች፡፡ “… ድንገት በሩን ከፍቼ እስቲ ተዋት ማለት አሰኘኝ… አንተ ልጅ ተኩስ ጭንቅላቴ ውስጥ አለ ትለኛለች፡፡ (ቅበላ፣2009፣127)፡፡

‘በቃ፣ ቃል በገባህልኝ ቃል መሰረት እሱን ልቀቀው’ አለቻው ተጫኔን፡፡ በእኔ ተዋውላ ራሷን አሳልፋ እንደሰጠችገባኝ፡፡ ለምን? ለምን? ለምን? ‘ና እስኪ’ ብላ አጠገቧ ግድግዳውን አስደግፋ አስቀመጠችኝ፡፡ የምሆነውን አጥቼአለሁ፡፡ ‘አይኖችህን ልያቸው፤ ታድለው ልጄን አድጋ ያዩዋታል፡፡ ስትል ለእኔ በሚሰማ ድምጽ አጉለመለመች፡፡ (ቅበላ፣2009፣131)፡፡

አስቴር የኮሌጅ ትምህርቷንም አቋርጣ ወደ ኢሃፓ ትግል ተቀላቅላ ብትቀይም የማይቀረውን ሁሉንም ፍጡር የሚገዛውን ስነህይወታዊ ሞት ሙታለች፡፡ አስቴር የምትሳሳላትን አንድ ልጇን፣ ትግስትን ጥላ በዱር በገደሉ ለትግል ብላ ስትማስን ኑራ በመጨረሻ "በእኔ ተዋውላ ራሷን አሳልፋ እንደሰጠች ገባኝ" (ቅበላ፣2009፣131)፡፡ ሲል መንክር የአስቴርን መሞትን ይነግረናል፡፡ "…ታድለው ልጇን አድገው ያዩዋታል" ማለቷም ስለምትሞት ልጇን በአይኗ ማየት አለመቻሏን መናገሯ ነው፡፡

"የመጨረሻውን ብቻ ንገረኝ አባብየ እናቴን አገኛት? አግኝቶ አሰቃያት? ገደላት?"

"አዎ" (ቅበላ፣2009፣131)፡፡

ከላይ ካለው ከትግስትና ከመንክር ምልልስ የምንረዳው የትግስትን እናት የሞት ሰበብ ተጫኔ መሆኑ ነው፡፡

የአስቴር ሞትም በመንክር እና በትግስት ህይወት ውስጥ ተፅእኖ አሳድሯል፡፡ ቴዎድሮስ (2001፣151) እንዳለው፣ "የእያንዳንዱ ገጸባህሪያት ሞት ቢያንስ የአንዱን የኑሮ ፈለግ ያስታል፤ የህይወትን ፍቺ እየነጠቀ፣ ለፍፁማዊ ባይተዋርነት እየዳረገ፡፡" ያልፋል፡፡ የአስቴርም ሞት ለመንክርና ለትግስት የኑሮ ፈለጋቸውን ከማሳቱ በላይ ርዕይ አልባነት በህይወታቸው ላይ ጥሎ አልፏል፡፡

## የሶረኔ ስነ ህይወታዊ ሞት

"ወይዘሮ ሶረኔ አርፋለች፡፡"

"አረፍት?"

"አ-ይ፤ ማለቴ ከዚህ አለም በሞት…" (ቅበላ፣2009፣159)፡፡ ከዚህ ምልልስ የምንረዳው ሶረኔ መሞቷን ነው፡፡ ሞቷም ስነ ህይወታዊ ሞት ነው፡፡

"ምን ሆና ሞተች?"

"ተገደለች"

"ማን ገደላት?"

"የምታውቂው አልመሰለኝም፡፡ አንድ…"ዝም አለና "እኛ መስሪያ ቤት ደራሲ አለ ብዬሽ ነበር?"

"አዎ"

"እ-ሱ እሱ ገደላት" አለና ኪሱን እየፈታተሸ "ይሄን ደብዳቤ ጽፎ እሱም ራሱን አጥፍቷል። (ቅበላ፣2009፣165)። ሶረኔን መግደሉ እነ ሌስተርና ሌስተር (1971, 58-59) አባባል ማቴዎስን ገድሎ ሟች (suicidal murderers) የደራሲ ፍጡር ነው። ሶረኔን ደግሞ The suicide murderers ናት ማለት ይቻላል።

ሶረኔ ከማቴዎስ ፍቅርን እስከ መቃብር ስትጠብቅ በአቋራጭ በማቴዎስ የተቀጠፈች የደራሲው ፍጡር ነች።

## የመንክር እናት ስነህይወታዊ ሞት

የመንክር እናት ከአንገቷ በላይ በጣም ቆንጆ ነበረች። ... ከትልቅ ቤት ጎን ጎተራ የመሰለች ሌላ ቤት ተቀለሰላትና ከዚያ ተከተተች። በጋብቻ በኩል ዘልለዋት ያገቡት ታናናሾቿ ሳይጸንሱ እሷ ከዚያው ሆና አረገዘች። እና ድፍን እንፍራንዝ ተወያየበት። ወሬው ድፍን ደንቢያን ወረረ። አውሬ ነው ተባለ አሉ። ቀኝ አማች ሊያሥፈጁን! አንዳንዴ ከሆነ በላይ ከጎናቸው ባያርቋት ምን አለበት? ባዶ ቤት አግኝቶ ተጫወተባታ! ተባለ። መንክር ተወለደ። የሰዎች ውሉ ያልለየ ጨኸት በእናቱ ላይ አመጸ። ቄስ ናቸው። አባ ፍቅሔር ሳይቀር "ጠበል አያረክሰው፣ ግዝት አይገስጸው" ይላሉ። (ቅበላ፣ 2009፣ 90-91)።

አባ "ሱባኤ ንጽህና ይጠይቃል። ከጉድፋችሁ ንጹ! እግዚአብሔር የማይፈቅደውን ከመካከላችሁ አስወግዱ። በርኩስ መንፈስ የተዘራን መጥፎ ዘር የእግዚአብሔር እጆች ሆይ!" (ቅበላ፣2009፣92)።

በአጠቃላይ በታሪኩ እንደምንመከለተዉ የመንክር እናት ትኖርበት የነበረዉ ማህበረሰብ የራሱን እሴት እና ስነምግባር ፈጥሯል። የመንክር እናት ማህበረሰቡ የሳይጣን ልክፍት በሚለዉ ደዌ እየተሰቃየች የዝንተ ዓለም የአልጋ ቁራኛ ሆና የምትኖር ናት። ሰዎች ካላነሷት የማትነሳ፣ ካላበሏት የማትበላና በሰዎች እገዛ ካልሆነ የማትንቀሳቀስ ናት። ይህ ሳያንሳት ቀድመዋት የተዳሩት ታናናሾቿ ሳይጸንሱ እሷ አልጋዋ ላይ እንዳለች አረገዘች። ከእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ይህ ክስተት ታዲያ ማህበረሰቡ የፈጠረዉን ስነምግባር የበለጠ ያጎላዋል። ዲያቢሎስ እንዲህ አድርጎ ያስቀመጣት ሳያንስ አስረገዛት በሚል አጉል እምነት እንድትወገዝ ብሎም እንድትወገድ ከእምነት ተቋማት ሳይቀር እንድትሞት ተሰብኮ በመጨረሻ ሥነ ህይወታዊ ሞትን ቀምሳለች።

የመንክርን እናት የገደላት ማህበረሰቡ ነው። የመንክር እናት በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ ሆና በማርገዟ ከማህበረሰቡ አልፎ በሀይማኖት አባቶች ሳይቀር "ከጉድፋችሁ ንጹ! እግዚአብሔር

የማይፈቅደውን ከመካከላችሁ አስወግዱ፡፡" (ቅበላ፣ 2009) በማለት ተሰብኮ ነው በማህበረሰቡ የተገደለችው፡፡

ለመንክር እናት ሞት ሰበብ የመንክርን መወለድ ነው፡፡ የመንክር እናት በደዌ ውስጥ ሆና ከዘመዷ አርግዛ ነው መንክርን የወለደቻው፡፡ ይህ ነው የመንክርን እናት በአልጋ ቁራኛ ሆና ደዌ ዳኛ እየተሰቃየች መሆኗና በዘመዷ መደፈሯ ሳያንሳት በመህበረሰቡ እንድተገደል አብቅቷታል፡፡

ቴዎድሮስ (2001፣151) እንዳለው፣ "የእያንዳንዱ ገጸባህሪያት ሞት ቢያንስ የአንዱን የኑሮ ፈለግ ያስታል፤ የህይወትን ፍቺ እየነጠቀ፣ ለፍፁማዊ ባይተዋርነት እየዳረገ፡፡" የመንክር እናትም ሞት ለመንክርና ለአያቱ የኑሮ ፈለጋቸውን ከማሳቱ በላይ ለርዕይ አልባነት በህይወታቸው ላይ ጥሎ አልፏል፡፡

ይህ የመንክር እናት ሞት ለመንክር ህይወት ሌላ ፈተና ፈጥሮ አልፏል፡፡ መንክር የእናቱን አሟሟት አያቱ ከነገሩቸው በኋላ ማህበረሰብ የሰው ጠላት ነው ብሎ እንዲያስብ ከማድረጉም በላይ ከመጀመሪያው እስከ መጫረሻው ባላው የህይወት ዘመኑ ርዕይ አልባ የሆነ ገጸባህሪ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

በእናቱ ሞትና አመሟሟት ምክንያት ከንቱና ዉጥንቅጡ በወጣ አለም ዉስጥ እንዲኖር አድርጎታል፡፡ ህይወትን የሚኖራት እንዲሁ ያለምንም ጉጉትና ፍቅር ነዉ፡፡ በልጅነት እድሜዉ ያለ እናትና አባት እንዲያድግ ስለተገደደ በኋላ ላይም በህይወቴ ልኖረዉ የሚገባኝ ህይወት ይህ ነዉ የሚለዉ አላማም ሆነ እቅድ የለዉም፡፡ ለዛም ነዉ ገና ስምንተኛ ክፍል እያለ አስቴር ከእሷ ጋር እንዲሄድ ስትጠይቀዉ ያለምንም ማመንታት ተከትሏት ሲሄድ የምናየዉ፡፡ ለመንክር በህይወት መኖርና መሞት ትርጉማቸዉ አንድ ነዉ፡፡ ይህን ደግሞ በተለያዩ የታሪኩ ክፍሎች እናየዋለን፡፡

"ማቲዎስ መንክርን "አንተ የተረጋጋህ ሰዉ ነህ ሁሉም ነገር አለህ ሲለዉ ሁሉንም ነገር ስለማልፈልግ ነዉ ሁሉም ነገር ያለኝ የመሰለህ፡፡" (ቅበላ፣ 2009፣ 143)፡፡ ትዳር የለዉም፡፡ ስለቀጣይ ህይወቱም ምን እንደሚፈልግና እደሚያስብ ምንም ነገር ሲናገርም ሆነ ሲያደርግ አናየዉም፡፡ በህይወት መቆየትም የሚፈልገዉ ለትእግስት ሲል ብቻ እንደሆነ ይናገራል፡፡

መንክር የኢሃፓን የትግል መስመር የተቀላቀለዉ አምኖበት ሳይሆን እንዲሁ አስቴርን በመፈለግ፡፡ አስቴርን መፈለጉ ሳያዉቀዉም ቢሆንም እናቱን የመፈለግ ያክል ሆኖ ነዉ የሚሰማዉ፡፡

አጠቃላይ ስለህይወቷና አንዲት ልጅ እንዳለቻት እሷንም ሳታሳድግ ወደትግል መስመሩ እንደገባች ታጫዉተዋለች፡፡ ይህ ድርጊት ታዲያ የዉስጡን ቁስል ስለሚነካበት በአስቴር የታከመ እስኪመስለዉ ድረስ በፍጹም አስቴርን ማጣት አይፈልግም፡፡ እሷ የትእንዳለች እንዲናገር መንክር ወደ ማሰቃያ ስፍራ ይወሰዳል፡፡ በርካታ ስቃይና እንግልት እየደረሰበት በሌሎችም ላይ እያየ ምንም ቅንጣት አይሰማዉም፡፡ አጎቱ ተጫኔ እንኳ ካልተናገረ በከንቱ እንደሚገደል እየነገረዉ ምንም አይመስለዉ፡፡ ለሱ የትግል መስመሩ ሳይሆን ትልቁ ጉዳዩ አስቴር ናት፡፡ በእሱ አስራትና ሞት የሚገናኙ እናትና ልጅን እያሰበ ደስተኛ ነበር፡፡ አስቴርንና ልጇን የእሱና የእናቱ ምሳሌ አድርጎ ስሏቸዋል፡፡

"ከዚህ ምድር ላይ ያለእሷ ማንም የለኝ፡፡ መኖሬን ታግሸ የምንከላወሰዉ ለእሷ ብቻ ነዉ፡፡ ግን የኔ መኖር የተስቦ ምንጭ ሆኖባት አንተን የመሰለ ክፉ በሽታ የሚጥልባት ከሆነ ያለጥርጥር እገድልሃለሁ፡፡" (ቅበላ፣ 2009፣ 105)፡፡

ለመንክር አያትም የልጇ ሞት በህይወቷ ሌላ ጠባሳ ፈጥሯል፡፡ የመንክርን እናት በማህበረሰቡ እንድትገደል በሀይማኖት አባት ሲሰበክ በደዌ እየተሰቃየች ያለቸውን ልጅ ትታ መንክርን በመያዝ ለመሰደድ ተገዳለች፡፡ በመንክር በአያት ህይወት ላይ የፈጠረው ጉስቁልና ከስደት በላይ ነው፡፡

## 3.3. የራስ ግድያ

ደርኪሄም(1963፣ 44) እንደሚለው፤ የሰው ልጅ በገዛ ፈቃዱ የሚፈጽመው ጉስቁልና፣ ድቀት፣ ወይም በጥቅ ስነህይወታዊ ጥንካሬውን የሚሸረሽር የትኛውም ተግባር ከራስ ጉዳት ከራስ ግዲያ ጋር ጋር እጅግ ጥብቅ እዝምድና አለው፡፡ ራስን ከምግብና ከውሃ ማቀብ፣ በሽጉጥ የገዛ አናትን እንደመንደል፣ በስለት ደም ስርን እንደመበጠስ፣ መርዝ እንደመጨለጥ፣ ከፎቅ እንደመወርወር ወዘተ. ሁሉ ራስን የመግደያ ዘዴ ነው፡፡ የመንክር አባትም ያደረገው ይህኑን ደርኪሄም አባባል መሆኑን ከዚህ በታች ያለው ቃለ ምልልስ ያስረዳል፡፡

## የመንክር አባት ራስ ግድያ

"አባቴ ማን ነው?" አለ "ዳቢሎስ ነው?"

"አይደለም" አያቱ በረጅም ተነፈሱ። በእርጅና በማይንቀሳቀስ ደረት ውስጥ ይህ ሁሉ አየር መኖሩ አስደነቀው። "አንድ ዘመዴ ነው። **እሱም ይኸን ከሰራ በኋላ መንኖ ዘወትር ራሱን በለበቅ እየገረፈ ከገዳም ይኖር ነበር።"** (ቅበላ፣2009፣92 አፅንዖቱ የኔ ነው)።

የመንክር አባት በአምላክ ተጠርቶ፣ እምነት ስቦት ወደ ገዳም አልሄደም። በገዳም ምግብ አይበላም፤ ውሃ አይጠጣም። ጠኔ ነው፤ ጥም ነው። የገጸ ባህሪው የገዳም አምሮት፣ የእምነት ቅንአት አላነቃውም። አለምን አልጠላም፣ አለምን አልናቀም። ዳሩ ግን አለም ግፍቶታል፣ አለም ፍቅር እና ተስፋ ነስቷቸዋል። ከሲኦል ፍራቻ ይልቅ የህይወት ጥላቻ ነው የመንክርን አባት ወደ ገዳም እንዲገባ ያስገደደው። ሰማያዊ ተስፋው ከምድራዊ ድቀቱ ልቆ አላማለለውም። ከሁለት ያጣ ላለመሆን ነው ሲል ነው የፈጣን ሞት አዕምሮቱን የገደበው። ይህ በጣም በህይወቱ ተስፋ የቆረጠ ገጸ ባህሪ ገዳም በመግባት በማይኮነንበት መንገድ ቴዎድሮስ(2001) እንደሚለው በረጅም የዝግታ ሞት(long and slow death) የሞት ጥሙን ይወጣል። በመሰረቱ ራስ ግድያ ከሞት ናፍቆት ይልቅ የህይወት ጥላቻ ነው ቅርቡ፤ የጠሏት ህይወት ውስጥ ተቀምጠው ከመጠበቅ እርሱ መዳለበት መሄድ።" ለዚህም ነው የመንክር አባት የጠላውን ህይወት ተቀምጦ ከመጠበቅ መደገዳም በመግባት ራሱን በለበቅ እየገረፈ በገዳም ለመኖር የወሰነው።

## የፋሲል ራስ ግድያ

በኢማይል ደርኪሄም (Durkheim, 1963, 44) ስለራስ ግድያ የሚሉት ይህኑኑ ነው፤

The term suicide is applied to all cases death resulting directly, or indirectly, from a positive or negative act of the victim himself, which he knows will produce this result.

ፋሲል አስቦበት አይደለም የሚወዳትን ትግስትን ጥሎ የጠፋው። አለም አልጠላም፤ አለም አልናቀም። ፋሲል ከሁለት ያጣ ላለመሆን ነው ትግስትን ጥሎ የኮበለለው። ለራስ ግድያ ቴዎድሮስ (2001፣ 178) በረጅም የዝግታ ሞት የሞት ጥማቸውን ይወጣሉ። ለራስ ግድያ ከሞት ናፍቆት ይልቅ የህይወት ጥላቻ ነው ቅርቡ፤ የጠሏት ህይወት ውስጥ ተቀምጠው ከመጠበቅ እሰዋ መዳለችበት መሄድ። ፋሲል የጠፋው መንክር የሚከተለውን ስላለው የጠፋው ነው፤

በዚች ሽረሪት ዘመድህ ግፊት ትግስት ላይ እያደራህ መሆኑን ደርሼበታለሁ፡፡ … እዚህ ምድር ላይ ያለሷ ማንም የለኝ፡፡ መኖሬን ታግሼ የምንከላወሰው ለእሷ ብቻ ነው፡፡ ግን የኔ መኖር የተስቦ ምንጭ ሆኖባት አንተን የመሰለ ክፉ በሽታ የሚጥልባት ከሆነ ያለጥርጥር እገድልሃለሁ፡፡ … እገድልሃለሁ ከዚህ በኋላ ለሚሆነው አስቤ አልጠነቀቅም፡፡ የትም ይሁን የት እገድልሃለሁ፡፡ አደባባይ፣ ጓዳ፣ ቤተክርስቲያን ሆነ ፍርድቤት ውስጥ ለእኔ ለውጥ አያመጣም፡፡ (ቅበላ፣2009፣104-105)፡፡

ከላይ ከልቦለዱ ታሪክ የምንረዳው ለመንክር ራስ ግድያ ሰበብ መንክር ነው፡፡ መንክር ፋሲልን ከትግስት ጋር ያለውን ሴራ ደርሸበታለሁ ስላለውና እገድልሃለው ብሎ ስላስተነቀቀው በማይፈልገው ህይወት ውስጥ ሆኖ ራሱን እንዲቀጣ አድርጎታል፡፡

የፋሲል ራስ ግድያ ለትግስት ህይወት እንደአባቷ ስለምታየው ለህይወቷ ጥላሸት አልፈጠረም ማለት አይቻልም፡፡ የአንድ ገጸረ ባህሪያት ሞት ይብዛም ይነስም በሌሎች ገጸባህሪያት ህይወት ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩ አይቀርም፡፡

እንዲሁም ፋሲል ለትግስት በፃፈው ደብዳቤ "እስከዛሬ ህይወትን እየኖርኩ ሞትን ማሰብ አላስፈላጊ እንደሆነ አምን ነበር፡፡ …ግን የሚተናነቀኝን የመኖር ፍላጎት ድል ስመታውና ሞትን የሚንቅ ወኔ ሳጠራቅም መጥቼ አይሻለለሁ፡፡ እስከዚያ ግን በክርስቶስ ስም ከእኔ ራቂ፡፡" (ቅበላ፣2009፣109-110)፡፡

በተጨማሪም "አሁንም እደግመዋለሁ፤ እኔ የማልፈለገው አንቺን አይደለም፡፡ ሞትን እንጂ፡፡ በማለት መንክር እገድልሃለሁ ስላለሁ ወደኬንያ እንደሄደና ለመንክር እንዳትነገረው በማሳሰብ፡፡" (ቅበላ፣ 2009፣ 163-164)፡፡

ከላይ ካለው የልቦለዱ ታሪክ የምንረዳው የሚወዳትን ትግስትን ትቶ ወደኬንያ የተሰደደው ስደትን መርጦትና ፈልጎት ሳይሆን መንክር እገድልሃለው ስላለው ሞትን ፈርቶ ነው፡፡ ለፋሲል የራስ ግድያ ሰበቡ መንክር መሆኑንም ያሳያል፡፡ ይህን ነው "የእያንዳንዱ ገጸባህሪያት ሞት ቢያንስ የአንዱን የኑሮ ፈለግ ያስታል፤ የህይወትን ፍቺ እየነጠቀ፣ ለፍፁማዊ ባይተዋርነት እየዳረገ፡፡" ቴዎድሮስ(2001፣151) ሚለው፡፡

## የማቴዎስ አባት ራስ ግድያ

“ታዲያ ሌሊት በር ከፍተን ይዝረፉን፣ ይግደሉን?” እናቴ የጥንቱን አባቴን መስላለች፡፡ ለምንም አይነት ንፋስ እንደማይናወጽ ውቅያኖስ፡፡ “እራስ ላይ ከርችሞ ሃያ አመት እራስን ከማሰር በሰው መዘርፍ፣ በሰው መገደል ፀጋ ነው፡፡ አትዝጊ አትዝጊ ልውጣበት፡፡ አልጋየን ስጭኝ ከውጭ አነጥፋለሁ! በቃ!”

“ተው አካል- ተው!”

… **በመጨረሻ ግድሏት፣ ሞተ፡፡** (ቅበላ፣2009፣ 42)

የማቴዎስ አባት ደርኪሄም(1963፣44) እንደሚለው፤ የሰው ልጅ በገዛ ፈቃዱ የሚፈጽመው ጉስቁልና፣ ድቀት፣ ወይም በጥቅሉ ስነህይወታዊ ጥንካሬውን የሚሸረሽር የትኛውም ተግባር ከራስ ጉዳት ከራስ ግዲያ ጋር ጋር እጅግ ጥብቅ እዝምድና አለው፡፡ የማቴዎስ አባትም ከውትድርና መልስ እስከ ሞቱ ድረስ “እራስ ላይ ከርችሞ ሃያ አመት እራስን ከማሰር በሰው መዘርፍ፣ በሰው መገደል ፀጋ ነው፡፡ አትዝጊ አትዝጊ ልውጣበት፡፡ አልጋየን ስጭኝ ከውጭ አነጥፋለሁ! በቃ!” የሚለው የማቴዎስ አባትን ራስ ግድያ ያመላክታል፡፡

### የመንክር ራስ ግድያ

በዚሁ የልብ ወለድ ታሪክ የምናገኘዉ ሌላኛዉ ገጸ ባህሪ ደግሞ የራሱን ግድያ ተጋላጭ መንክር ነዉ፡፡ መንክር ስምንተኛ ክፍል እስኪሆን ድረስ ያሳደጉት የአያቱ እህት ናቸዉ፡፡ በዚህ ቤት ዉስጥ ሲኖር ከማንም ጋር ይህ ነዉ የሚባል ቀረቤታ የሌለዉና ማንንም የማይወድ በርካታ ጊዜዉን የሚያሳልፈዉ ከብቶችን በመጠበቅ ነበር፡፡ አዲስ አበባ ልኑር እንጅ ያደኩት እንደ አንድ በገጠር እንደሚኖር ልጅ ነዉ ይላል፡፡ በዚህ ወቅት ታዲያ ይህ ነዉ የሚባል የትምህርት ቤትም ሆነ የሰፈር ጓደኛ የለዉም፡፡ በትምህርት ቤትም በየትኛዉም ክበብም ሆነ የቡድን ጉዳይ ተሳትፎ የለዉም፡፡ በዚህ ሁኔታ እያለ ነዉ መንክር ባላሰበዉና ባልጠበቀዉ መንገድ ከአስቴር ጋር የሚተዋወቀዉ፡፡

በዚህ ከንቱና ዉጥንቅጡ በወጣ አለም ዉስጥ የሚኖረዉ መንክር ህይወትን የሚኖራት እንዲሁ ያለምንም ጉጉትና ፍቅር ነዉ፡፡ በልጅነት እድሜዉ ያለ እናትና አባት እንዲያድግ ስለተገደደ በኋላ ላይም በህይወቱ ለኖረዉ የሚገባኝ ህይወት ይህ ነዉ የሚለዉ

አላማም ሆነ እቅድ የለዉም፡፡ ለዛም ነዉ ገና ስምንተኛ ክፍል እያለ አስቴር ከእሷ ጋር እንዲሄድ ስትጠይቀዉ ያለምንም ማመንታት ተከትሏት ሲሄድ የምናየዉ፡፡

አስቴር በወቅቱ የነበረዉን ፖለቲካ በመንቀፍ ትክክል ነዉ ብላ ባሰበችዉ የኢሃፓ መስመር ተሰልፋ ህዝቤን ነጻ አወጣለሁ በማለት ቆርጣ የተነሳች ሴት ናት፡፡ ይች ሴት ታዲያ ዘወትር ማታ ማታ መንክር ከሚኖርበት ቤት በመሄድ ከባለቤቷ ጋር የሚበላ ነገር እንዲያመጣ ያዙታል፡፡ ባለቤቷ ለመንክር ዘመድ ይሁን እንጅ ሁሌም መንክርን የሚያየዉ በጥላቻና በስድብ ነዉ፡፡ ተጫኔ ይባላል፡፡ ሁሌም ማታ ማታ እነዚህ ሁለት ግለሰቦች እየተደበቁ መንክር ቤት ያፈራዉን እየሰረቀ በማምጣት መመገቡ የተለመደ ተግባር ሆነ፡፡ አንድ ቀን ግን ያልተጠበቀ ነገር ይከሰታል፡፡ አስቴርና ተጫኔ እየተደበቁ የሚመገቡበት ሲፈልጉም ትንሽ እረፍት የሚያደርጉበት የሳር ሰቀላ ሌሊቱን ተቃጥሎ አደረ፡፡ በዚህም የአያቱ እህት መንክርን በመጠርጠር ሲደበድቡት አደሩ፡፡ መንክር ግን ከድብደባዉ ይልቅ ያመመዉ ምናልባት አስቴር ዉስጥ ተቃጥላ ይሆናል የሚለዉ እሳቤዉ ነዉ፡፡ ሳያዉቀዉ አስቴርን የመፈለግ እሳቤዉ እናቱን የመፈለግ ያክል ሆኖ ተሰምቶታል፡፡ በጣምም አዝኗል፡፡ በሌላኛዉ ቀን ከትምህርት ቤት ሲመለስ ድንገት አስቴርን ሲያገኛት ድጋሚ እንዳያጣት ምክንያት ሲፈልግ እያለ ከእሷ ጋር እንዲሄድ ስትጠይቀዉ ምንም ሳያመነታ አብሯት ይሄዳል፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነዉ መንክር የኢሃፓን የትግል መስመር የተቀላቀለዉ፡፡ አምኖበት ሳይሆን እንዲሁ አስቴርን በመፈለግ፡፡ አስቴርን መፈለጉ ሳያዉቀዉም ቢሆንም እናቱን የመፈለግ ያክል ሆኖ ነዉ የሚሰማዉ፡፡

በትግል መስመሩም የሚሰጠዉን ተልኮ ከፈጸመ በኋላ ሪፖርት እንኳን ሳያደርግ ክፍሉ ገብቶ ይተኛል፡፡ ይህ ሁኔታዉ አስቴርን በጣም ያስገርማታል፡፡ ከተልዕኮ መልስም እንዲህ ስትለዉ እንሰማለን፡፡

"የታጋይ ወጣት ድፍረት አለህ፡፡ ድፍረትህ ግን እንደ አንድ ታጋይ ወጣት ሁሉ ትግሉ ላይ ተስፋ ከመጣል የመነጨ አይመስለኝም፡፡ እንዲያዉም ለህይወት ዋጋ ከመንፈግ ከተስፋ መቁረጥ የምትደፍር ሆኖ ነዉ የሚሰማኝ፡፡" (ቅበላ፤2009፣ 122-123)

አጠቃላይ ስለህይወቷና አንዲት ልጅ እንዳለቻት እሷንም ሳታሳድግ ወደትግል መስመሩ እንደገባች ታጫዉተዋለች፡፡ ይህ ድርጊት ታዲያ የዉስጡን ቁስል ስለሚነካበት በአስቴር የታከመ እስኪመስለዉ ድረስ በፍጹም አስቴርን ማጣት አይፈልግም፡፡ አንድ ቀን ግን የተደበቁበት ቤት በታጣቂዎች ይከበብና አስቴር ስትፈለግ ትጠፋለች፡፡ እሷ የትእንዳለች

እንዲናገር መንክር ወደ ማሰቃያ ስፍራ ይወሰዳል ፡፡ መንክር ታዲያ አስቴር የት እንዳለች ሲጠየቅ ምንም አይነት ምላሽ አይሰጣቸዉም፡፡ በርካታ ስቃይና እንግልት እየደረሰበት በሌሎችም ላይ እያየ ምንም ቅንጣት አይሰማዉም፡፡ አጎቱ ተጫኔ እንኳ ካልተናገረ በከንቱ እንደሚገደል እየነገረዉ ምንም አይመስለዉ፡፡ ለሱ የትግል መስመሩ ሳይሆን ትልቁ ጉዳዩ አስቴር ናት፡፡ በእሱ አስራትና ሞት  የሚገናኙ እናትና ልጅን እያሰበ ደስተኛ ነበር፡፡ የእነሱ ፖለቲካ ለእሱ ምኑም አይደለም፡፡ አስቴርንና ልጇን የእሱና የእናቱ ምሳሌ አድርጎ ስሏቸዋል፡፡

"ደጋግሞ ተጫኔ መረመረኝ፡፡ አስቴር የትናት? የምድር መንቀጥቀጥ የተነሳ የሚያስመስል ዱላ፡፡ 'አስቴር የት ናት? ፣ 'አስቴር የት ናት? ...እኔ አስባለሁ፡፡"(ቅበላ፣129)

ከዚህ ላይ የምንረዳዉ ነገር ቢኖር የመጀመሪያዉ መንክር ይህ ነዉ የሚለዉና የሚያጓጓዉ ነገር በህይወቱ አለመኖሩን ነዉ፡፡ ለመኖሬ ተስፋ ያላትን አስቴርንም አንድ ቡድን ሊያጠፋት እንደተቃረበ ያዉቃል ይህንን ለመታገል ታዲያ እራሱን ለመስዋትነት ሲያቀርብ እናየዋለን፡፡

"ተጫኔ በእኔ ሁኔታ ታክቷል 'አንተ እንከፍ! በከንቱ መሞትህ ነዉ፡፡ በቅርብ ጊዜ ተወስደህ ትገደላህ' አለኝ፡፡ ግድ አልነበረኝም፡፡ በእኔ ሞት የሚተያዩ እናትና ልጆች አሉ፡፡"

ለመንክር በህይወት መኖርና መሞት ትርጉማቸዉ አንድ ነዉ፡፡ ይህን ደግሞ በተለያዩ የታሪኩ ክፍሎች እናየዋለን፡፡ አሰቴርም በበኩሏ እሷን ለመያዝ መንክርን መያዣ እንዳደረጉት ስለምታዉቅ እራሷን አሳልፋ ስትሰጥ እናያለን፡፡ በዚህ መንክር በጣም ይበሳጫል፡፡ ግን ደግሞ አብሮ ከሷ ጋር እንዳይሞት መኖሩ ለአስቴር ትልቅ ዋጋ እዳለዉ ያምናል እሱም የአስቴር ልጅ ትእግስት ናት፡፡ ለዚህም ነዉ አስራ ሁለት  አመት በበዓድ ሃገር ሲንከራተት ቆይቶ በወቅቱ የነበረዉ አገዛዝ ሲወድቅ ወደ ሃገር ቤት የተመለሰዉ፡፡

መንክር ከተመለሰ በኋላም አስቴር የጣለችበትን አደራ ለመወጣት መኖሩን ታግሶ ትእግስት ትክክለኛ ማንነቷን እንድታዉቅ ትክክለኛ ጊዜዉ እስኪደርስ በትእግስትና በተስፋ ሲጠብቅ እናየዋለን፡፡

ማቲዎስ መንክርን "አንተ የተረጋጋህ ሰዉ ነህ ሁሉም ነገር አለህ ሲለዉ ሁሉንም ነገር ስለማልፈልግ ነዉ ሁሉም ነገር ያለኝ የመሰለህ፡፡" (ቅበላ፣ 2009፣143)

ከዚህ ንግግሩ የምንረዳዉ መንክር ከዚች ምድርና ከንሮዋ ምንም ነገር እንደማይፈልግ ያሳየናል፡፡ ትዳር የለዉም፡፡ ስለቀጣይ ህይወቱም ምን እንደሚፈልግና እደሚያስብ ምንም ነገር ሲናገርም ሆነ ሲያደርግ አናየዉም፡፡ በህይወት መቆየትም የሚፈልገዉ ለትእግስት ሲል ብቻ እንደሆነ ይናገራል፡፡

"ከዚህ ምድር ላይ ያለእሷ ማንም የለኝ፡፡ መኖሬን ታግሸ የምንከላወሰዉ ለእሷ ብቻ ነዉ፡፡ግን የኔ መኖር የተስቦ ምንጭ ሆኖባት አንተን የመሰለ ክፉ በሽታ የሚጥልባት ከሆነ ያለጥርጥር እገድልሃለሁ፡፡" (ቅበላ፣ 2009፣105)

መንክር ከትእግስት ዉጭ ለእሱ ህይወት ምንኑም እንዳልሆነች አበክሮ ይናገራል፡፡ በከንቱነት ዉስጥ ሆኖ ተስፋ የሚያደርገዉና በህይወት ለመቆየቱ የሙጥኝ ያለዉ ትእግስትን መሆኑ በተደጋጋሚ በታሪኩ ሲናገር ይደመጣል፡፡ እንደነገረ ህላዌ እሳቤ ይህ የሚያሳየን ሰዎች በህይወታቸዉ ትርጉምን የሚያገኙት ትርጉም አልባ በሆነ ህልዉናቸዉ በሚያደርጉት ያልተቋረጠ ትግል ነዉ፡፡ ሪቻርድ ቴለር (በዴል ጃክዌ ፣ 2001) ለዚህም ነዉ መንክር ትርጉም በሌለዉ አለም ዉስጥ እየኖረ የህይወት ትርጉምን ለማግኘት ትእግስትን የሙጥኝ ሲል የምናየዉ ብሎም በህይወቱ ብዙ ተስፋ አስቆራጪራጭ ሁኔታዎች እየገጠሙት መኖሩን ታግሶ ለመኖር ሲሞክር የምንመለከተዉ፡፡

በአጠቃላይ ከመንክር ታሪክ የምንረዳውም ይህንን ነው፡፡ ደርኪሄም (1963፣ 44) እንደሚለው፤ የሰው ልጅ በገዛ ፈቃዱ የሚፈጽመው ጉስቁልና፣ ድቀት፣ ወይም በጥቅሉ ስነህይወታዊ ጥንካሬውን የሚሸረሽር የትኛውም ተግባር ከራስ ጉዳት ከራስ ግዲያ ጋር ጋር እጅግ ጥብቅ እዝምድና አለው፡፡ የመንክርን የራስ ግድያ ነው፡፡ መንክር የኔ የሚለው ምንም የለውም፡፡ በትግል መስመሩም የሚሰጠዉን ተልኮ የሚፈጽመው ለትግሉ መሳካትና ለእሱ ብሎ አይደለም፡፡ መንክር ሁሌም ማታ ማታ ለእነአስቴር እየተደበቁ መንክር ቤት ያፈራዉን እየሰረቀ በማምጣት የሚመግበው ለእሱ ብሎ አይደልም፡፡ እነ አስቴር እረፍት የሚያደርጉበት የሳር ሰቀላ ሌሊቱን ተቃጥሎ በማደሩ የአያቱ እህት መንክርን በመጠርጠር ሲደበድቡትና አስቴር የት እንደሄደች እንዲናገርና እምደሚገሉት ሲደበድቡት የማይነገረው ለእሱ ብሎ አይደልም፡፡ መንክር ግን ከድብደባዉ ይልቅ ያመመዉ ምናልባት አስቴር ዉስጥ ተቃጥላ ይሆናል የሚለዉ እሳቤዉ ነዉ፡፡ ለመንክር ሞትና ህይወት አንድ ናቸው፡፡ መንክር በህይወት ዘመኑ ራሱን ሲገድል የኖረ ገጸ ባህሪ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህን ነው ደርኪሄም(1963፣44) የሰው ልጅ በገዛ ፈቃዱ የሚፈጽመው

ጉስቁልና፣ ድቀት፣ ወይም በጥቅሉ ስነህይወታዊ ጥንካሬውን የሚሸረሽር የትኛውም ተግባር ከራስ ጉዳት ከራስ ግዲያ ጋር ጋር እጅግ ጥብቅ እዝምድና አለው የሚለው፡፡

## 3.4. ጊዜውን ያልጠበቀ ሞት

በአለማየሁ ገላጋይ ቅበላ ረጅም ልቦለድ ሁሉም ገጸ ባህሪያት ጊዜውን የጠበቀ ሞት የሞተ ገጸ ባህሪ የለም ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ገጸባህሪያት በህይወት አልነው በዩኒቨርስ ውጥ ለመገኘታቸው ምክንያት የሆነውን ታላቅ ተግባር በማከናወን የተጋዳሊነትን ግዳጅ በመፈጸም ማይልስ እንደለው በጥበብ  ኖረው በጥበብ ማለፍ ስላልቻሉ ነው፡፡

Miles (1991፣ 202) እንዳለው፤ አንድ ሰው በህይወት አልነውም በዩኒቨርስ ውስጥ ለመገኘቱ ምክንያት የሆነውን ታላቅ ተግባር በማከናወን ወይም የጀግንነትን፣ የተጋዳሊነትን ግዳጅ በመፈጸም በጥበብ ኖሮ በጥበብ ማለፍ ካልቻለ፣ ሞቱ ጊዜውን ያልጠበቀ ሞት ነው፡፡

### የማቴዎስ ጊዜውን ያልጠበቀ ሞት

ማቲዎስ ገና በ5 ዓመት እድሜዉ ከእናትና ከአባቱ ተነጥሎ ከአክስቱ ጋር እንዲኖር የተፈረደበት ሲሆን ከእናትና አባቱ ጋር እያለም የእናት ፍቅር የሚባለዉን ነገር አይቶት እንደማያዉቅ እና ይባስ ብሎም እናቱ የአባቱን ፍቅር እንዳያጣጥም እንቅፋት ትሆንበት እንደነበር ይተርክልናል፡፡ ታዲያ ማቲዎስ እንኳንም የዕናቱን ፍቅር ሊያገኝ  ይቅርና የአባቱን ፍቅር እንኳን እንዳያገኝ ደንቃራ ትሆንበት ነበር፡፡ ሁል ጊዜ አባቱ ከቤት ሲገባ ጭኑ ላይ ለመቀመጥ ሲፈልግ እናቱ ቀድማ ትቀመጥበታላች፡፡ ይባስ ብላ ደግሞ ማቲዎስን ዉጭ እንዲጫዎት ታደርግና አባቱን ወደዉስጥ ይዛዉ ትገባለች፡፡

ከዚህም ባለፈ የማቲዎስ እናት ገና በዚህ እድሜዉ ለአክስቱ ሰጥታዉ ከአባቱ ጋር ትሄዳለች፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ማቲዎስ ከአክስቱ ጋር መኖር ይጀምራል፡፡ በዚህን ጊዜ ታዲያ ትርፍና ተፈላጊ አይደለሁም ብሎ ስለሚያስብና የብቸኝነት ስሜት ስለሚሰማዉ ሁሌም እራሱን የሚያዋጣበት ቦታ ፍለጋ ይባዝናል፡፡ እነዚህና ሌሎች ጉዳዮች  የማቲዎስን ህይወት ፍዳ ዉስጥ ይከቱታል፡፡ ከሰዉ ጋር ለመቀላቀልና ሰዉን ላለማጣት የሚያደርገዉ እንቅስቃሴዉ የመኖር ህልዉናዉን በእጅጉ ሲፈትነዉ በልብወለድ ታሪኩ በግልጽ ይታያል፡፡

ማቲዎስ ይህ እንዲሆን አይፈልግም ምክንያቱም በልጅነቱ ከእናትና አባቱ ፍቅር ያላገኘዉ ሶስተኛ ሰዉ በመሆኑና ትርፍ ነኝ ብሎ በማሰቡ ከወላጆቹ ፍቅር ባለማግኘቱ የተፈጠረበት ችግር አሁንም ትርፍ በመሆኑ የሚያጣዉ ፍቅር እንዳለ ይሰማዋል፡፡ ለዚህም ነዉ በታሪኩ

አጋማሽ ላይ ለኩንየ ብር ሰጥጦ እንድትኮበልል ያደረገዉ፡፡ ብዙም ሳይቆይ ግን ለ35 ዓመት በአልጋ ቁራኛነት ስትሰቃይ የነበረችዉ የክቴ ከዚህ ዓለም በሞት ትለይና ያዉ ጎደሎነት በማቲዎስ ህይወት እደገና ቦታ ሲኖረዉ እናያለን፡፡

ማቲወስ ወደዚህ ምድር ሲመጣ ስለሰዉ ልጅ ፍቅር እንደተላከ ሰዉን ሳይነጣጥል በነሲብ የሚወድና ስለፍቅር ራሱን መስዋዕት እንደሚያደርግ ይነግረናል፡፡ በልብ ወለድ ታሪኩ መጀመሪያ ላይም እንዲህ በማለት ለራሱ ያወራል፡፡

“ከዚህ ምድርና ከንሮዋ ያተረፍኩት ለሰዉ ልጅ ያለኝን ጽኑ ፍቅር ነዉ፡፡” (ቅበላ፣ 2009፣ 5) በማለት እራሱን ልክ እንደ ፍቅር ሃዋርያ ይቆጥራል፡፡

ማቲዎስ እንዲሁ እራሱ ከሚናገረዉ ተነስተን ስለሰዉ ልጅ ያለዉን ጥልቅ ፍቅር ይናገር እንጅ ስለፍቅር ብሎ ግን ምንም ዓይነት ሃዋርያዊ ተግባር ሲፈጽም አይታይም፡፡ እንዲያዉም በልጅነቱ ያጣዉን (ያላገኘዉን) የእናትና አባቱን ፍቅር ከማህበረሰቡ ያገኘ ስለሚመስለዉ ብዙ ጊዜ ብዙ ሰዉ በተሰበሰበበት ቦታ መገኘትን ያዘወትራል፡፡

ስለፍቅርም ቢሆን ሰዉን እወዳለሁ፣ በሰዉ ፍቅር ወድቄያለሁ ብሎ የሚያስብ እንጅ በሚለዉ ፍቅር ዉስጥ የሚኖር ገጸ ባህሪይ አይደለም፡፡ ይህንንም በተግባር ላለማሳየት እናቱ  የአባቱን ፍቅር እንዳያገኝ የከለከለችዉ ስለሚመስለዉ በጣም እንደሚጠላት ይናገራል፡፡ የአክስቱን ልጅ ኩንየን ብር ሰጥቶ ከቤት እንድትኮበልል አደረገ፡፡ በታሪኩ የመጨረሻ ክፍልም በጣም አፈቅራታለሁ ብሎ የሚናገርላትን ሶረኔን ገድሎ እራሱን ሲያጠፋ እንመለከታለን፡፡ ታዲያ የዚህ አይነቱ ተግባር እዴት ብሎ ነዉ ለሰዉ ልጅ ያለዉን ፍቅር የሚያሳይ እራሱንስ እንደሃዋርያ የሚያስቆጥር፡፡ ይህ በትክክል የሚያሳየዉ  አስተሳሰቡም ሆነ ስብእናዉ ከሌሎች የለየዉ መሆኑን፣ በዉስጡ ያለዉን ለራስ ታማኝ አለመሆንና ራስን የመጥላት ስሜት ለማጥፋት የሚያደርገዉ ያልተገናዘበና ደመነፍሳዊ እቅስቃሴ ነዉ፡፡

ማቲዎስ የሚያስበዉ ሰዉን ነጥሎ ሳይሆን በጋራ በማህበር መዉደድ እንዳለበት ብሎም ሰዉ ተነጥሎ ሳይሆን በጅምላ መውደድ አለበት ብሎ ያምናል፡፡ ይህ እሳቤዉ ደግሞ አንድ ማህበረሰብ ስለፍቅር (ስለመዉደድ) ከሚያስበዉ እሳቤዉ ጋር በእጅጉ ስለሚያለያየዉ ለባይተዋርነት  ሲዳርገዉ እናያለን፡፡ ስለፍቅር ራሱን እንዲህ ይሞግታል፡፡

> ያለጥርጥ ሶረኔን አፍቀሬአታለሁ፡፡ በፍቅር ላይ ፍቅር ይደረባል እኔ እኮ ከአለም ሁሉ ፍቅር ወድቄአለሁ ብየ የማስብ ሰዉ ነኝ፡፡ እናስ ሶረኔ ከየክቴ፣

ከአክስቴ፣ ከኩኑ፣ ከዘመናይ ፣ከእማማ ሽምስያ ... ከሁሉም የተሻለ ድርሻ ሊኖራት ይገባል እየሱስ ማንን ነጥሎ ወደደ? የምንኩስና ቆቤን መቅደዴ ቁርባኔን ማፍረሴ ይሆን ኢየሱስ ተነጥለዉ መወደድ የሚሹትን እያገደ ወደ ብዙሃኑ ሲቀላቅል ኖሯል። እናትና ወንድሞቹ እንኳን ሲፈልጉት 'ለእኔስ ወንድሞቸ የአባቴን ትእዛዝ የፈጸሙ' ብሏል። እኔ ግን ሶረኔን ወደ መንጋዋ መልሼ መዉደዴን በእኩል እንድትቃረጥ ማድረግ ተሳነኝ። የተሻለ ድርሻ ለእሷ መደብኩ። እንዴት አሳፍራለሁ? (ቅበላ፣ 2009፣ 20)

ማቲዎስ እንደዚህ ራሱን እንደ እግዚአብሔር በመቁጠር ሰዉን እኩል እወዳለሁ ይበል እንጅ እዉነተኛ ማንነቱ ግን ሶረኔን በማፍቀሩ ገሃድ ሲወጣ በራሱ አንደበት እራሱን ሲወቅስ እናያለን። ማቲዎስ የሚተርከዉ የሚኖርበትን ሳይሆን የሚያልመዉንና ከንቱ የሆነዉን ምኞቱን ነዉ። ይህን እንደነገረ ህላዌ እሳቤ ስናየዉ አንድ ሰዉ ከራሱ አለም ዉጭ ሆኖ ያገኘዋል። በፍላጎቱ ሳይሆን ያለምርጫዉ እርግጠኛ ወዳልሆነበት ህልዉናዉ የተወረወረና በልቡ እንደተራራ ተቆልሎ ወደሚያስጨንቀዉ ህልዉና እንደተጣለ ሆኖ ይሰማዋል ። ይህ ማለት አለም ሰዎች ከራሳቸዉ የሚገለሉባት እና ለራሳቸዉ ባእድ የሚሆኑባት ናት።(ሆንድሪች፣ 1995)

"የሰዉ ልጅ እንደ ጨዉ ወይም እንደ ስኳር አንኳሮች ሟሙቶ ቢደባለቅ ፣ አልያም እንደላመ ዱቄት ተቦክቶ በሊጥ ህልዉና እኛ ብቻ ብሎ ቢኖር ፣ እዚህ የመዋጮ ንሮ ዉስጥ እራሴን መስዋዕት አድርጌ ስብዕናየን አደባልቃለሁ።" (ቅበላ፣ 2009፣ 20)

ከዚህ አነጋገሩ የምንረዳዉ ማቲዎስ አብሮ የመኖርና የመቀላቀል፣ እኔ የሚለዉ አስተሳሰብ ተቀይሮ እኛ የሚለዉ አስተሳሰብ እንዲነግስ ከመፈለግና በከንቱ ምኞትና ሃሳብ ከመዋተት በዘለለ ይህን ሃሳቡን ሲኖረዉ አይታይም። እንዲያዉም ይህ የሚያሳየዉ የሆነ ሃይል መጥቶ አንድ ሁኑ ተቀላቀሉ ፣ በጋራ ኑሩ የሚል መለከት አስኪነፋ የሚጠብቅ አይነት ገጸ ባህሪ ነዉ።

ማቲዎስ ታዲያ ከገባበት ርዕይ አልባነት ለመዉጣት በርካታ ሰዎች በሚገኙበት ቦታ ከማዘዉተር፣ በታክሲ ከመሄድ በባስ መሄድን ቢመርጥና ከበርካታ ሰዎች መካከል እንዳለ ቢመስለዉም በዉስጡ ያለዉን ርዕይ አልባነቱን ግን ሊያስወግድለት አልቻለም። ይህን እጣ ፈንታዉን አምኖ ለመቀበልም ሲሞግት እናየዋን።

"እንደተቀረዉ ሰዉ ለስድብ የተጋነነ ፍች ሰጥቼ አላዉቅም። ስድብ ብቻ አይደለም ስስት፣ ቅቅት፣ ጥላቻ፣ ዉዴታ፣ ሽሚያ፣ ዝርፊያ፣ ማጭበርበር፣

ዝሙት፣ ድብድብና እነኝህን የመሳሰሉ የሚከሰቱት አብሮ ከመኖርና ከመቀራረብ በመሆኑ ዘወትር ይቅርታ ሊነፈጋቸዉ አይገባም ባይ ነኝ። የሰዉ ልጅ ከነዚህ ነገሮች የሚድነዉ ብቸኛ ሆኖ በባይተዋርነት ህይወቱን ሲገፋ ብቻ ነዉ። እኔ እደሚገባኝ ደግሞ አብሮ መኖር ከሚፈጥራቸዉ 'መጥፎ' ነገሮች የከፋዉ መጥፎ ብቸኝነትን መርጦ ህይወትን በዚሁ እቅድ መምራት ነዉ።" (ቅበላ፣ 2009፣ 11)

ማቲዎስ እንዲህ እያለ በሃሳብ ባህር ከመዋለል ዉጭ በቤተሰቡም ሆነ በማህበረሰቡ ዙሪያ ይህ ነዉ የሚባል ተሳትፎ ሲያደርግ አይስተዋልም። እንዲያዉም እሱ ራሱ የፍቅር ሃዋርያ ነኝ ፣ አብሮ መኖር ጥሩ ነዉ እያለ ለራሱ ያወራል እንጅ አሳ ከምትመስል ቤቱ ብቻዉን እንደሚኖር ታሪኩ ይነግረናል። ሰዎች ስለሱ ያላቸዉን መጥፎ አመለካከት እንኳ ሲነግሩት አሜን ብሎ ይቀበላል። አክስቱ ስትሰድበዉ ዝም ብሎ ይቀበላል። ሶረኔ እንደማትወደዉ ስትነግረዉ ይህንም በጸጋ ይቀበላል እንጅ ፍቅሩን ለማሳየት ጥረት ሲያደርግ አይታይም። ስለራሱ እንዲህ ነኝ ብሎ ከመናገር ይልቅ ሰዎች ስለሱ የሚነግሩትን  አሜን ብሎ ሲቀበል ይሥተዋላል። ከዚህ በተቃራኒዉ ማድረግ ይችል ነበር። ፍቅራቸዉንና እንክብካቤያቸዉን ለማግኘት መታገልና ማድረግ የሚችለዉን ሁሉ የማድረግ እድል ነበረዉ። ነገር ግን አንድ ነገር ለማድረግ ወይም ትክክል ባልሆነዉ ነገር ላይ ለማመጽ ቸልተኛ ነዉ ማለት ይቻላል። ከዚህ ይልቅ ራሱን በመጥላት በመካድና ለራሱ የሚሰጠዉን ግምት ዝቅ በማድረግ በሃሳብ ባህርና በማይተገበር ከንቱ ምኞች ሲዋልል እናየዋለን።

በአጠቃላይ አነጋገር ማቲዎስ ወደ ህይወት ራሱን የሚወረዉረዉ በፍቅርና በጉጉት ሳይሆን በቸልተኝነት፣ በግድ የለሽነትና ፍላጎት በማጣት ስሜት ነዉ።

መገለሉን በገሃድ የምናየዉ ምንም እንኳን የሚኖረዉ በብዙ ሰዎች ተከቦ ቢሆንና ሰዉ በተሰበሰበበት ቦታ ራሱን ለማዋጣት ቢሞክርም በነፍስም ሆነ በአስተሳሰብ ከሰዎች ጋር የሚያቆራኘዉ ነገር እንደሌለ ስንመለከት ነዉ።

"እዉነቷን ነዉ። ብቸኝነት ያስፈራል። የተጋነነዉ የአባቴ በሽታ ትዝ አለኝ። ለካስ ከሰዉ የተገነባ የብቸኝነትም እስር ቤት አለ"? (ቅበላ፣ 2009፣ 51)

ሌላዉ ማቲዎስ አብዛኛዉን ጊዜ የሚያስበዉ ራሱን እንደ ሃዋርያ ነዉ።

"ከፍታ ቦታ ላይ ሆኘ ቁልቁል የመመልከት እድል ሲገጥመኝ አቅሜን ያላገናዘበ ስሜት ያድርብኛል፡፡ ከእግዚአብሔር መንበር ላይ ሆኘ ፍጡሩን በትዝብት እንዳስተዉል የተወከልኩ ይመስለኛል፡፡" (ቅበላ፣2009፣ 27)

ይህ የሚያሳየን ራሱን እንደሰዉ ሳይሆን እንደ ሃዋርያ ከዛም ከፍ ሲል እንደክርስቶስ በማሰብ እራሱን ከሰዎች መካከል ነጥሎ እንደሌላ አካል የቆጠረ መስሎ ብናይም ሲኖረው ግን አንመለከትም፡፡ ለዚህ ማስረጃም የሚከተለውን መመልከት ይቻላል፡፡

"… ህይወቴ ባዶ፣ ምኞቴ ከንቱ፣ ፍላጎቴ የማይረባ ነዉ፡፡ ይሄን ሁሉ የምገላገለዉ ከሰዎች ጋር ስቀላቀልና መካከላቸዉ ስገኝ ነዉ፡፡ እኔ ማለቴን ትቸ እኛ የማለት መብት ሳገኝ ነዉ፡፡" (ቅበላ፣ 2009፣ 177)

"እግዚአብሔርን የሚያስደስተዉ ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት፣ እርግደት፣ ቅዳሴ፣ ዉዳሴ … ሳይሆን እንዲህ ያለዉ የሰዎች ፌሽታ ይመስለኛል፡፡ እንኳን እሱ እኔ እነሱን በማየት ምን ያህል ተደሰትኩ?" (ቅበላ፣ 2009፣ 28)

በማለት አምላክ ምን እንደሚያስደስተዉና ለእሱ የጓደኛዉ ያክል ቅርበት እንዳለዉ በድፍረት ሲናገር እናየዋለን፡፡ ነገር ግን ማቴዎስ እንዲህ እያለ ከመዘባረቅ ያለፈ ለራሱ ምንም ክብር የሌለው ራሱን ዝቅ አድርጎ የሚያይ ርዕይ አልባ ገጸባህሪ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የስራ ባልደረባዉ መንክርም እንደማይረባና ተራ የሆነ ሰዉ እንደሆነ ሲነግረዉ ይህንንም በጸጋ ይቀበላል፡፡ በአንድ ወቅት ማቲወስ የጻፈዉን የድርሰት ስራ መንክር እንዲያይለት ሲሰጠዉና መንክርም ይህ ልብወለድ ሳይሆን ተራ አሉባልታ ነዉ ብሎ ሲመልስለት ወዲያዉኑ ጽሁፉን ቀዳዶ ይጥለዋል፡፡ ይህ የማቴዎስን ርዕይ አልባነት ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ማቲዎስን ስናየዉ የእኔ ልኖረዉ የሚገባ የህይወት ጎዳናየ ይህ ነዉ ብሎ ከማሰብና የራሱን ምርጫ ከመዉሰድ ይልቅ ሰዎች በመረጡለት ጎዳና የሚጓዝ አይነት ገጸ ባህሪይ ነዉ፡፡

እንደ ነገረ ህላዌ እሳቤ ትክክለኛ ሰዉ መሆን ማለት አንድ የተረጋገጠ ሁኔታ ወይም አንድ ሰዉ ያለበትን ቅጽበት መረዳት ሲሆን ሁኔታዉ አስከሞት ሊያደርስ ይችላል በዚህ አለም ላይ ለመኖሩ እየተጨነቀና እያዘነ ባለበት ስሜት ዉስጥ ሆኖ ስለሁኔታዉ የራሱን ምርጫ መምረጥ እና ያሰዉ እንደዛ ለመሆኑ ሃላፊነቱን መዉሰድና ዉጤቱን መቀበል ማለት ነዉ (ድሬፋስ እና ራትሆል፣ 2006)፡፡

በማቲዎስ ህይወት ግን የምናየዉ በትክክል የሚኖርበትን ህይወት ከመረዳት ይልቅ የማይኖርበትን ከንቱ ምኞት በመመኘት በከንቱ በመዋተት በርዕይ አልባነት የሚኖር አይነት ገጸባህሪ ነዉ። ይህን ደግሞ በተለያዩ የታሪኩ ክፍሎች እናየዋለን።

"… ህይወቴ ባዶ፣ ምኞቴ ከንቱ ፣ ፍላጎቴ የማይረባ ነዉ። ይሄን ሁሉ የምገላገለዉ ከሰዎች ጋር ስቀላቀልና መካከላቸዉ ስገኝ ነዉ። እኔ ማለቴን ትቸ እኛ የማለት መብት ሳገኝ ነዉ።" (ቅበላ፣ 2009፣ 177)

ማቴዎስ ወደዚች ምድር ሲመጣ  እራሱን ለሰዉ ልጅ ፍቅር የተላከ ሃዋርያ አድርጎ ከመቁጠር በዘለለ በሚለዉ ፍቅር ዉስጥ ግን የሚኖር ሰዉ አለመሆኑና በልጅነት ዘመኑ ያላገኘዉን ፍቅር ከማህበረሰቡ አገኛለሁ በሚል ከንቱ ምኞት የሚዋትት አይነት ሰዉ ነዉ። እኔ ለራሴ አዉቃለሁ ሳይሆን ማህበረሰቡ ስለእኔ ያዉቅልኛል ብሎ የሚያስብ ግለሰባዊ ማንነትን አጥፍቶ ማህበራዊ ተቋምን እገነባለሁ ብሎ በከንቱ የሚያስብ መሆኑን ያሳየናል።

Miles (1991፣ 202) እንዳለው፤ አንድ ሰው በህይወት አልነውም በዩኒቨርስ ውስጥ ለመገኘቱ ምክንያት የሆነውን ታላቅ ተግባር በማከናወን ወይም የጀግንነትን፣ የተጋዳሊነትን ግዳጅ በመፈጸም በጥበብ ኖሮ በጥበብ ማለፍ ካልቻለ፣ ሞቱ ጊዜውን ያልጠበቀ ሞት ነው።

በአጠቃላይ በማቲዎስ ህይወት ከታሪኩ መጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ የምናየዉ በህይወቱ ይህ ነዉ የሚባል ጥሩ ነገር የሌለዉ፣ ስለ ሰዉ ልጅ ፍቅር ወደዚች ምድር እንደተላከ ከማስመሰል በዘለለ ለራሱም ሆነ አፈቅረዋለሁ ለሚለዉ ማህበረሰብ ፍቅር የሌለዉ ይህን ችግሩን ደግሞ አምኖ የማይቀበልና ትክክል የሆኑ ነገሮችን ከማድረግ ይልቅ ትክክል ባልሆኑት ነገሮች ላይ በመዝመት ከማይወጣዉ የህይወት ዉጥንቅጥ ራሱን የዘፈቀ ገጸባህሪ ነዉ። በህይወቴ ይህንን አደርጋለሁ  ልኖረዉ የሚገባኝ ህይወት ይህ ነዉ የሚለዉ ምርጫ የሌለዉ፤ ለሚያደርጋቸዉ እያንዳንዱ ድርጊቶች ሃላፊነትን የማይወስድ እንዲያዉም በፍቅር ሰበብ ተወዳጅነትና ተቀባይነትን አገኛለሁ በሚል ከንቱ ምኞት ራሱን ወደ ሞት የጨመረ ከንቱ ገጸባህሪ ነዉ።  ሰዉን እንደ ክርስቶስ በጅምላ እወዳለሁ የሚል ባዶ ምኞት ሰንቆ በከንቱ የሚንከራተት፣ ሰዉን ለመዉደድ መጀመሪያ ራስን መዉደድ፣ ሌሎችን ለማክበር ቅድሚያ ራስን ማክበር፣ ለለሎች ከመኖር በፊት ለራስ መኖር ሲገባዉ እነዚህን ነገሮች በሙሉ ለሰዉ ልጆች አደርጋለሁ በሚል ከንቱ ሃዋርያነት በከንቱ ሲባዝን ኖሮ በከንቱ የሞተ ለመሆኑ ታሪኩ

ማስረጃ ነዉ፡፡ ስለዚህ ማቴዎስም ሞትን በድል መወጣት ያልቻለ ሞትን በሞት የተቀበለ ርዕይ አልባ ገጸ ባህሪ ነው፡፡

## የመንክር ጊዜውን ያልጠበቀ ሞት

በዚሁ የልብ ወለድ መጽሃፍ የምናገኘዉ ሌላው ጊዜው ያልጠበቀ ሞት ተጠቂ መንክርን ነዉ፡፡ ከንቱና ዉጥንቅጡ በወጣ አለም ዉስጥ የሚኖረዉ መንክር ህይወትን የሚኖራት እንዲሁ ያለምንም ጉጉትና ፍቅር ነዉ፡፡ በልጅነት እድሜዉ ያለ እናትና አባት እንዲያድግ ስለተገደደ በኂላ ላይም በህይወቱ ልኖረዉ የሚገባኝ ህይወት ይህ ነዉ የሚለዉ አላማም ሆነ እቅድ የለዉም፡፡ ለዛም ነዉ ገና ስምንተኛ ክፍል እያለ አስቴር ከእሷ ጋር እንዲሄድ ስትጠይቀዉ ያለምንም ማመንታት ተከትሏት ሲሄድ የምናየዉ፡፡

መንክር የኢሃፓን የትግል መስመር የተቀላቀለዉ አምኖበት ሳይሆን እንዲሁ አስቴርን በመፈለግ፡፡ አስቴርን መፈለጉ ሳያዉቀዉም ቢሆንም እናቱን የመፈለግ ያክል ሆኖ ነዉ የሚሰማዉ፡፡

በትግል መስመሩም የሚሰጠዉን ተልኮ ከፈጸመ በኂላ ሪፖርት እንኳን ሳያደርግ ክፍሉ ገብቶ ይተኛል፡፡ ይህ ሁኔታዉ አስቴርን በጣም ያስገርማታል፡፡ ከተልዕኮ መልስም እንዲህ ስትለዉ እንሰማለን፡፡

"የታጋይ ወጣት ድፍረት አለህ፡፡ ድፍረትህ ግን እንደ አንድ ታጋይ ወጣት ሁሉ ትግሉ ላይ ተስፋ ከመጣል የመነጨ አይመስለኝም፡፡ እንዲያዉም ለህይወት ዋጋ ከመንፈግ ከተስፋ መቁረጥ የምትደፍር ሆኖ ነዉ የሚሰማኝ፡፡" (ቅበላ፣ 2009፣ 122-123)

አጠቃላይ ስለህይወቷና አንዲት ልጅ እንዳለቻት እሷንም ሳታሳድግ ወደትግል መስመሩ እንደገባች ታጫዉተዋለች፡፡ ይህ ድርጊት ታዲያ የዉስጡን ቁስል ስለሚነካበት በአስቴር የታከመ እስኪመስለዉ ድረስ በፍጹም አስቴርን ማጣት አይፈልግም፡፡ እሷ የትእንዳለች እንዲናገር መንክር ወደ ማሰቃያ ስፍራ ይወሰዳል፡፡ በርካታ ስቃይና እንግልት እየደረሰበት በሌሎችም ላይ እያየ ምንም ቅንጣት አይሰማዉም፡፡ አጎቱ ተጫኔ እንኳ ካልተናገረ በከንቱ እንደሚገደል እየነገረዉ ምንም አይመስለዉ፡፡ ለሱ የትግል መስመሩ ሳይሆን ትልቁ ጉዳዩ አስቴር ናት፡፡ በእሱ አስራትና ሞት የሚገናኙ እናትና ልጅን እያሰበ ደስተኛ ነበር፡፡ የእነሱ ፖለቲካ ለእሱ ምኑም አይደለም፡፡ አስቴርንና ልጇን የእሱና የእናቱ ምሳሌ አድርጎ ስሏቸዋል፡፡

“ደጋግሞ ተጫኔ መረመረኝ፡፡ አስቴር የትናት? የምድር መንቀጥቀጥ የተነሳ የሚያስመስል ዱላ፡፡ ‘አስቴር የት ናት? አስቴር የት ናት? ... እኔ አስባለሁ፡፡” (ቅበላ፣2009፣129)

ከዚህ ላይ የምንረዳዉ ነገር ቢኖር የመጀመሪያዉ መንክር ይህ ነዉ የሚለዉና የሚያንጓዉ ነገር በህይወቱ አለመኖሩን ነዉ፡፡ ለመኖሬ ተስፋ ያላትን አስቴርንም አንድ ቡድን ሊያጠፋት እንደተቃረበ ያዉቃል ይህንን ለመታገል ታዲያ እራሱን ለመስዋትነት ሲያቀርብ እናየዋለን፡፡

“ተጫኔ በእኔ ሁኔታ ታክቷል ‘አንተ እንከፍ! በከንቱ መሞትህ ነዉ፡፡ በቅርብ ጊዜ ተወስደህ ትገደላህ’ አለኝ፡፡ ግድ አልነበረኝም፡፡ በእኔ ሞት የሚተያዩ እናትና ልጆች አሉ፡፡” (ቅበላ፣ 2001)

ለመንክር በህይወት መኖርና መሞት ትርጉማቸዉ አንድ ነዉ፡፡ ይህን ደግሞ በተለያዩ የታሪኩ ክፍሎች እናየዋለን፡፡ ግን ደግሞ አብሮ ከሷ ጋር እንዳይሞት መኖሩ ለአስቴር ትልቅ ዋጋ እዳለዉ ያምናል እሱም የአስቴር ልጅ ትእግስት ናት፡፡ ለዚህም ነዉ አስራ ሁለት አመት በበዓድ ሃገር ሲንከራተት ቆይቶ በወቅቱ የነበረዉ አገዛዝ ሲወድቅ ወደ ሃገር ቤት የተመለሰዉ፡፡

መንክር ከተመለሰ በኂላም አስቴር የጣለችበትን አደራ ለመወጣት መኖሩን ታግሶ ትእግስት ትክክለኛ ማንነቷን እንድታዉቅ ትክክለኛ ጊዜዉ አስኪደርስ በትእግስትና በተስፋ ሲጠብቅ እናየዋለን፡፡

“ማቲዎስ መንክርን “አንተ የተረጋጋህ ሰዉ ነህ ሁሉም ነገር አለህ ሲለዉ ሁሉንም ነገር ስለማልፈልግ ነዉ ሁሉም ነገር ያለኝ የመሰለህ፡፡” (ቅበላ፣ 2009፣ 143)፡፡ ከዚህ ንግግሩ የምንረዳዉ መንክር ከዚች ምድርና ከንሮዋ ምንም ነገር እንደማይፈልግ ያሳየናል፡፡ ትዳር የለዉም፡፡ ስለቀጣይ ህይወቱም ምን እንደሚፈልግና እደሚያስብ ምንም ነገር ሲናገርም ሆነ ሲያደርግ አናየዉም፡፡ በህይወት መቆየትም የሚፈልገዉ ለትእግስት ሲል ብቻ እንደሆነ ይናገራል፡፡

“ከዚህ ምድር ላይ ያለእሷ ማንም የለኝ፡፡ መኖሬን ታግሽ የምንከላወሰዉ ለእሷ ብቻ ነዉ፡፡ግን የኔ መኖር የተስቦ ምንጭ ሆኖባት አንተን የመሰለ ክፉ በሽታ የሚጥልባት ከሆነ ያለጥርጥር እገድልሃለሁ፡፡” (ቅበላ፣ 2009፣ 105)፡፡ በህይወት ለመቆየቱ የሙጥኝ ያለዉ ትእግስትን መሆኑ በተደጋጋሚ በታሪኩ ሲናገር ይደመጣል፡፡ እንደነገረ ህላዌ እሳቤ ይህ የሚያሳየን ሰዎች በህይወታቸዉ ትርጉምን የሚያገኙት ትርጉም አልባ በሆነ ህልዉናቸዉ በሚያደርጉት ያልተቋረጠ ትግል ነዉ፡፡ ሪቻርድ ቴለር (በዱል ጃክዌ ፣ 2001) ለዚህም ነዉ መንክር ትርጉም

በሌለዉ አለም ዉስጥ እየኖረ የህይወት ትርጉምን ለማግኘት ትእግስትን የሙጥኝ ሲል የምናየዉ ብሎም በህይወቱ ብዙ ተስፋ አስቆራጨራጭ ሁኔታዎች እየገጠሙት መኖሩን ታግሶ ለመኖር ሲሞክር የምንመለከተዉ፡፡

በአጠቃላይ ከልቦለዱ ታሪኩ የምንረዳው መንክር ማይልስ (1991፣202) እንዳለው፣ በህይወት በርዕይ አልባነት ኖሮ ብሎ በጥበብ ኖሮ በጥበብ ማለፍ ያልቻለ ገጸ ባህሪ ስለሆነ ጊዜው ያልጠበቀ ሟች ነው ማለት ይቻላል፡፡

## የአስቴር ጊዜውን ያልጠበቀ ሞት

አስቴር በወቅቱ የነበረዉን ፖለቲካ በመንቀፍ ትክክል ነዉ ብላ ባሰበችዉ የኢሃፓ መስመር ተሰልፋ ህዝቤን ነጻ አወጣለሁ በማለት ቆርጣ የተነሳች ሴት ናት፡፡ ይች ሴት ታዲያ ዘወትር ማታ ማታ መንክር ከሚኖርበት ቤት በመሄድ ከባለቤቷ ጋር የሚበላ ነገር እንዲያመጣ ያዙታል፡፡

አስቴር መንክርን የእናት ያክል ትበልጠዋለች፡፡ አጠቃላይ ስለህይወቷና አንዲት ልጅ እንዳለቻት እሷንም ሳታሳድግ ወደትግል መስመሩ እንደገባች ታጫዉተዋለች፡፡ አንድ ቀን ግን የተደበቁበት ቤት በታጣቂዎች ይከበብና አስቴር ስትፈለግ ትጠፋለች፡፡

አሰቴርም በበኩሏ እሷን ለመያዝ መንክርን መያዣ እንዳደረጉት ስለምታዉቅ እራሷን አሳልፋ ስትሰጥ እናያለን፡፡ በዚህ መንክር በጣም ይበሳጫል፡፡ ግን ደግሞ አብሮ ከሷ ጋር እንዳይሞት መኖሩ ለአስቴር ትልቅ ዋጋ እዳለዉ ያምናል እሷም የአስቴር ልጅ ትእግስት ናት፡፡

አስቴር በቀይ ሽብር ምክንያት ምክንያት የኮሌጅ ትምህርቷን አቋርጥና አንድ ልጇን፣ ትግስትን ትታ ወደ ትገሉ ተቀላቅላ ብዙ ከደከመች በኂላ በራሷ ባለቤት ያሰበችውን ርዕይ ሳትደርስ በመሞቷ ጊዜው ያልጠበቀ ሞትን ተቋድሳለች ማለት ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ አራት፡- ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ዋና አላማው የነገረ ህላዌ ፍልስፍናን መሰረት በማድረግ በልቦለዱ ውስጥ የተንጸባረቁ የሞትን ጭብጥ ተንትኖ ለማሳየት ሞክሯል፡፡

ጥናቱ አይነታዊ የምርምር ዘዴን መሰረት በማድረግ በጥልቅ ንባብ ተተንትኖ ቀረበ ሲሆን ለጥናቱ አስፈላጊ ሆኑ መረጃዎች ደግሞ ቀዳማይና ዳህራይ የመረጃ ምንጮችን መሰረት በማድረግ ተሰብስበዋል፡፡

በልቦለዱ ዉስጥ የተንፀባረቁ የሞት ጭብጦችን ተንትኖ ለማሳየት የነገረ ህላዊ ንድፈ ሀሳብ ለተመረጠዉ ልቦለድ መተርጎሚያነት ጥቅም ላይ ዉሏል፡፡

ለትንተና በተመረጠዉ ረጅም ልቦለድ ዉስጥ የሚገኙትን ዋና ዋና እና ንዑሳን ገፀባህርያት እንደአስፈላጊነቱ ዓለማዊ ኑባሬያቸዉ ምን እንደሚመስል እና በህይወታቸዉ ዉስጥ ያለፈባቸዉ ገናን የህላዌ ክስተቶች የትኞቹ እንደሆኑ በመፈተሽ ነዉ የህልዉናዊነት፣ ሞት ጭብጦቹ ተለይተዉና ተተንት ነዉ የቀረቡት፡፡

ስነ ህይወታዊ ሞት፣ ራስ ግድያና ጊዜውን ያልጠበቀ ሞት በልቦለዱ የተንፀባረቁና በዚህ ጥናት ትኩረት ተደርጎባቸዉ የተሰሩ ዋና ዋና ጭብጦች ናቸዉ፡፡

ለነዚህ ጭብጦች መከሰት ከሚጠቀሱ ምክንያቶች መካከል ከልዩ ልዩ ችግሮችና ስቃይ ለማምለጥ፣ የህይወት ትርጉም ሲጠፋ፣ ሀገርን ዳር ድንበር ለማስከበር፣ የፍቅርን ህይወት ለመመስረት፣ የሰዉ ልጅ ለምን እንደሚኖርና እንደሚሞት ለማወቅ፣ የራስ ማንነት ሲታጣ፣ ሰዉ ልጅ የህይወት ዑደት፣ የቀናት እና የፀሐይ መዉጫና መግቢያ ድግግሞሽና ተመሳሳይ መሆን፣ ባልና ሚስት እንድሁም የፍቅር ጓደኛሞች በሞት ምክንያት ሲለያዩ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የገፀባህሪያት ሞት በገፀባህርቱ ህይወት ላይ የተለያዩ ተፅዕኖዎችን አሳድረዋል፡፡ መንክር እናቱን በሞት ማጣቱ ሙሉ ለሙሉ እምነቱን ከማህበረሰቡም ከአምላኩም በማንሳት ለባይተዋርነት ሲዳርገዉ ማቲዎስን ደግሞ ለጭንቀት ለተስፋ ቢስነት ብሎም ለሞት ዳርጎታል፡፡ በሌሎች ገጸባህሪያት ላይም ተጽእኖዉ ከፍተኛ ሆኖ እናየዋለን፡፡ እንዲሁም ርዕይ አልባነት፣ ፍርሃት፣ ራስ ግድያ፣ ሀዘን፣ ሞት፣ ግዞት፣ ለባይተዋርነት፣ ተስፋቢስነት

ከእዉነተኛ ዓለም ይልቅ የህልም ዓለምን መምረጥ በገፀባህያቱ ላይ ከተከሰቱ ተፅዕኖዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡

በአጠቃላይ በቅበላ ረጅም ልቦለድ ያሉ ገጽ ባህሪያት ሞት ለመኖር ወይም በልቦለድ ውስጥ ለመገኘቱ ምክንያት ምክንያት ታላቅ ተግባር ያከናወነ፣ ታላቅ ህልሙን ያሳካ፣ በጥበብ ኖሮ በጥበብ በድል የሞተ ለራስ ትንሳኤ ለሌሎች ርዕይ ማደሪያነት የሚያበቃ አይደሉም ማለት ይቻላል፡፡ እንዲያውም ተስፋ የተጣለባቸው ገጸ ባህሪያት ሞት ለቀሪዎቹ ገጸ ባህሪያት ልብ ስብራት ምክንያት ነው የሚሆነው መንክርና ትግስትን ጨምሮ በህይወት ከተረፉ ገጸ ባህሪያት መሃል አንዱም ለባለተስፋነት፣ ለባርዕይነት፣ ለባለትንሳኤነት አይታጩም፡፡ ከሟች ገጸ ባህሪያት መሃል አንዱ የገጸ ባህሪያት አሟሟት ነው፡፡ ከገጸ ባህሪያት መሃል የበርካቶች አሟሟት ድንገት ደራሽ ሞት ብሎ ነው፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


መስለች ተሻገር። (2010) ። "የነገረ ህላዌ ጭብጦች በአለማየሁ ገላጋይ *ቅበላ*፤ የነገረ ህላዌ ንባብ"። በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍሌ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ያልታተመ።

ቴዎድሮስ ገብሬ። (2001) ። *በይነዲሲፒሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ*፡ አዲስ አበባ፣ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ።

ንጉስ መስሰ። (2013) ። "የህልውናዊነት ጭብጦች ትንተና በትዝታሽ ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ ረጅም ልቦለድ"። በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍሌ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ያልታተመ።

አለማየሁ ገላጋይ ፡፡ (2009) ፡፡ *ቅበላ* ፡፡ አ.አ፣ ኢ.ምፕረስ ማተሚ.ያ ድርጅት፡፡

አንለይ ወንዲራድ። (2012) ። ስነ ልቦናዊ ሞት በበእውቀቱ ስዩም እንቅልፍና እድሜ። ለባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለድህረ ምረቃ የቀረበ ጥናት

ዘሪሁን አስፋው። (1992) ። *የስነ-ጽሁፍ መሰረታዊያን።* አ.አ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ያለው እንዳወቅ። (2009) ። *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር*፡3ኛ እትም። ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ተስፋ ስዩም ፕሪንቲንግ ፕሬስ።

Azhar, I. (2013). "A Critical Study of Existentialistic View of Education and Its Relevance to Human Existence and Progress. (PHD Thesis) Aligarh (India).Aligarh Muslim University.

Dreyfus,H and Wrathall, M (Eds).(2006). *A companion to Phenomenology and Existentialism.*Australia; Blackwell publishing ltd.

Existentialism. (2004). *The American heritage dictionary of the English language*.

Flynn, T. (2006). *Existentialism: A very short introduction*. New York: Oxford university press.

Honderich, T. (Ed). (1995). *the oxford companion to philosophy*. New York: Oxford University press.

Kaufman, W.(ED).(1989). *Existentialism from Destoyevsky to Sartre.*N.P: Meridian publishing company.

Macqarrie, John.1972. *Existentialism: An Introduction, Guide and Assessment.* New York: Penguin Books.

Mallah, J.A. (2016). “Historical Roots and Basic Themes of Existential Philosophy: An Analysis”. Pune Research World ISSAN 2455-359x: An International journal of Interdisciplinary studies, Vol. 1, Issue. 2.

Michelman, S. (2008). Historical Dictionary of Existentialism. United Stats of America: Scarecrow Press Ltd.

Mobini, M. and Salim Pour, M. (2016). International Academic Journal of Humanities. Vol.3, No. 8, 2016. Pp. 81-89.

Reinhardt, K.F. (1952). *The existentialist revolt.* USA: The Bruce publishing company Milkwaukee.

Solomon, C. R. (2003). Living with Nietzsche: What a Great “Immoralist” Has to Teach Us. New York: Oxford University Press, Inc.

Solomon, R. and Sherman,D.(2003).*The Blackwell guide to continental philosophy.*

Australia: Blackwell Publishing Ltd.

Tseday Wondimu. (2007). *The case of existence in Fikir Eskemekabir, Kadimas Bashager and Gracha qachaloch*: From existentialist perspective. (MA thesis). Addis Abeba. Addis Abeba university.

Westphal, Merlod. 1984. God, Guilt and Death: An Existential phenomenology of Religion. Bloomington: Indian University press.

Wolcot, H.F. (1992). “Posturing in qualitative Research: In MDLE Compet, W.L, Millroy & J. Preissle” (eds). The Handbook of Qualitative Research in Education. Santiago: Academic press; pp.3-52